# ኦርቶዶክሳዊነት እንዲህ ነው!

## The Early Orthodox Church Doctrine

መስከረም 1999 ዓ.ም

በመጋቢ ጥበብ ሰሎሞን

© ይህንን መጽሐፍ ያለደራሲው ፈቃድ ማሳተም የተከለከለ ነው።

## መታሰቢያነቱ

ይህ መጽሐፍ «ለሥሉስ ቅዱስ /ለሥላሴ/ ራሴን አስገዝቻለኹ፣ በስላሴ ላይ አራተኛ አካል አልጨምርም»[1] በማለት ሠማእት ለሆኑት ለአባ እስጢፋኖስ ዐምደ ሃይማኖት ወማኅቶተ ክርስቲያን፣ እና ቤተ ክርስቲያኗ አባቶች የሠጧትን እውነት ብቻ ጠብቃ እስከ እለተምፅአት ዘላለም ድርስ እንድትቆይ በማድረግ ለተሠዉ እንዲሁም በመጋደል ላይ ላሉ ሠማእታት ሁሉ በእውነት ይሁንልኝ ::

## ምስጋና

በቅድሚያ ምስጋናና ክብር አልፋ ወኦሜጋ ለሆነው ለአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ይሁንልኝ:: ከዚያም ረቂቁን በኮምፒውተር ታይፕ ያለመሰልቸት ላደረገችልኝ እህት: የተጻፈውን ረቂቅ ላረሙልኝ ወንድሞች: ወደ ሕትመት እንዲደርስ በጸሎታቸው በሃሳባቸውና በገንዘባቸው ላገዙኝ ሁሉ እግዚአብሔር ሁለንተናቸውን ይባርክ እላለሁ ::

# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


1. የሽፋኑ ስእል መግለጫ 3
2. መግቢያ 5
3. ሐይማኖት 6
4. ዶግማ /ዶክትሪን/ አዕማደ ምስጢር 16
    1. ምስጢረ ስላሴ 17
    2. ምስጢረ ሥጋዌ ---------------------------------------- 31
    3. ምስጢረ ጥምቀት ---------------------------------------- 52
    4. ምስጢረ ቁርባን 55
    5. ምስጢረ ትንሳኤ ሙታን 61
5. ሰባቱ ምስጢራት ቤተክርስቲያን 67
    1. ምስጢረ ሜሮን .. 68
    2. ምስጢረ ቀንዲል 70
    3. ምስጢረ ክህነት 73
    4. ምስጢረ ተክሊል----------------------------------------74
    5. ምስጢረ ንስሐ ---------------------------------------- 77
6. ሥርዓተ አምልኮና አስተዳደራዊ አደረጃጀት ---------------- 80
7. የሐይማኖት መግለጫ /ፀሎተ ሐይማኖት ·91
    1. አንቀጽ አንድ ---------------------------------------- 99
    2. አንቀጽ ሁለት---------------------------------------- 104
    3. አንቀጽ ሦስት 110
    4. አንቀጽ አራት ----------------------------------------116
    5. አንቀጽ አምስት------------ ... 119
    6. አንቀጽ ስድስት — 127

አንቀጽ ሰባት ---------------------------------------- 133
አንቀጽ ስምንት ---------------------------------------- 138
አንቀጽ ዘጠኝ ---------------------------------------- 143
አንቀጽ አስር ---------------------------------------- 148
አንቀጽ አስራ አንድ ---------------------------------------- 148
አንቀጽ አስራ ሁለት ---------------------------------------- 151
8. የአስተምህሮው መጠቅለያ ---------------------------------------- 153
9. ይህን እውነት መጠበቅ ---------------------------------------- 158
1. ከቤተክርስቲያን ክርስቶስ የሚጠብቅባት ነገር -------- 159
2. ይህን እውነት ከመጠበቅ አንጻር የተጋደሉ አባቶች ---- 163
10. ማጠቃለያ ---------------------------------------- 169

## የሽፋኑ ስእል መግለጫ

ስእሉ የተገኘው በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ክልል በአክሱም ከተማ «እንዳ ኢየሱስ » ተብሎ በሚጠራው ደብር በቅጥረ ቤተ ክርስቲያኑ የውጭ ግድግዳ ላይ ተስሎ የሚገኝ ሆኖ ሐዋርያው ጳውሎስን የሚወክል የጥንት ስእል ነው።

በስእሉ ላይ የሚገኘው የግእዝ ጽሁፍ በ2ኛ ጢሞ 4፣6-8 ያለው ቃል ሲሆን ይሄውም «ወአንሰ ወዳእኩ ሰለጥኩ ወበጽሐኒ ዕድሜየ ለአዕርፎ። ሠናየ ገድለ ተጋደልኩ በድርየኒ ፈጸምኩ ወሃይማኖተኒ ዐቀብኩ ። እንከሰ ጽኑሕ ሊተ አክሊለ ጽድቅ ዘየዐስየኒ እግዚአብሔር ይእተ ዕለተ መኰንነ ጽድቀ ። ወአኮ ለባሕቲትየ ። አላ ለኩሎሙ እለ ያፈቅሩ ምጽአተ ዚአሁ።»ሲሆን

ትርጉሙም «በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሰዋልና የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአልና መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፡ ሩጫውን ጨርሻለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል።ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፡ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም ።» የሚል ነው ።

ስእሉ ለዚህ መጽሐፍ የተመረጠበት ምክንያትና ተዛምዶው ከጌታችን ከመድሐኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እግር ስር ተምረው ላስተላለፉልን ሐዋርያቶችና ከነርሱ ተቀብለው ወደአገራችን ኢትዮጵያ ባመምጣት እውነተኛውን ወንጌል አስተምረው ቤተክርስቲያናችንን በተጋድሎ የተከሉትንና ያጸኑትን የጥንት አባቶች ያስተማሩንን እውነተኛ ወንጌል በመጠበቅና ፍለጋቸውን በመከተል እግዚአሐርንም በማምለክ እንድንጸናና ጊዜ አመጣሽ ስህተት ትምህርቶች የሆኑትን ጠርጎ መማውጣት መልካሙን ገድል መጋደል እንድንችል ይህ መጽሐፍ ስለሚያሳስብ ነው።

## 1.መግቢያ

ወንጌል ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ህብረተሰቡ ለዘንዶ ይገብርና ዘንዶ ያመልክ እንደነበረ የጥንት መረጃ ቅርሶች በኢትዮጵያ ውስጥ በ“የሀ”ና በ“አድቤደራ” እንዲሁም በሌሎችም ሥፍራዎች አያሌ የጣዖት ምስሎችና መገልገያ ዕቃዎች እንዲሁም ቤተመቅደሶችና የፀሐይና የጨረቃ ምስል የተቀረጸባቸው የመገበያያ መሐልቆች በቁፋሮ መገኘታቸው ባዕድ አምልኮ በስፋት እንደ ነበረ ያሳያል:: አንዳንድ ጥቂት መረጃዎች ደግሞ በጥቂት የኢትዮጵያ ቦታዎች ከክርስትና በፊት ወደ ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነትና ባህል እንደገባ የሚያስረዱ አንዳንድ መስዋእቶች ይቀርቡበት የነበሩ የፈራረሱ ምኩራቦች ያስረዳሉ:: በተለይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በህዝቡ ዘንድ ያሉ አያሌ ልማዶችና ባህሎች ለምሳሌ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳይበሉ የሚከለክሏቸውን እንስሳትና አዕዋፍ አለመመገባቸው ግዝረት ስርዓት ማከናወናቸው ፤በኃዘንና በደስታ ጊዜ ያለው ስርዓት፤ የበዓላት አከባበር፤ የሴቶችና የሕጻናት ጌጣጌጥ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው የማኅሌት ሥርዓት የካህናቱ ልብሰ-ተክህኖ ካባው ድርቡ፣ ጸናጽሉ፣ ከበሮው፣ ኩፋሩ፣ መጠምጠሚያው፣ የታቦቱ ክብርና ሌላውም ሁሉ ከብሉይ ኪዳን ጋር መመሳሰሉ[2] አይሁዶች በተወሰነ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው እንደነበረና የብሉይ ኪዳን ስርዓት እንዳስተማሩ መገንዘብ ይቻላል::

በ330ዎቹ ዓመታት ፍሬምናጦስ /አባሰላማ/ ወንጌልን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት መንበረ መንግስታቸውን አክሱም አድርገው ስተቀመጡት አብርሃና አጽብሃ ለሚባሉ ሁለት ንድማማቾችንና

---

2. የኢ.ኦ.ተ.ቤ ታሪክ አባገርገሪዮስ /ሊቀጳጳስ ገጽ 13-16

ቤተሰቦቻቸውን በማስተማር በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ከቤተ መንግስት የተጀመረው አገልግሎት ቀስበቀስ እየተስፋፋ ወደታችኛው የህብረተሰብ ክፍል በመድረሱ ፍሬምናጦስ ይህን ሪፖርት ይዞ እስክንድርያ በዘመኑ ጳጳስ ለነበረው ለአትናቴዎስ ጉዳዩን በማቅረቡ አትናቲዎስም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለኢትዮጵያ በመስበኩ በእጅጉ ደስ ብሎት ቋንቋቸውንና ባህላቸውን የሚያውቅ ሌ ላ አይገኝም በማለት ፍሬምናጦስን «ኤጲስ ቆጶስ ዘአክሱም ወዘኩላ ኢትዮጵያ» ብሎ በቅብዓትና በአንብሮተእድ/እጅ በመጫን/ ተሾሞ ተ ላከ።

ፍሬምናጦስ ጵጵስናውን ተቀብሎ ከተመለሰ በኋላ በኢትዮጵያ ወንጌልን አስፋፍቶ ሰበከ ። በዚህ አኳኋን የተጀመረው የወንጌል ስርጭት ተስፋፍቶ በ350 ዓ/ም ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ወደመሆን ደረጃ ደረሰ።[3] በ325 ዓ/ም በኒቅያ በተደረገው የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ 318 ሊቃውንት ተሰብስበው አርዮስ "ወልድ ፍጡር ነው" ያለበትን ስህተት አውግዘው ሃይማኖታቸውን "ኦርቶዶክስ" ብለውታል። "ኦርቶዶክስ" የሚለው ቃል የጽርእ ቋንቋ ሲሆን ከሁለት ጥምር ቃል የተዋቀረ ሲሆን ይህም "ኦርቶስ" ርትዕ ት ቀጥ ያለ ቀጥተኛ ማለት ነው ።" ዶክስ " ደግሞ "ዶክ" ካለው ግስ የወጣ ሲሆን ፍቺ ማሰብ መገመት መተርጎም ማመን ማለት ነው"[4] እንዲሁም ተዋህዶ የሚለው ስያሜ የተገኘው በ431 ዓ.ም በጉባኤ ኤፌሶን "ቃል ስጋ ሆነ እና ቃል በእኛ አደረ" በሚል ክርክር በክርስቶስ ባህሪያት ተሟግተውና ተወጋግዘው ከተለዩ በኋላ "ተዋህዶ" የሚለውን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወግና ተቀበለችው ፡ ስያሜዋና መለያዋም አደረገችው ። ነገር ግን በወቅቱ በነበረው ፖለቲካዊ አንድምታ ካልሆነ በስተቀር "ቃል ስጋ ሆነ" ና "አደረ" ልዩነትና መነጣጠል የሌለው መሆኑን በአንድ ሐረግ መጽሐፍ ቅዱስ «ቃል ስጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ» በሚል ገልጾታል /ዮሐ 1፤14/።

---

3. የኢ.ኦ.ተ.ቤ ታሪክ አባ ጎርጎሪዮስ /ሊቀጳጳስ ገጽ 21
4. የኢ.ኦ.ተ.ቤ ታሪክ አባ ጎርጎሪዮስ /ሊቀጳጳስ ገጽ 24

ከዚህ በኋላ በ480 ዓ.ም[5] በሃገራቸው በደረሰባቸው ፖለቲካዊ ስደትና ብዙም ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ዘጠኝ መነኮሳት ማለትም አባሊሌፍ፣ አባ አረጋዊ፣ አባ አፍጼ፣ አባ ሊቃኖስ፣ አባ ገሪማ፣ አባ ጉባ፣ አባ ይምአታ፣ አባ ጳንጠሌዎን ፣ አባ ጽሕማ የተባሉት በወቅቱ የነበረውን የሀገራችንን ብሔራዊ የግእዝ ቋንቋን ተምረው አያሌ መጽሐፍትን ከሱርስትና ከጽርእ ቋንቋ በመተርጎማቸው ሲመሰገኑ በአንጻሩ ደግሞ ከወንጌል ውጭ የሆነውን ገለልተኛ መንፈስን ከአረማውያን ይዘውት የመጡትን የምነና አስተምህሮን በማስፋፋትና ገዳማትን በመቆርቆር እንዲሁም ሌሎች ተቃራኒ አስተምህሮችንም ጭምር በጤናማው ወንጌል ላይ በመበረዝም አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

እንግዲህ ከዚህ በኋላ በሃገሪቱ የአህመድ ግራኝ ወረራ፣ የእስልምና አስተ ምህሮ መስፋፋት፣ የዮዲት /ጉዲት/ ቤተክርስቲያን ማቃጠል፣ ቤተመንግስት በቤተክህነት ላይ ሰፊ ስልጣን ማግኘትና ጣልቃ ገብነት፣ የኢጣሊያ ወ ረራ፣ ተዋህዶ ጸጋ ካራና ቅባት የሚል የውስጥ ለውስጥ አስተምህሯዊ ግጭት፣ ከ13ኛው እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን የከረረ ጦርነት መፈጠር፣ የተቃጠሉትን መጻህፍት ለመተካት ሲባልና በየዱር በየገደሉ ቆዳ ፈቅፍቀው ብራና በማዘጋጀት ገደብ የለሽ ሐይማኖታዊ መጻህፍቶች ግለሰቦችና ቡድኖች በማዘጋጀት ጣልቃ ማስገባታቸው፣ የካኖንም አለመዘጋት እንዲሁም የደርግ መንግስት ቤተክርስቲያንን መዝጋት ... ወዘተ አሁን ላለችበት መንፈሳዊ መሸቃቀጥ አዎንታዊ ተጽእኖ ፈጥሮባታል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ ከምስረታዋ ጠቅት ጀምሮ እስከ ረኝርም ዘመናት የቆየውን ንጹሁን አስተምህሮዋና አምልኮዋ ምን እንደነበረና እንደሆነ በማሳየት፣ ምእመናን የተሸቃቀጠውን የእግዚአብሔ ርን ቃል በመለየት እንክርዳዱንም በመጣል የአባቶችን የጥንት ሃይማኖት

---

5.የኢ.ኦ.ተ.ቤ ታሪክ አባ ጎርጎሪዮስ / ሊቀጳጳስ / ገጽ 23-24

መከተል ያመቸው ዘንድ እንዲሁም በፕሮቴስታንቱና በሌሎች ዘንድ የቤተክርስቲያኗን ክብር በመናቅ አረማዊት አድርጎ የመቁጠር አመለካከት እንዲለወጥና ቤተክርስቲያኗ ጤናማ አስተምህሮም እንደሞላት በማሳየት ያለውን ክፍተት ማጥበብ እንዲቻል ይህ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል ::

በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቤተክርስቲያኗን የጥንት ሁኔታ /በመጀመሪያዎቹ ዘመናት/ የነበሩትንና አሁን ያሉትን መሠረታዊ የአስተምህሮ /ዶክትሪኒካል/ አቋሞች የሆኑትን በማሳየት እንደ ቤተክርስቲያን ሊያስቆጥራት የሚችሉትን አስተምህሮና እውነት እንደተጠበቀ እንዲኖር በማድረግ የተጋደሉትን የአበው እምነትንና አቋምን ያነሳል::

በሚያነሳቸውም ርዕስ ነገሮች ላይ ዋና ዋና ሃሳቦችን ከመግለጽ በስተቀር ሠፊ ማብራሪያ አልተሠጠም:: ማብራሪያ የሚፈልግም ከግርጌ በተገለጹ የመጽሐፍት ጥቅሶች መሠረት ሄዶ ማንበብና ማረጋገጥ እንዲችል ተቀምጦለታል::

በመጨረሻም ለአንባቢ የምናሳስበው ነገር የተጠቀሱ ትውፊታዊ መጻህፍቶች ሁሉ በሁለንተናቸው ፍጹማንና ስህተት የሌለባቸው ናቸው ማለት ሳይሆን ከስንዴ እንክርዳድ ባለመጥፋቱ የተገኘባቸው የጥንቱን መልካም አስተምህሮ የሚያንጸባርቁ የንባብ ክፍሎች የተለቀመባቸው እንደሆኑ ለመግለጽ ነው:: ለዚህም ደግሞ ረጅም ዘመንና የቅብብሎሽ መንገዱ አሊያም ከጊዜ በኋላ ሊቃውንት ነን በማለት የተነሱ ክፍዎች እንደበረዟቸው መረዳቱ ሊናቅ ስለማይገባው ነው::

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ !

የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን !

## 2. ሐይማኖት

ሐይማኖት የሚለው ቃል ሐይመነ ከሚል ግስ የወጣ ሲሆን ይህም አመነ ማለት ነው ሐይመነ - አመነ፣ ሐይማኖት እምነት ማለት ነው፡፡ ሃይማኖት በአሁኑ አነጋገር የነገረ መለኮትን ትምህርት፣ የአምልኮትን ሥርዓት፣ ከእምነትም የተነሣ የሰውን አካሄድ ያጠቃልላል፡፡ የሃይማኖት መሠረት የሰው ምርምር ሳይሆን የእግዚአብሔር የራሱ በተፈጥሮና በመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ነው፡፡ ለዚህም መገለጥ ሰው የሚሰጠው ተገቢ የሆነ የአፀፋ ምላሽ ማመንና መታዘዝ ነው::[6] /2ጢሞ 4፡7፣ ይሁዳ 3፣ 20፣ 1ኛቆሮ 2፡11-16/

እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» እግዚአብሔርን «ያለ እምነት ደስ ማሰኘት አይቻልም፣ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ /ወደ ፈጣሪው የሚመጣ ሰው/ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና» /ዕብ 11፡1 እና 6/[7]

የክርስቲያን ሕልውና መሠረተ ትምህርቱም መነሻው የእግዚአብሔርን ሕልውና ማወቅና በእርሱም ማመን ነው ማለት እግዚአብሔር እንዳለ ማመን ፣ መግቦቱንና ሐልዎቱን ማወቅና ባንድ እግዚአብሔርም ማመን ነው፡፡ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ እርሱ ነው የሚታየውን የማይታየውንም ሁሉ የፈጠረ እርሱ ብቻ ነው:: በእግዚአብሔር ማመን ለሰው ልጅ ሁሉ የቀደመ፣ አንድም ዋናው አስፈላጊ ተግባሩ ነው፡፡ ምክንያቱም የሕይወቱ ዘመን ሁሉ እርሱን የተደገፈና ከእርሱም ጋር የተያያዘ ነውና፡፡ የሰው ልጅ ከየት

---

6. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 7ኛ እትም 1996ዓ.ም ገጽ ፡11

7.ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት ከሊቀጉባኤ አባ አበራ በቀለ 1996ዓ.ም ገጽ 19

እንደመጣና ወዴት እንደሚሔድ ለምንስ እንደመጣና እንዴትስ፣ እስከመቼስ ለመኖር እንደሚችል የሚመራው ይህ አይነት እምነት ብቻ ነው:: ሁሉን ያስገኘ እግዚአብሔር ፍጹምና በዓለም ምሉዕ ሲሆን የማይመረመር ረቂቅ፣ የማይደረስበትም ምጡቅ ቢሆንም ልንረዳው የምንችል አምላክ ነው:: ነገር ግን የሰው ልጅ እውቀት የተወሰነና የተለካ ፍጹምነትም የሌለው ስለሆነ እንደ እግዚአብሔርነቱ ዐውቆ ሊያመልከው እንጂ በመራቀቅ፣ በመጠበብ፣ በፍልስፍና ባህሪውን ሊመረምረውና መጠኑ ይህን ያክላል፣ መልኩም ይህን ይመስላል ብሎ ልክና መልክ ሊያወጣለት አንድም ግምት ሊሰጠው ከቶ አይችልም::[8] ኤጰፋንዮስ እንደተናገረ «ሥውረ ውእቱ ዘአይረክብዎ በሕሊና ወምጡቅ ውእቱ ዘኢይጤይቅዎ በልቡና፣ ነዋህ ውእቱ ዘኢይበጽሕዎ አንሥርት፣ ቀላይ ውእቱ ዘኢይጸብትዎ ዓሣት»[9] በህሊና እንኳን ሊያገኙት የማይችሉት ስውር፣ በአሳብ እንኳ ሊጠይቁ የማይችሉት ሙጡቅ፣ ንስሮች እንኳ ሊደርሱበት የማይችሉት ትልቅ፣ አሳዎች እንኳ ሊያዳርሱበት የማይችሉት ባህር ነው ብሏል::

ይሁን እንጅ እምነት ወደ እግዚአብሔር ያደርሳል /ዕብ 11፤6/ ለማመን አንዱ መረጃ ደግሞ ዓይን የሚያየው ሥነ ፍጥረታዊ አስ ረጂ በመሆኑ እግዚአብሔር በዚህም ራሱን ገልጧል::

ለዚህም «የማይታየው ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና» ብሏል ቅዱስ ጳውሎስ /ሮሜ 1፤21/ በመዝሙረ ዳዊትም «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል »ተብሎ ተጽፏል:: /መዝ 18(19)፤1 / እንዲሁም

---

8. የኢ.ኦ.ተ.ቤ እምነትና ትምህርት ከአባ መልከጸዴቅ ሊቀጳጳስ 1994ዓ.ም ገጽ 7 - 8
9. የኤጲፋንዮ ስቅዳሴ ቁጥር 6

በመጽሐፈ ኢዮብ «እንስሶችን ጠይቅ ያስተምሩህማል የሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነግሩህማል ወይም ለምድር ተናገር እርሷም ታስተምርሃለች። የባሕር ዓሣዎች ይነግሩህማል የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ፣ ከእነዚህ ሁሉ የማያውቅ ማን ነው?» ይላል ።
/ኢዮ 12፤7-9/

ሌላው ሰው ራሱ ማሰቡ፣ መናገሩ፣ በሁሉ ተፈጥሮ ላይ የመግዛት የመንዳት፣ ሥልጣኑ ስነምግባሩ በልቡ ውስጥ የተጻፈውን ተፈጥሯዊ ህግ ሁሉ ሠራዒ እንዳለው እንጂ በአጋጣሚ እንዳልመጣ ያስረዳል። እርሱ /ሰው/ ሳያመለክት ወደዚህ ምድር ምርጫም ሳይኖረው በአንድ ስፍራ ይወለዳል፣ ያድጋል ያረጃል ሳይፈልገውም እስትንፋሱ ከእርሱ ወጥታ ይሞታል። ይህ ታዲያ በአንድ ጌታ እጅ ህይወቱ ሁሉ እንዳለች ያስረዳዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም ከእናንተ ከባለቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደተናገሩ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖራለን» /ሐዋ 17፤26-28/ ብሎ በብሩህ ሁኔታ ገልጾታል።

ከሊቃውንተ ቤተክርስቲያን መካከል አንዳንዶቹ በዓይን የሚታዩትን አማልክት በእጅ የሚዳሰሱትን ጣዖታትን ሌሎችንም አምልኮ ባእድን በመቃወም ስለማይታየው እውነተኛ አምላክ በሥነ ፍጥረት እንደሚታወቅ በልዩ ልዩ ምሳሌዎችና ማስረጃዎች እያስ ረዱና እየተከራከሩ አሕዛብን ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር መልሰዋል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በነፍስና በመርከብ ነጂ መስሎ የተናገረውን ብንጠቅስ፤- «ነፍስ በሰው ውስጥ እንደማትታይ ግን በሰውነት እንቅስቃሴ እንደምትታወቅ

እግዚአብሔርም በሥጋዊ ዓይን አይታይም ግን በፈቃዱና በሥራው ይገለጣል፡ ይታወቃልም። በባሕር ላይ ተንሳፍፋ ወደ ፊት የምትጓዝ መርከብን የሚመለከት ሰው በውስጧ የሚመራት ነጂ /ሊቀ ሐመር/ እንዳለ ማወቅ አለበት እንደዚሁም በምንም በዓይነ ሥጋ ባይታይ ሁሉንም የሚመራ እግዚአብሔር እንደሆነ ማስተዋል ይገባዋል» / የዮሐንስ አፈወርቅ ትርጓሜ /[10]

በአጠቃላይ የሥነ ፍጥረት ውበትና መልካምነት የሰው ነፍስ ባህርያት አስደናቂነት ሌሎችም ዓላማና ትርጉም ያላቸው የተፈጥሮ ስርዓቶችና ክሥተቶች ሁሉ የመለኮታዊ ጥበብ አሠራርን ያመለክታሉ። ከጥንት ጀምሮ የሰው ልጅ በሕገ ልቡና - በምርምር ፈጣሪውን መፈለጉና የአምልኮት ዝንባሌም እንዳለው የምናውቀው ከራሱ ከሰው ልጅ ታሪክ ነው። «አሕዛብ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፣ እነርሱም ኅሊናቸው ሊመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሊካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተ ጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉና» /ሮሜ 2፤14-15/። በመላው ዓለም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የነበሩት የልዩ ልዩ ሕዝቦች ሁሉ መንገዱና ሥርዓቱ ይለያይ እንጂ ሁሉም በአምልኮ ቅርጽና ይዘት ነበራቸው። እያንዳንዱ የሃይማኖት ዓይነት ፍልስፍናን ማለት የምርምርን ስልት የተከተለ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ዓይነቱ የበዛ ባህላዊ ባእድ አምልኮና እንዲሁም መናፍስተን፣ጥንቆላንና ልዩልዩ ኅጺእምነቶችን የቀላቀለ አሠራር የሚታይባቸው ነበር። እነዚህ ሁሉ የሃይማኖት ዓይነቶች በታሪክ እንደምናውቃቸው ያህል ባይሆኑም ባህላቸውንና መልካቸውን እየለዋወጡም ሆነ ሳይለዋውጡ ዛሬም በየሀገሩ ይገኛሉ። ትክክልም ይሁን ወይም በማናቸውም መልኩ የሰው ልጅ የሕይወትን ትርጉም አውቆ ለመኖር ፈጣሪውን ፈልጎ ለማግኘት የሚያስብ ሃይማኖታዊ

---

10. ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት በሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ ገጽ29

ፍጡር እንደሆነ ታሪክ ይመሰክራል።[11]

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ ገልጧል «በሥጋ የተገለጠ በመንፈስ የጸደቀ ለመላእክት የታየ፣ በአህዛብ የተሰበከ፣ በዓለም የታመነ፣ በክብር ያረገ ያለጥርጥር ታላቅ ነው /1ጢሞ 3፤16/ «ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል ... ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ አሐዱ ዋሕድ ለአቡሁ ዘምሉእ ጸጋ ወጽድቀ ወሞገሰ - በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ... ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትም ተሞልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን /ዮሐ 1፤1 እና ቁ.14/ የእግዚአብሔር ቃል በሥጋ መገለጡና የማዳን ሥራውም መነጣጠል የለባቸውም። የመዳን ሥራ ማለት ከሰው ልጆች ላይ ኃጢአትንና ሞትን አስወግዶ በምትኩ ጽድቅንና የዘላለም ሕይወትን መስጠት ማለት ነው። የክርስቶስም በሥጋ መገለጽ ምክንያትም ይህንኑ ተልዕኮ ለመፈጸም ነበር። ይህንንም ለማድረግ የሰዎችን ኃጢአትና ሞት በሰውነቱ ተሸከመ በእኛ ፈንታ ሕማምና ሞትን ተቀበለ እንደዚህም በማድረጉም ከኃጢአትና ከሞት አዳነን። እንግዲህ እግዚአብሔር የገለጸው የማዳን ሥራ በእንደዚህ ዓይነትና ሁናቴ የተፈጸመ ነው።አንድ መጽሐፍ እንዲህ ይላል « ...እኛስ ወልደ እግዚአብሔር ሰውን ለመዳን ከሰማየ ሰማያት እንደወረደ ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደተወለደ እናምናለን የጠፋውን በግ ሊፈልግ እንደመጣ ፈልጎም እንዳገኘው እንዳዳነውም ለጠፉት ወገኖች ሁሉ ቤዛ እንደሆነላቸውም እናምናለን እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ፣ እንደ ዕብራይስጡ ቃል የስሙ ቀጥታ ትርጉም እግዚአብሔር ያድናል ማለት ነው። / ማቴ 1፤21፣

---

11. ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት -በሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ ገጽ 33

ሉቃ 2፥11/ መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና /ሐዋ 4፥12/ እንግዲህ በእግዚአብሔር አዳኝነት ማመን በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን የክርስትና ሃይማኖታችን የተስፋችንና የፍቅራችን የደኅንነታችንና የደስታችን መሠረት እንደሆነ በቃለ ወንጌል የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ ነው ስለ እኛ ስለሰዎች ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ ተብሎ በአንቀጸ ሃይማኖት የተናገረ።»[12]

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሐተታ ሁሉ ክርስቶስን ለማይቀበሉና ከክርስትና ውጭ ለሆኑት ሕዝቦች ብቻ ነው እንጂ ለእኛ ለክርስቲያኖችስ መድኃኒታችን መመሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ በዚህ ዓለም በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙ ማስረጃዎችን አስቀድሞ ስለሰጠን ስለእግዚአብሔር ፍጹም ዕውቀት አለን ምንም ጥርጥር የለብንም፤ እርሱም በትምህርቱ «አቡነ ፈነወኒ ወአነሂ ተፈኖኩ» «ዘርእየ ኪያየ ርዕዩ ለአቡየ» /አባቴ ላከኝ እኔም ተላኩ እኔን ያየ አባቴ ደግሞ አየ/ እያለ እግዚአብሔር እርሱም ከአምላክ የተገኘ አምላክ እንደሆነ በማስረዳት በሥራው ድውይ እየፈወሰ ሙት እያስነሣ ለምጽ እያነፃ ልዩ ልዩ ተአምራትንም እያደረገ በእግዚአብሔር ሐልዎት ማመን እውነተኛ ሃይማኖት እንደ ሆነ እግዚአብሔርም አንዳለና ፈጣሪም እርሱ ብቻ እንደ ሆነ ነግሮናል፤ አስተምሮናል፤ ትምህርቱንም በእርግጥ አምነን ተቀብለነዋል። እኛ ክርስቲያኖች ማዕበልና ሞገድ የሚያማታውን ይኸን ዓለም ለመሻር የምንችለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመን እንደሆነና የርሱንም ትምህርት የተከተልን እንደሆነ ነው። በእርሱም እንድናምን እርሱንም እንድንሰማና እንድንከተል እግዚአብሔር አብ አዞናል «ከደመናውም ውስጥ በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይኸ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ» / ማቴ 17፥5 / ።

---

12. ትምህርተ ሃይማኖት ክርስቲያናዊ ሕይወት በሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ ገጽ 48-44

ስለዚህ እርሱ እውነተኛ መምህር እርሱ እውነተኛ ድልድይና መሸጋገሪያ መሆኑን ማመንና ማረጋገጥ ግዴታችን ነው እውነተኛ መንገድ፣ እውነተኛ ፈጣሪ፣ እውነተኛ አዳኝ እርሱ ብቻ እንደሆነ መመስከር አለብን፣ እርሱ «እኔ ትንሣኤም ሕይወትም ነኝ» ብሎ የመሰከረውን ማመንና መቀበል አለብን::»[13]

እንግዲህ ስንጠቀልለው ቤተክርስቲያኗ ሐይማኖት ወይም እምነት የምትለው / ስትለው የነበረው / መንፈሳዊ ድርጅትን ሳይሆን እንድ ሠው በአንድ አምላክ ብሎም ለዚህ ዓለም ፈጣሪ ሠራኢ መጋቢ እንደሆነ ማመኑን እና በዚህም ሳይወሰን ስለሠው ልጆች ከሰማየ ሰማያት ወረዶ የተወለደውን፣ የተሠቀለውን የሞተውን፣ የተነሳውን በአብ ቀኝ ያለውን ደግሞም ተመልሶ የሚመጣውን ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብሎ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ ክብር መስጠቱ ብቻ ነው ብላ ትገልጻለች::ስለዚህ በአጭሩ የክርስትና እምነት ማለት ሃይማኖተ ወንጌልማለት ነው ::

ስለዚህ ከእምነት በፊት ከእግዚአብሔር ስለተገለጠው ነገር ማወቅና ቃሉን መስማትን እናስቀድማለን ቀጥሎ የሰውን እምነት በተ መለከተ ማለት የአማኙንና የእምነቱን ትክክለኛ ሁኔታ ከተገነዘብን በኋላ በክርስቶስ የተገኘውን የእምነት ዓይነት አጥብቀን መያዝና ለተ ገለጠው ሃይማኖት ለእውነተኛው ቃል ለወንጌል እምነት በቁርጥ ኅሊና በፍጹም ተስፋ ፍቅር እስከመጨረሻው መታዘዝ ይኖርብናል / ሮሜ 1:3-5፣ ገላ 5፣ 6፣ ኤፌ 1:43/:: ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት በወንጌል ለተገለጠው እውነተኛ እምነት ራሳችንን ብናስገዛ በእምነት ከሚገኘው ጸጋና በረከት ተካፋዮች እንሆናለን:: ስለዚህ ከሁሉ በፊት ለእምነት መታዘዝን እናስቀድም በሥጋ

---

13. የኢ.አ.ተ.ቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት ከአባመልከጼዴቅ ሊቀጳጳስ ገጽ 21

የተገለጠውን ክርስቶስን በማመን ከአለውም ከሚመጣውም ክፉ ነገር ሁሉ እንድናለን ፣ ጽድቅንም እናገኛለን::[14] ገለጠውን ክርስቶስን በማመን ከአለውም ከሚመጣውም ክፉ ነገር ሁሉ እንድናለን ፣ ጽድቅንም እናገኛለን::[14]

## 3. ዶግማ /ዶክትሪን/ አዕማደ ምሥጢራት

ዶግማ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን መሠረተ እምነት ማለት ነው:: የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት መሠረት እንደሆኑ የምታምነውና የምታስተምረው አምስቱ አዕማደ ምስጢራትን ነው:: እነዚህም የጥንት /የቀደሙ/ አበው ጽፈው ያለፉት አስተምህሮ የሃይማኖት መሰረት የሚባሉት አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት :-

1. ምሥጢረ ሥላሴ
2. ምሥጢረ ሥጋዌ
3. ምሥጢረ ጥምቀት
4. ምሥጢረ ቁርባን
5 .ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው::

እነዚህም የቀደሙት አበው ቤተክርስቲያኗን ሲመሠርቱ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው ትርጓሜያቸው ሳያዛንፍ ለመ ረዳት በሚያስችል ቋንቋና ምሳሌ ዘርዝረው አስተምረዋል:ጽፈዋል አስተላልፈዋልም:: ምሥጢር መባላቸውም የተደበቀ የተሠወረ ማለት ሳይሆን የአስተምህሮታቸው ጥልቀት የሰው አእምሮ ማነስን በእጅጉ የሚያሳዩ በመሆናቸው ምክንያት ነው::

አዕማድ ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን የአምድ ብዜት ቃል ነው አዕ ማድ /ምሰሶዎች/ ዋና ቋሚዎች ማለት ሲሆን የእምነት ዋናማዕዘን / ምሰሶን/ ለማመልከት የተገለጸ ቃል ነው::

---

14. ትምህርተ ሃይማኖት ክርስቲያናዊ ሕይወት ሊቀጉባኤ አባ አበራ በቀለ ገጽ 20፣ 53 : 57

## ምሥጢረ ሥላሴ

ቤተክርስቲያኗ ይህን ምሥጢረ ሥላሴ በአጭሩ ለማስተማር በጥያቄና መልስ መልኩ በደረጃ አስቀምጠዋለች:: ይሄውም :-

1. ማን ፈጠረህ? ሥላሴ::
2. ሥላሴ ስንት ናቸው? አንድም ሦስትም ናቸው::
3. ሦስትነታቸው እንደምንድን ነው? በስም፣ በአካል፣ በግብር::

4.በስም ሦስትነታቸው እንደምንድን ነው?አብ፣ ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ

5.በአካል ሦስትነታቸው እንደምንድን ነው?

- ለአብ ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ ፍጹም አካል አለው::
- ለወልድም ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ ፍጹም አካል አለው
- ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ ፍጹም አካል አለው[15]

6. በግብር ሦስትነታቸው እንደምንድን ነው?

- አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣መንፈስ ቅዱስ ሰራጺ ነው::ይሄውም :-
- አብ ይወልዳል ያሰርጻል እንጂ አይወለድም አይሰርጽም
- ወልድም ይወለዳል እንጂ አይወልድም አይሰርጽም አያሰርጽም
- መንፈስ ቅዱስም ይሰርጻል እንጂ አይወልድም አያሰርጽም

7. አንድነታቸው እንደምንድን ነው? በባህሪይ፣ በመለኮት፣ በመፍጠር፣በመግዛት፣ በስልጣን፣ በአገዛዝ ... ይህን በመሳሰሉት ሁሉ አንድ ናቸው::

ይህ ከላይ ባጭሩ የተቀመጠው የሥላሴ አስተምህሮ ጠቅለል ተ ደርጎ የተቀመጠ ሲሆን እያንዳንዷ ቃል ሰፊ ትንታኔን የያዘና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የጠገበ መሆኑን ከዚህ በታች ዛተታውን መረዳት በቂ ነው::

---

15. ሊቀ ጳጳስ አትናቴዎስ ዘሃይማኖት አበው

1. እግዚአብሔር-ስላሴ የሆነ ፈጣሪ ነው

እግዚአብሔር ልዑል ክቡር በመሆኑ ስለእርሱ ቅኔና ግጥም እንዲሁም መዝሙር ሊገልጠው የማይችል ነው። በብዙ ሠባኪዎች ከተነገረው ክብር የበለጠ ሁሉም አድንቆና አመስግኖ ተናግሮና ዘምሮ ሊተረጉመው ከሚችለው በላይ የሆነ በድንቅ ቃል ምሳሌ የሌለው መልዕልተ ኩሉ የሆነ አማላኩ ነው :: /ኢሳ 40፥18-26፣ ኢሳ 66፥1-2፣ ኤር 23: 24/ ከመለኮታዊት ችሎታው የተነሣ ሁሉን ማድረግ የሚችል ተዋርዶ የሌለበት መለኮታዊ ልዑል፣ ከክህሎቱ በላይ አንዳች ነገር የሌለ፣ ያለድካም መሥራት፣ ያለሕልፈት መኖር፣ ያለመሞት ሕይወት፣ ያለጊዜ መኖር፣ ያለመወሰን መላት፣ ያለመታከት መምራት፣ ያለለውጥ መንግስት፣ ያለመሰልቸት መያዝ፣ ያለማዘንበል መመልከት የሚቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነው: አዎ ብቻ ነው። / ዘፍ 17፥1፣ ዘፍ 18፥14፣ ኢዮብ 6፥14፣ ኢዮብ 26፥11፣ ኢዮብ 42፥1-2፣ ኤር 32፥17፣ መዝ 138፥1-10፣ ዳን 4፥35፣ ራእ 4፥1-11/ ደግሞም እርሱ የማይታይ የማይመረመር ረቂቅ /1ጢሞ 1፥17፣ ኢዮብ 5፥9-11፣ ኢሳ 40፥21-26፣ ሮሜ 11፥33/ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው አልፋ ወኦሜጋ ዘላለማዊ አምላክ ለዘመኑ ጥንት ለመንግሥቱ ፍጻሜ የሌለው /መዝ 89(90):2፣ ኢሳ 43:1-13፣ ኢሳ 44፥6፣ ራዕ 1፥5፣ ራዕ 1፥8/ ለምህረቱ ማለቅ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ርኅሩህ አባትና አምላክ ነው /መዝ 135 (136)፥ 1-26፣ ዘኁ 14፥17/ እርሱ :

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1፥1 «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ይላል በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር የሚለው ቃል በእብራይስጥ «ኤሎሂም» የሚል ነው ኤሎሂም ብዙ ቁጥር ሲሆን ግሡ ግን ነጠላ ነው::[16] ይህም በፍጥረት ሥራ ውስጥ

---

16. አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ የግርጌ ማስታወሻ 1993ዓ.ም የታተመ

አብ እንደፈጠረ /ሐዋ 4፤24/ ወልድ እንደ ፈጠረም /ዮሐ 1፤1-10/ መንፈስ ቅዱስም እንደ ፈጠረ /ዘፍ 1፤2፣ መዝ 3፤6፣ ኢዮብ 33፤4/ በግልጽ ያሳያል።

ለዚህ ነው ፈጣሪ ስላሴ ነው የሚባለው "ምንም በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድ የሆነውን አምላክ በአካል በስም በግብር 3 ብንልም ሦስት አማልክት ከቶ አንልም አንድ አምላክ ብቻ እንጂ 3ቱም አካላት በባሕርይ በመለኮት አንድ ናቸውና። ይኸንም በአዋጅ መልክ "ስማ እሥራኤል ሆይ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ እግዚአብሔር ነው ሲል ነብዩ ሙሴ ተናግሯል ዘዳ 6፤4[17] ሃይማኖታቸው የቀና ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንትም ስለ እግዚአብሔር አንድነት በዋናው የሃይማኖት አንቀጽ በጸሎተ ሃይማኖት "ነአምን በ1ዱ አምላክ ... " ሲሉ ተናግረዋል /ጸሎተ ሃይማኖት/ እስቲ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ማንነት ወደ ሚነግረን በአጭሩ ጠለቅ ብለን እንግባ፤-

## 2. ስላሴ አንድም ሦስትም

ሥላሴ ማለት ሦስት፣ ሦስትነት ማለት ሲሆን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል አብ ፣ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ( ስላሴ ) ብለውታል[18] መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚሰጠን መገለጥ በእጅጉ የጠለቀ ነው፤፤ የእግዚአብሔርን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ከተፈጥሮ ልንረዳ በማንችልበት መንገድ ይገልጻል። የዚህ መገለጥ እጅግ አስደናቂው ክፍል እግዚአብሔር እራሱን አንድ እንደ ሆነ / ዘዳ 6፤4/ እና ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ይገልጻል/ኢሳ 45፤5/

---

17. የኢ.ኦ.ተ.ቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት ከአባ መልከ ጸዴቅ ሊቀጳጳስ ገጽ 22
18. መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ሊቀመዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ 1969 ዓ.ም ገጽ 1

እንዲሁም ደግሞ ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ እንዳልሆነና ዳሩ ግን ሦስት የተለያዩ አካላት ፤- እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ይገልጻል ። ለምሳሌ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ /ስሞች ሳይሆን/ ስም እንዲጠመቁ አዟአል።/ ማቴ.28፤19/ በዚህ ስፍራ አንድ ስምና ሦስት አካላት ተጠቅሰዋል። በ1ቆሮ8፤4 "ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን ይላል። በያዕቆብ 2፤19ም አጋንንት እንኳ አንድ አምላክ እንዳለ እደሚያውቁ ይናገራል እግዚአብሔር አንድ ህላዌና ሦስት አካላት እንዴት ሊኖረው ይችላል? የሥላሴ እውነት ለመቀበል ትልቁ ችግር ለእኛ ለሰዎች የሚፈጥረው አመለካከት አንድ ህላዌ ብቻ ካለ ሊኖር የሚችለው አንድ አካል ብቻ ነው።ይህም የሆነው እኛ ሰብአዊ ሰዎች ስለሆንንና የተፈጠርነውም በዚሁ መንገድ ስለሆነ ነው።እያንዳንዳችን አንድ ህላዌና አንድ አካል ነን እግዚአብሔር ግን እንዲህ አይደለም እርሱ አንድ ህላዌ ሲኖረው ሦስት አካላት እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል ይሁንና አንዲት ሰብአዊ አእምሮ እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ልትረዳው አትችልም ለዚህ ነው ሚስጥር የተባለው።

ሦስቱ የእግዚአብሔር አካላት እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩ ሲሆን እርስ በርሳቸውም የተዛመዱ ናቸው። ይህም በዘፍጥረት 1፤6፣ 3፤22 እና በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊታይ ይችላል፤፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት የተገኙ ሲሆን እርስ በርሳቸው ተዛምደው እናያለን። አብ ድምጹን በማሰማት «የምወድህ ልጄ አንተ ነህ በአንተ ደስ ይለኛል» አለ። በዚሁ ቅጽበት መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በክርስቶስ ላይ ወረደ /ማር 1፤9-11/።

እግዚአብሔር ራሱን «እኛ» በሚል የብዜት ቃልና «እኔ» በሚል አሃዷዊ ቃል ራሱን ይጠራል ለምሳሌ :-

"ሠውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" /ዘፍ 1፤26/
"አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" /ዘፍ 3፤22/
"ኑ እንውረድ ... ቋንቋቸውን ... እንደባልቀው" /ዘፍ 11፤5-7/
"የጌታንም ድምፅ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ" /ኢሳ 6፤8/ የሚሉትና የመሳሰሉት ክፍሎች ብዛትና ከአንድ በላይ መሆኑን ሲገልጽልን

"ማቴ 3፤13-17፣ 17፤1-8፣ ማቴ 19፤20፣ ሐዋ 2፤1-4፣ ዮሐ 1፤1-2፣ ዮሐ 14፤16-17 እና 26፣ 16፤7-11 እና 13-15፣ 2ዮሐ 9/
እነዚህና በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ደግሞ ስለእግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስነት ያብራሩልናል ::

መጽሐፍ ቅዱስ አብ እግዚአብሔር እንደሆነ ያስተምራል: /ሮሜ 1፤7/ ወልድ እግዚአብሔር እደሆነ ያስተምራል /ዕብ 1፤፤8/:: መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር እንደሆነ ያስተምራል /ሐዋ 5፤3-4/፤፤ ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ አንድ አምላክ ብቻ እንዳለና እርሱንም የሚመስል እንደሌለ በግልጽ ያስቀምጣል /ዘዳ 4፤35/:: በኢሳያስ 44:6-7 እግዚአብሔር "እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ ከእኔም ሌላ አምላክ የለም" ይላል:: በመሆኑና ስለእግዚአብሔር ሊኖረን የሚችለው ብቸኛና ትክክለኛ እውቀት የሚገኘው እርሱ ስለራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከገለጸው ነው::

ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን አንድነት ለመግለጽ የተጠቀመበትን የዕብራይስጥ ቃል በጥንቃቂ ማጥናቱ መረዳታችንን ያሳድገዋል:: ይህ ቃል «ኢቻድ» የሚል ሲሆን በዘዳግም 6፤4 ተጠቅሶ ይገኛል ::

"እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ /ኢቻድ/ እግዚአብሔር ነው"

ይህ ቃል እግዚአብሔር ለጋብቻ ያቀደውን አይነት ጥምረታዊ አንድነት ይገልጻል:: ይህም ሁለቱ አንድ ይሆናሉ የሚለው ሁለቱ ኢቻድ ይሆናሉ በሚል ነው / ዘፍ 2፤24/:: የባቢሎን ግንብ ይሠሩ የነበሩትን ሰዎች «አንድ» መሆን ለመግለጽም አገልግሏል /ዘፍ 11፤6/ በዕብራይስጥ ቋንቋ ፍጹማዊ አንድነትን የሚያገለግል ሌላ «ያቼድ» የሚባል ቃል አለ :: ይህ ቃል ግን እግዚአብሔርን ለመግለጽ አላገለገለም :: በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር የሚገልጽልንን ሁሉ በእምነት መቀበል አለብን በሦስት አካላት የተገለጸ አንድ አምላክ ብቻ አለ:: እርሱንም የሚመስል ማንም የለም /ኢሳ 44፤6-7/[19] ይህንንም የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ በመንተራስ እግዚአብሔር ስላሴ /ሦስት የሆነ አንድ፣ አንድ የሆነ ሦስት/ በማለት "ስሉስ-ቅዱስ" ብለው አበው በአጭር ቃል አስቀመጡት:: "እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ውይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ?" /ኢሳ 40፤18/

## በዚህ አስተምህሮ ላይ የጥንት አባቶች ያላቸው እምነታዊ አቋም

1. እንዘ አሐዱ ሰለስቱ ወእንዘ ሰለስቱ አሐዱ-አንድ ሲሆኑ ሶስት ሶስት ሲሆኑ አንድ (ሃይማኖተአበው)
2. አምላክ ውእቱ አብ፣ ወአምላክ ውእቱ ወልድ፣ ወአምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ወኢይትበሀሉ ሰለስተ አማልክተ:: አላ አሃዱ አምላክ:: አብ አምላክ ነው ወልድም አምላክ ነው መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው:: ግን ሦስት አማልክት አይባሉም አንድ አምላክ እንጂ/ አትናቴዎስ ሃይማኖተ አበው ምዕ 25 ቁ 4/

---

19. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካውያን ዕይታ ገጽ 65

3. ነአምን አብ በወልድ ጠበመንፈስ ቅዱስ: ወወልድ በአብ ወበመንፈስ ቅዱስ፤ ወመንፈስ ቅዱስ በአብ ወበወልድ:: ዛቲ ሥላሴ ዕሪት እንበለ ፍልጠት ወዘእንበለ ውላጤ በ3ቱ አካል ወ1ዱ መለኮት:: አሐቲ ምልክና ወአሐቲ ሥምረት ወአሐቲ ኃይል ወአሐቲ መንግስት አሐቲ ስግደት ወአሐቲ አኰቴት:: ወአሐዱ ስብሐት ይደሉ ለሥሉስ ቅዱስ:: ኣሐቲ ምክር ወአሐቲ ሥልጣን ወአሃዱ ክብር ወአሐቲ ፅንዕ ወአሃዱ ህሊና:: ወአሃዱ ፈቃድ ለሥሉስ ቅዱስ::

*ትርጉም፡-* አብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ህልው እንደሆነ ወልድም በአብ በመንፈስ ቅዱስ ህልው እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም በአብ በወልድ ህለው እንደሆነ እናምናለን:፤ ይህች ሦስትነት ያለመለየት ያለ መለወጥ በሦስት አካላት በአንድ መለኮት የተካከለች ናት::

አንዲት አገዛዝ አንዲት ፈቃድ አንዲት ኃይል፣ አንዲት መንግስት፣አንዲት ስግደት፣አንዲት ምስጋና፣ አንዲት ክብር፣አንዲት ጽንዕ አንድ አኗኗር አንድ ፈቃድ ለሥሉስ ቅዱስ ነው::

/ ዘአግናጥዮስ ሃይማኖተ አበው ምዕ 11፤5-6/

## 3. የስላሴ ሦስትነት በስም በአካል በግብር

**3.1 የስም ሦስትነት፤-** ስም ከሶስት አቅጣጫ ሊገኝ ይችላል:: ነገሩን ግልጽ ለማድረግ የሰውን ስም እንደ ምሳሌ እንውሰድ:- ሰው የሚባል ስም የተፈጥሮ ስም እንጂ የሚጠራበት ወይም የሚሠራውን ኃላፊነትን የሚገልጽ የግብር ስም አይደለም:: ሁለተኛው ደግሞ የተ ጸውኦ /የመለያ መጠሪያ/ ስም ደግሞ አዳም፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ ያዕ ቆብ እንደ ሚባለው ሁሉ እንዳንዱ ሰው የተጸውኦ ስም አለው:: ሦስተኛው ገዢ፣ መጋቢ፣ ቄስ፣ ... ወዘተ የሚል ሰዎች የሥራ ስም ተሰጥቶአቸውን በግብር ስማቸው የሚጠሩበት ነው፤፤እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር የማንነቱ ስም "ያህዌ" ወይም «ያለና የሚኖር» ባሚል ብቻ ለሙሴ ገልጾአል "እግዚአብሔርም ሙሴን፤- "ያለና የሚኖር" እኔ ነኝ አለው:: ... ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ አለው::" ዘዳ 3:14/

ይህ ያለና የሚኖር የሚለው ስም ሁኔታውን የሚገልጽ እንጂ የተጸውኦ ወይም የወል ስም አይደለምና እግዚአብሔር የተጸውኦ ወይም የወል ስም የለውም። ለዚህ ነው ሰዎች በየቋንቋቸው ማንነቱን በሚገልጽ ስም ሁኔታ ሠጥተው የሚጠሩት የሚያመልኩት።

እንዲሁም እያንዳንዱ ሠው የአካል ስም እንዳለው አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ተብሎ እንዲጠራ የስላሴ አካላት ስም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ። ይህም በግልጽ በማቴ 28፤19 ላይ የስላሴ አንዱ አካል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድነት ገልጾአቸዋል።

የግብር /የሥራ/ ስም ደግሞ አብ አባት ወልድ ልጅ መንፈስ ቅዱስ ሰራፂ ነው። ይህም በራሱ ርዕስ ስር እንገልጸዋለን።

እንግዲህ ሥላሴ በስም ሦስት ናቸው።እነርሱም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ፤፤ ለወልድ ግን በተለየ አካሉ ሌሎች ስሞች አሉት። ሰው ከመሆኑ በፊት ቃል፣ ወልድ ይባላል ከሰውም ሥጋ ከነሣ /ከለበሰ/ በኋላ አማኑኤል፣ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ መድኃኔ ዓለም ይባላል። እግዚአብሔር የሚባለው ስም አብዛኛውን ጊዜ ለአብ የተሰጠ ነው ቢባልም በበርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎችም ይኸው ስም ሁሉም የሥላሴ አካላት የሚጠሩበት ሆኖም ተጠቅሷል። እነዚህን ጥቅሶች ተመልከት /2ኛቆሮ 13፤14፣ 1ኛቆሮ 12፤4-6፣ ኤፌ 2፤20-22፣ 1ኛጴጥ 1:1-2፣ ዮሐ 14:26፣ ዮሐ 15፤26፣ ዮሐ 16:7-11፣ ሉቃ 1፤35፣ ሐዋ 7፤55-56፣ ራዕ 1፤4-5፣ ዮሐ 14፤15-17

**3.2 የአካል ሦስትነት፡-** በመጽሐፍ ቅዱስ ሦስቱ የስላሴ አካላት በርካታ ቦታ ተጠቅሰውይገኛሉ። በየፊናቸው የተጠቀሱትን ለአንባቢ በመተው በጣምራ የተጠቀሱበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻ ላል፤፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ፣ መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል ሲወርድ፣ አብም በደመና ውስጥ ሆኖ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። /ማቴ 3፤15-17/ በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔርን ... አየሁት። ሱራፌልም ... አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ...እያለ ይጮኽ ነበር ።/ኢሳ 6፤1-5/ ነብየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ሦስት ጊዜ ቅዱስ ያለው በልማድ ሳይሆን የሦስትነቱን፣ እግዚአብሔር ያለው ደግሞ የአንድነቱን አስረጂ ነው። ይህንም ክፍል በዮሐንስ ወንጌል አንዱ ቅዱስ የተባለው አካል ወልድ እንደ ነበረ ተ ጠቅሶ ተቀምጦአል /ዮሐ 12፤37-41/። እንዲሁም ይህንን ክፍል በመጥቀስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አንዱ ቅዱስ የተባለው ተናጋሪ መንፈስ ቅዱስ እንደ ነበረ ተጠቅሷል /ሐዋ 28፤25-27/።እንግዲህ ሦስት ጊዜ ሱራፌል በኃይል በመጮህ «ቅዱስ» ያለው ሦስቱን አካላት በመረዳት እንጂ በልማድ እንዳልነበረ መጽሐፍ ያስረዳል፤፤ በዚሁ በኢሳያስ መጽሐፍ ክፍልም እግዚአብሔር ራሱን «ማንስ ይሄድልናል» በማለት በብዜት ቃል ተናግሯል /ኢሳ 6፤8/ እንግዲህ ሦስቱን አካላት በተደጋጋሚ 3 ጊዜ ብቻ ሳይጎድል ሳይበዛ እግዚአብሔርን ያመልኩትና ይጠሩት ነበር። ከዚህ በታች የተ ቀመጡትን ጥቅሶች በማስተዋል ማንበብ ይረዳል።/ዘጸ 3፤6፣ ዘኁ 6፤24-26፣ መዝ (147)፤5፣ ራዕ 4፤8/ እንግዲህ ለአብ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል፣ፍጹም መልክ አለው።ለወልድም ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክዕ አለው። ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክዕ አለው። አብ ወልድም መንፈስ ቅዱስም አይደለም ወልድም አብና መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

**3.3. <u>በግብር</u> ሦስትነት፡-** የሥላሴ ግብር በምንልበት ጊዜ እያንዳንዱ አካል የሚፈጽሙትን ሦስት ልዩ ልዩ ግብራትን ብቻ የሚያመለክት ነው:: ይህም ማለት አንዱ አካል ከሌላው ጋር ያለውን የእርስ በእርስ ግንኙነትና ሁኔታ ይገልጽልናል:: አብ አባት ወልድ ልጅ መንፈስ ቅዱስ ሰራፂ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል:: እንግዲህ የአባት ግብሩ መውለድ ነው:: የልጅ ግብሩ መወለድ ነው:: የመንፈስ ቅዱስም ግብሩ መሥረፅ ነው:: መሥረፅ ማለት መገኘት መውጣት ማለት ነው:: ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሲባልም በሰውሰውኛ መንገድ እንደ ሰው መወለድ ሳይሆን በባህሪ መልክ መገኘ ትን መኖርን ያመለክታል፤፤ መጽሐፍ ቅዱስ አብ አባት ተብሏል ወላዲም አስራፂም ተብሏል /ዮሐ 8፤42፣ ኤፌ 4፤6፣ ዮሐ 15፤26/ አብ ወልድን አንድያ ልጄ ብሎ ይጠራዋል /ዮሐ 17፤5፣ ዕብ 1፤5 ዩሐ 3:16/ ወልድም አባቴ ብሎ ይጠራዋል /ዮሐ 17፣1.5፣ ዮሐ 5፤18፣ ዮሐ 5፤43፣ ዮሐ 6፤32/ አብ መንፈስ ቅዱስን«መንፈሴ» ብሎ ይጠራዋል /ሐዋ 2፤17/ ወልድም መንፈስ ቅዱስን አጽናኝ፣ የእውነት መንፈስ ... ብሎ ይጠራዋል /ዮሐ 15፤26፣ ዮሐ 16፤13/ መንፈስ ቅዱስም አብንና ወልድን ያከብራል ይወዳል/ዮሐ 16፤13-14/ ::

የሦስቱ ግብራት ከአንዱ አካል ወደ ሌላው አይተላለፍም:: ስማቸውም አይወራረስም አብ በተለየ አካሉ ለሁሉም አስገኚ ነው:: ማለት ወላዲ አሥራፂ ነው እንጂ እንደ ወልድ አይወለድም እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሰርጽም ፣ ወልድም በተለየ አካሉ ተወላዲ ነው እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሰርጽም እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅም:: መንፈስ ቅዱስም በተለየ አካሉ ሠራፂ ነው እንጂ እንደ አብ አይወልድም፣ አያሰርፅም እንደ ወልድም አይወለድም::በግብርና በስም አለመወራረሳቸውም የሥላሴ አካላት በያሉበት አንዱ አካል ወደ ሌላው አካል ሳይፋለስ ጸንቶ መኖሩን ያረጋግጥልናል::

ይህም ማለት አብ፣ወልድና መንፈስ ቅዱስን አለመሆኑ ወልድም፣አብንና መንፈስ ቅዱስን አለመሆኑን መንፈስ ቅዱስም አብንና ወልድን አለመሆኑን ያስረዳናል ማለት ነው:: ደግሞም አብ ልጁን ሠጠ፡ ወልድ ለማዳን ራሱን ሰጠ፡ መንፈስ ቅዱስም ቃሉን ሰጠ:: ይህ የሥራ/የግብር/ ሦስትነት አይደባለቅም ወልድ በለበሰው ስጋና ክህነቱ ዛሬም አስታራቂ አማላጅ ነው::/ለተጨማሪ ማብራሪ ገጽ47 ይመልከቱ/ ይህንም ስራ ይዞ በአብ ቀኝ ተቀምጦአል አብም ምልጃን እርቅን በልጁ በኩል ይቀበላል መንፈስ ቅዱስም ስለኃጢአት በመውቀስ ሠዎችን ወደ ክርስቶስ አዳኝነት ያመለክታል ያመጣል / ዮሐ 3:16፣ ሮሜ 5፤6-11፣ ሮሜ 8:34፣ ዕብ 7፤24-25፣ ራዕ 5:9/

**በዚህ አስተምህሮ ላይ የጥንት አባቶች ያላቸው እምነታዊ አቋም**

«አብሂ አብ ውእቱ ወኢኮነ ወልደ፣ ወኢኮነ መንፈስ ቅዱስ፣ ወልድሂ ወልድ ውእቱ ወኢኮነ አበ ወኢመንፈስቅዱስ፣መንፈስ ቅዱስሂ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ ወኢኮነ አበ ወኢወልደ ፣ኢይፌልስ ስመ አብ ለከዊነ ስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወስመ ወልድሂ ለከዊነ ስመ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወስመ መንፈስ ቅዱስሂ ለኮዊነ ስመ አብ ወወልድ - አብ አብ ነው እንጂ ወልድም መንፈስ ቅዱስም አይደለም:: ወልድም ወልድ ነው እንጂ አብም መንፈስ ቅዱስም አይደለም:: መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ አብም ወልድም አይደለም:: የአብ ስም ለወልድም ለመንፈስ ቅዱስም አይሆንም፣ የወልድ ስም ለአብም ለመንፈስ ቅዱስም አይሆንም፣ የመንፈስ ቅዱስም ለአብም ለወልድም አይሆንም አይፋለስም :: /አግናጥዮስ ክፍል 1 ሃይማኖተ አበው/

«ሠለስቱ ስም አሐዱ እግዚአብሔር- ሦስቱ ስሞች አንድ እግዚአብሔር /ቄርሎስ እስክንድርያው ሊቀጳጳስ ሃይማኖተ አበው/

«ንባርኮ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» አብን ወልድን መንፈስ ቅዱስን እናመሰግነዋለን /ሃይማኖተ አበው ሕንጻ መነኮሳት/

"አብሶ ኢተወለደ አላ ውእቱ ወላዴ ወልድ እምቅድመ ኩሉ ዓለም -
አብ አልተወለደም ነገር ግን ቅድመ አለም የወልድ አባት ነው /
ሃይማኖተ አበው አትናቴዎስ ክፍል 4/

## 4. የስላሴ አንድነት

እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው:: /ዘዳ 6፤4/

"ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ" /ኤፌ 4፤6/

"ለእኛ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን" /1ቆሮ 8፤6/

እንዲሁም ዘዳ 4፤35፣ ዘዳ 20፤2-3፣ ኢሳ 44፤6፣43፤10-11፣ 45፤5፣ 1ኛጢሞ 2፤5 ተጠቅሷል/ ነገር ግን በአንድነቱ በህልውና በባህሪ በመለኮት በአገዛዝ በስልጣንና በፈቃድ ይህን በመሳሰሉት ነው::

በመለኮታዊ ባሕሪይ አንድ የሚሆንበት አንዱ በአንዱ ውስጥ ህልው ሆነው ስለሚኖሩ ነው ይህም ማለት ሦስት ሲሆኑ አንድ፡ አንድ ሲሆኑ ሦስት ሆነው ይገኛሉ:: እስቲ ክርስቶስ ያስተማራቸውን እንይ:- ፊሊጶስ፤- ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው ኢየሱስም አንተ ፊሊጶስ ይህን ያህል ዘመን ከአንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቷል ... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምኑምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፣ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ» /ዮሐ 14፤8-11/ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ዘንድ እንዳለ /ዮሐ 15፤26/ ከወልድ ጋርም ህልው ሆኖ እንዲኖር በሮሜ 8፤9-11 ተጽፏል::

በስልጣንም «እኔና አብ አንድ ነን» /ዮሐ 10፤30/ በማለት መበላለጥ እንደሌለ ተገልጾአል:: «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ተብሎ በወልድና በአብ ልዩነት እንደሌለ ሲገለጽ ሁለቱም እግዚአብሔር ተ ብለዋል:: መንፈስ ቅዱስም ደግሞ እንዲሁ እግዚአብሔር ተብሏል ሐዋ 5፤3-4፣ 1ኛቆሮ 3:16-17/ በአገዛዝና በፈቃድም በኩል « ያ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል ... አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል ... ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም» /ዮሐ 5፤19-24/::« አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው:: ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንካኦ የለውም በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው» /1ኛዮሐ 2፤22-23/:: በክርቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት /2ኛዮሐ 1:9/ መንፈስ ቅዱስም «የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርም» ክርስቶስ« ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ አለ» / ዮሐ 16:13-15፣ ዮሐ 14-26/ ይህ ልዩ አንድነታዊ /ኢቻድ/ ነው:: ይህንን እውነት የጥንት አባቶች ለማስረዳት የተለያዩ ምሳሌዎችን ይጠቀማሉ ለምሳሌ ሥላሴን በእሳት መስሎ መናገር አብ በነበልባሉ፣ ወልድ በብርሃኑ፣ መንፈስ ቅዱስ በሙቀቱ /በዋዕዩ/:: «ነበልባል ብርሃኑን ፈንጥቆ ጨለማን በማራቁ፣ ሙቀቱ /ዋዕዩን/ ልክ በመሞቁ ህልውናውን እንዲያሳውቅ፣ የአብ ህልውናው በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስለተገለጸ ነው እንጂ በሥላሴ መቅደም መቀዳደም መብለጥ መበላለጥ ኖሮባቸው አይደለም::»[20]

---

20. መድሎተ አሚን ገጽ 286-287

የፀሐይ ምሳሌነት ፀሐይ አንድ ሲሆን ሦስትነትም አለው:: ክበቡ ብርሃኑ፣ ሙቀቱ፣ ሦስትነትን ያመለክታል እንደ ክበቡ አብ፣ እንደ ብርሃኑ ወልድ እንደ ሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይባላል:: "የፀሐይ ክበብ ከሰማይ እንዳይወርድ አብ ከመንበሩ አይናወጥም»[21] ብርሃንና ሙቀት ከፀሐይ ክበብ ወርደው ሲመጡ ከሀሐይ አያንሱም ምክንያቱም ተ ፈጥሮአዊ ባህሪያቸው አንድ ነው ወልድም መንፈስ ቅዱስም ከአብ ዘንድ ወጥተው ሲመጡ አያንሱም ብርሃንና ሙቀት ሲወጡም ከክበቡ አያንሱም አይበልጡም የተገኙ እንጂ ከፀሐይ የተፈጠሩ አይደሉም:: ከሦስቱ አንዱ ቢጎድል ፀሐይ እንደማይባል የስላሴ መገለጥ እንዲሁ ነው::

የሰው ልጅ ተፈጥሮ ምሳሌነት ሠው ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ነው:: ሠው ልባዊ ነው ሲባል ልቡን ወይም ስነ-ልቡ መናገር ነው:: እንዲሁም ይህ ሰው ነባቢ ነው ሲባል ደግሞ ቃሉን ያመለክተናል፤፤ ሕያው ነው ያልን እንደሆነ ደግሞ እስትንፋሱን ወይም ስለ ነፍሱ መናገራችን ነው እንግዲህ ለአንድ ሰው እነዚህ ሁሉ ተሟልተውለት ሲገኝ ጸንቶ ይኖራል::

ሥላሴም በአብ ልብነት ያስባሉ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ጸንተው ይኖራሉ:: አብ በልብ ይመሰላል ወልድ ደግሞ በቃል ይመሰላል መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በእስትንፋስ ይመሰላል::[22]

---

21. መዝገበ ሃይማኖት ምዕ 2-3

22. አዕማደ ምስጢር ገጽ 13

## 2 ምስጢረ ስጋዌ

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን /የሰው ልጅን/ ፈጥሮ ከስልጣንና ከክብር ጋር በዔደን ገነት ሲያኖራቸው /ዘፍ 1-26፤28፣ ዘፍ 2፤6-8/ የገዢና የተገዢ ምልክት የነበረው ትዕዛዝ በዲያብሎስ ሃሳብና ምክር በማፍረሳቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ህብረት ተቋረጠ። ክብርና ስልጣን አጥተው ከኤደን ገነት ከእርግማን ጋር እንዲወጡ ሆነ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሠው በራሱ መልካም ግብርና አጠቃላይ ሁኔታ የመዳን አቅም ስለሌለውና በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረቱን መቀጠል ስላልቻለ የሰሡን ልጅ ወደ ቀደመ ቦታው፣ ስልጣኑና ክብሩ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ያለውን ህብረት ይቀጥል ዘንድ አንድያ ልጁን በመላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም "ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ"[23] ስለ ሰው ልጅ ቤዛ የሆነበት ይህ የማዳን ሥራ ምሥጢረ ሥጋዌ /ሠው የመሆኑ ግሩም ምስጢር/ በመባል ይታወቃል።

**1.ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ አለም ከመምጣቱ በፊት ማን ነበረ?**

1.1. <u>እግዚአብሔር ነበር</u> "በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ... ቃልም /ኢየሱስ ክርስቶስ/ ሥጋ ሆነ ጸጋና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ" /ዮሐ1፤1፣ ቁጥር 14/ ይላልና ቅድመ ልደትም ድህረ ልደትም ቢሆን እግዚአብሔር ነው።

1.2. በአባቱ እቅፍ ያለ ወልድ ነበር "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንካአ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው /ዮሐ 1፤18/ "እቅፍ" ማለት በመለኮትነትና በተለየ ትስስራዊ ፈቅር ውስጥ እንደነበረ የሚያሳይ ነው ።

---

23. መራሔ ድኅነት - ከብርሃኑ ጉበና ገጽ 23

1.3. መለኮት ነበር "በእርሱ /በክርስቶስ/ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል" /ቆላ 2፤9/

1.4. አምላክ ተብሎ ተጠርቷል " ስለ ልጁ ግን አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል ... ይላል" /ዕብ 1፤8/

1.5. የሚቀድም የሚበልጥም የሌለው ተብሏል "ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፤- አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል:: ... አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያው እኔ ነኝ" /ራዕ 1፤8፣ 17-18/

1.6. አለም ሳይፈጠር በክብር ነበር " ... ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር ... " ይላል::

ስለዚህ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አበው ምርኩዝ አድርገው በተለየ አካሉ ተፈናዊ /ተላኪ/ በተለየ ስሙ ወልድ፣ በተለየ ኩነቱ ተወላዲ /ልጅ/ በባሕርዩ ደግሞ ነባቢ ቃል ይሉት ነበር::[24] ደግሞም ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወለደ፣ ተወለደ እንጂ አልተፈጠረምና ዘተወልደ ወኢኮ ዘተገብረ ሲሉ ሰለስቱ ምዕት አስረድተዋል::[25] በአጭሩ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፣ ከአባቱም ጋር ያለመቀዳደም ዘላለማዊ ኗሪና ትክክል፣ በመለኮት አንድ የሆነ የስላሴ አንዱ አካል ነበረ አሁንም ነው::

## 2. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ምን ሆነ?

### 2.1 ሥጋ ለበሰ /ሆነ/

«ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ / ዮሐ 1፤14/

«ወደ ቤትም ገብተው ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፡ ወድቀውም ሰገዱለት ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ

---

24 .ቅዳሴ ማርያም

25. ጸሎተ ሃይማኖት

ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት» /ማቴ 2፤11/

« ... በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የያዘው የመላዕክትን አይደለም ::»/ዕብ 2፤15/

## 2.2 ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ተሰጠው

"ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ ... ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል ... ስለዚህ ደግሞ ከአንች የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ያባላል» /ሉቃ 1:30-35/

"እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ በነብይ ከጌታ ዘንድ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኗል ትርጓሜውም፤- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው» /ማቴ 1፤21-23/

"በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደ ረገው ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» /ፊሊ 2፤9-11/

## 2.3 ከአብ ጋር የተካከለ ክብሩን ትቶ እጅግ ትሁትና ታዛዥ ሆነ

«እርሱ /ኢየሱስ/ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ... ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም

ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ" /ፊሊ. 2፥6-8/

"ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተ ወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» /ገላ 4፥4-5/

## 2.3. በሥራው /በድርጊቱና በትምህርቱ/ እግዚአብሔርን የተረከ ወይም የገለጠ ነበረ።

"መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንካአ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው» /1ዮሐ 1፥18/

«እኔን ያየ አብን አይቷል ... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገ ረውም ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለሥራው እመኑኝ» /ዮሐ 14፥10-11/

"ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ፡- እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር" /ዮሐ 5፥18/

«አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ ይህ የማደርገው ሥራ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራል» /ዮሐ 5፥36/

እንግዲህ አንባቢ ሆይ ከዚህ በታች ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ጊዜ እግዚአብሔርነቱንና ባህሪያቶቹን እንዴት እንደገለጠው በማስተዋል ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብብ፡-

ሀ.የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ቸርነት[26]/ኢዮ 42፥2፣መዝ(145) 16

- አጋንንትን አስወጥቷል /ማር 5፥1-16/
- በውኃ ላይ ተራምዷል /ማር 6፥45-51/

---

26. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካ ዕይታ ገጽ 77

- ነፋስና ማዕበልን አዟል /ሉቃ 8፤22-25/
- ምግባረ ብልሹዎችን ለውጧል /ሉቃ 19፤ 1-9/
- ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል /ዮሐ 2፤1-11/
- ከሁለት ዓሣና ከአምስት እንጀራ 5000 ሺ አጥግቦ አትርፏል / ማቴ 14፤15-21/
-ዓሳ ሳያጠምዱ ያደሩ ሙያተኞችን በርካታ ዓሣዎችን ሠጥቷል / ዮሐ 21፤3-6/

ለ. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ሁሉን አዋቂነት :-/መዝ (139)፤2-4፣ 1ኛሳሙ 2፤3-8/

- እርሱ ገና ሳይሆን በፊት የወደፊቱን የሚያውቅ ነው /ሉቃ 21፤1-28/
- ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር ዝርዝር ጉዳዮችን የገለጸ ነው /ማር 14፤12-16/
- የሳምራዊቷን ሴት ስውር ኃጢአቶች ያወቀ ነው /ዮሐ4:17-18/
- በሰማይና በምድር ሁሉ ሥልጣን ያለው ነው /ማቴ 28፤18/

ሐ. የእግዚአብሔር ፍቅር /1ዮሐ 4፤8/

- ከማህበረሰቡ የተገለሉ ለምጻሞችን ፈውሷል /ሉቃ 17፤11-19/
- ጋለሞታ ሴት ይቅር ያለና ያዘነላት ነው /ሉቃ 7፤36-48/
- ልጇ ለሞተባት መበለት አዝኖላት አስነስቶ ሰጥቷታል /ሉቃ 7፤11-15/
- ሠቀለው የገደሉትን ይቅር ያለና ምህረት የለመነ ነው /ሉቃ 23፤34/
- ገና ኃጢአተኞችና ዓመጸኞች ሳለን ለኃጢአታችን ዋጋ የከፈለልን ነው /ኢሳ 53፤5፣ ሮሜ 5፤8/

መ. የእግዚአብሔር ርኅራኄና መልካምነት /ሰቆ.ኤር 3፤22-26/

- የሳምራዊቷን ሴት ባዶነትና የስሜት ጠባሳዎችን የገነባና የጠገነ ነው /ዮሐ 4፤4-29/

- ዲዳና ደንቆሮ የነበረውን ሰው የፈወሰ ነው /ማር 7፥31-37/
- ህጻናትን ያቀፈና የባረከ ነው /ማር 10፥13-16/
- የአንድ ሰው የሰለለ እጅ የፈወሰ ነው /ማር 3፥1-6/
- ወንድማቸው ሞቶ ያዘኑትን ቤተሠብ ኃዘናቸውን ወደ ደስታ የለወጠ ነው/ዮሐ 11:33-34/

ሠ. የእግዚአብሔር ቅድስናና ቁጣ /1ኛጴጥ 1:15-16፣ ዘሌ 19፥1-2፣ ዘዳ 20፥5/

- እርሱ ቅዱስ ነቀፋ የሌለበትና ንጹህ ነው /ዕብ 7፥26/
- ምንም ኃጢአት ያልፈጸመና ውሸት ያልተናገረ ነው /1ጴጥ 2፥22/
- ተከሶ በቀረበ ጊዜ ምንም በደል አልተገኘበትም የተባለ ነው /ሉቃ 23፥4/
- ጠላቶች የሚከሱበት በደል ያጡበት ነው /ዮሐ 8፥46፣ 10፥32-34/
- ገንዘብ ለዋጮችን ከመቅደስ በጅራፍ ገርፎ ያባረረ ነው /ዮሐ 2፥14-16/
- አጋንንት እንጠፋለን ብለው በፊቱ የተንቀጠቀጡለት ነው /ማር 1፥24/

ረ. የእግዚአብሔር ፍትሕና ምህረት /ዕብ 2፥2-3፣ መዝ (103)፥10/

- እርሱ ወደ ሴት ተመልክቶ የተመኘ በልቡ አመንዝሯል ያለ ነው /ማቴ 5፥28/
- እርሱ ጋለሞታ ሴት እግሮቹ ስር በንስሐ ስታለቅስ ኃጢአቷን ይቅር ያላት ነው/ሉቃ 7፥36-48/

ሸ. የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ህልውናና አለመለወጥ /ሚልክ 3፥6፣ ኢሳ 43፥6/

- ከ2000 ሺ. አመት በፊት ከአብርሃም ጋር የነበረና የተነጋገረ ነው /ዮሐ 8፥56-59/

-ዳዊት ከአንድ ሺ አመት በፊት እረኛዬ ያለው ነው /መዝ (23):1/

- ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል የተባለለት ነው /ዕብ 1፤8/

- ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው የተባለለት ነው /ዕብ 13፤8/ እንግዲህ ከላይ በተጠቀሱት በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስ ረጃዎች በመንተራስ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: አጠቃላይ ስሞቹም ማንነቱንና እግዚአብሔርነቱንም ይገልጣል:-

- አዳኝ ማቴ /1፤21/
- የእግዚአብሔር ልጅ /አንድያ/ ዮሐ 5፤25፣ 10፤36፣ 11፤4፣ ማቴ 16፤16/
- የሰው ልጅ /ዳን 7፤9-14፣ ዮሐ 5፤27/
- ቅዱስ /ሉቃ 4፤34/
- ሁሉን ቻይ/ራዕ 1፤8/
- የእግዚአብሔር ቃል /ዮሐ 1፤1፣ 14/
- የነገሥታት ንጉሥ /ራዕ 19፤16፣ ሐዋ 10፤36/
- አማኑኤል /ኢሳ 7፤14፣ ማቴ 1፤23/
- የምድር ሁሉ ፈራጅ /ሐዋ 17፤31/
- የእግዚአብሔር በግ /ዮሐ 1፤29-36/
- የይሁዳ ነገድ አንበሳ /ራዕ 5፤5/
- ድንቅ መካር /ኢሳ 9፤6/
- እኔ ነኝ /ዮሐ 8፤24/
- አልፋና ኦሜጋ /ራዕ 1፤8 እና 22፤13/
- መሢህ /4፤25-26/
- የሰላም አለቃ /ኢሳ 9፤6/
- መልካም እረኛ /ዮሐ 10፤14/
- የክብር ንጉሥ /መዝ (24)፤7 እንዲህ ያሉ መጠሪያ ስሞች ያሉት ፍጡር ከዚህ በፊትም አልነበረም ወደፊትም አይኖርም በመሆኑም ክርስቶስን ለማወቅ የፈለጉ ሰዎች ሁሉ ይህን በሚገባ ሊያውቁ ግድ ይላቸዋል::

## 2.4. ስለበደላችን የተሠቀለ የሞተ የተቀበረ የተነሣ ነው

« በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንም ተሸከሚል ... እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን ... ተጨነቀ ተሠቃየም አፉንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም» /ኢሳ 53፤4-7/

« ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና» /ሮሜ 5፤6/

« ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹህ በፍታ ከፈነው ከዓለት በወቀ ረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው በመቃብርም ደጃፍ ከላይ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ »/ማቴ 27፤59/

« እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሳው ይገለጥም ዘንድ ሠጠው » /ሐዋ 10፤40/

## 2.5. ወደ ሰማይ አረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ

« ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው» /ሐዋ1፤9/

« ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው» /ዮሐ 3:13/

« የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ነው» /ሮሜ 8:34/ /ለተጨማሪ ገጽ 24 ይመልከቱ /

“ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ” /ዕብ 1፤3/

## 2.6 ደግሞም ተመልሶ ለፍርድ ይመጣል

«ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው» /ሐዋ 1:11/
«የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላዕክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል:: አህዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋቂ::» /ማቴ 25፤31/
« እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋየ ከእኔ ጋር አለ» /ራዕ 22:12፣ 20፣ 21/

## 3. የኢየሱስ ክርቶስ ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት እንዴት በአንድነት ሊስማሙ ቻሉ?

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ስለ፡ዐሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ለምሳሌ :-

« ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን::» / ሮሜ 9:5 /
« እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላም ሀይወት ነው» / 1ኛዮሐ 5:20 /
« ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» / ኢሳ 9:6 /
« ስለ ልጁ ግን አምልክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይሆናል» / ዕብ 1:8 /

" ... ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ... ቃልም ሥጋ ሆነ ::"
/ ዮሐ 1:1-14/

"ቶማስም ጌታየ አምላኬም ብሎ መለሰለት" /ዮሐ 20፤28/

በእነዚህና በበርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር የሆነ አምልክ እንደ ሆነ ስንገነዘብ በአንጻሩ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው እንደ ነበረ ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ:-

- እንደሰው መጸነሱ መወለዱ :- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከቅድስት ድንግል ማርያም ተጸነሰ ተወለደ ::/ ሉቃ 1:30-35፣ ሉቃ 2:7 /
- የሰው የዘር ሃረግ መያዘ :- " የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ" / ማቴ 1:1 /
- እንደ ማንኛውም ሰው ምግብ መጠቀሙ :- «የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቶአልና»/ ሉቃ 7:34 /

- " አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጾመ በኋላ ተራበ" / ማቴ 4:2 /

- እንደ አንድ ምንም የሌለው ድሃ መኖሩ

- "ኢየሱስም:- ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይ ወፎችም ማሳፈሪያ አላቸው::ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው::" /ማቴ 8፤20/

- " ስለ እናንተ ድሃ ሆነ " / 2ቆሮ 8:9 /

- እንደ ማንኛውም ሰው እድሜው መቆጠሩ:- "የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ እንደ በዓሉ ስርዓት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ" /ሉቃ 2፤42/

- እንደ ማንኛውም ሰው መተኛቱ፤- " እርሱ ግን ተኝቶ ነበር" /ማቴ 8፤24/

እንዲሁም ታመመ፣ ተጨነቀ፣ ተሠቃየ፣ ጸለየ፣ ተሠቀለ፣ ሞተ፣ ተነሣ ... ወዘተ /ኢሳ 53፤6፣ ማቴ 27፤46፣ ዮሐ 19፤18፣ ዮሐ 19፤30፣ ማቴ 28፤5-7/

እነዚህ ሁሉ የሠው ባህሪዎች ናቸው እንጂ መለኮታዊ ባህሪያት አይደሉም።ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ ራሱን «የሰው ልጅ» በማለት ብዙ ጊዜ ይጠራም ነበር። / ማቴ 11:19፣ ማቴ 13:41፣ ማቴ 16:27፣ ማቴ 17:9፣12፣ ማቴ 18:11፣ ሉቃ 12:40፣ ዮሐ 5:27፣ ዮሐ 6:53 / በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሠው ነበረ።

እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው? እግዚአብሔርም/ዮሐ 1:1/ ሠውም ነው / 1ጢሞ 2:5 /። በሌላ አገላለጽ የእግዚአብሔርም ልጅ የሠውም ልጅ ተብሎ ሁለቱም መጠሪያዎቹ ለእርሱ ሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናገኛቸዋለን። /ማቴ 16፤13፣16/።

"ልጅ" የሚለው ቃል ተፈጥሮአዊ ማንነትን የሚገልጽ እንጂ በዚህ ዘመን ቋንቋው እንደ ሚያገለግለው ውልደትን አያመለክትም ። ይህም ማለት በተፈጥሮ የወፍ ልጅ - ወፍ፡ የአንበሳ ልጅ- አንበሳ የነብር ልጅ- ነብር እንደሆነ ሁሉ የሰው ልጅም - ሰው እንጂ ሌላ እንዳልሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውልጅ ሰው መሆኑንና የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር እንደሆነ ተፈጥሯዊ ማንነቱን የሚገልጽ እውነት ነው። በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሆነ አንድ ጌታ ነው። እርሱንም የሚመስል ማንም የለም። ደግሞም ይህ ማለት እርሱ ከፊል ሰውና ከፊል አምላክ ሳይሆን ዳሩ ግን እንደኛ ፍጹም ሰው ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ ፍጹም አምላክ የሆነ አንድ አካል ነው ።ይህን ሁኔታ አባ መልከጸዴቅ ሲቀጻጸስ እንዲህ ይገልጹታል።

"እርሱ ቀዳማዊ አምላክነው እርሱን የሚቀድም የሚበልጥም ከቶ የለም እርሱ የመጀመሪያውና የመጨረሻው አምላክ ነው። ያ ቀዳማዊ አምላክ ቃለ አብ በፍጻሜ ዘመን ሰው ሆኖ ሥጋንም ለብሶ ለሰው ልጅ

ተገለጠ አንድነቱንም ከሰው ጋር አደረገ ከኃጢአትም በቀር ሰው እንደ ሆነው ሁሉ ሆነ: ማለት ፍጹም ሰው ሆነ:: ሰው የሠራውንም ሁሉ ሠራ ይኸም ሲሆን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ አላተለየም፣ ልዑላዊ መንበሩንም አልለቀቀም፣ እርሱ እውነተኛ አምላክ ሲሆን እውነተኛም ሰውም ነውና፣ በዚህም ምክንያት በመሬት ተመላለሰ፣ ወጣ ወረደ፣ ሰው የሰራውን ሁሉ ሠራ በዚህም ፍጹም ሰውነቱ ታወቀ ተረዳ:: ስለ እርሱም የምንማረውና የምናስተምረው ትምህርት ምስጢረ ሥጋዊ ይባላል፣ ትርጉሙም ሰው የመሆን ምስጢር ማለት ነው አምላክ ሲሆን ሰው፣ ሰውም ሲሆን አምላክ ነው ብሎ ለመናገር ከባድ አንድም ረቂቅ ነገር ነውና»[27]

ከዚህም በላይ የቀደሙት አበው ይህን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ሰው መሆን የነበራቸውን አቋም በተለየ ቋንቋ ይገልጹት ነበር:: ይህም ሚጠት፣ ውላጤ ፣ ቱሳሔ ፣ ትድምርት በሚሉ ቃላት አብራርተው አስተምረውናል እስቲ ላፍታ ያህል እነዚህን ቃላት እንያቸው:-

ሚጠት:- ማለት እንደ ሙሴ በትር፣ እንደ ግብጽ ወንዝ መሆን ማለት ነው:: የሙሴ በትር በመጀመሪያ በትር ስትሆን ኋላ እባብ ሆነች መልሶ ቢያነሳት ደግሞ በትር ሆነች:: የግብጽ ወንዝም ሙሴ በመታው ጊዜ ቀድሞ ውኃ ነበር ኋላ ደም ሆነ እንደ ገናም ውኃ ወደ መሆን ተመለሰ:: /ዘጸ 4፤1-9፣ ዘጸ 7:16/ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆን ግን እንዲህ ያለ መፈራረቅ የለበትም::ሲሉ "እንበለ ሚጠት" አሉ::

ውላጤ፤- ማለት እንደ ሎጥ ሚስት፣ እንደ ገሊላ ቃና ውሃ፣ መሆን ማለት ነው:: የሎጥ ሚስት ፊት ሰው ነበረች ኋላ የጨው

27. የኢ.ኦ.ተ.ቤ እምነትና ትምህርት በአባ መልከጸዴቅ ሊቀጳጳስ ገጽ150

ሐውልት ሆና ቀረች በገሊላው ቃና ሠርግ ላይ ደግሞ ወይን ሲያልቅ ውኃው ወደ ወይን ጠጅ ተለወጠ።የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆን ግን እንዲህ መለወጥ የሌለበት ነው። ትናንትና ዛሬም እስከ ለዘላለም ያው ነውና /ዘፍ 19፤26፣ዮሐ 2:7፣ ያዕ 13፤8/ ሲሉ "እንበለ ውላጤ" አሉ።

ቱሳሔ፡- ማለት ቅልቅል ማለት ሲሆን እንደ ማርና እንደ ውኃ እንደ ወተትና እንደ ውኃ ማለት ነው። ማርና ውኃ ሲቀላቀሉ ማእከላዊ ስም፣ ማእከላዊ መልክ ፣ ማዕከላዊ ጣዕም ይገኝባቸዋል። ማዕከላዊ ስም ማለት ብርዝ፣ ማዕከላዊ መልክ ማለት እንደ ማር ሳይነጣ እንደ ውኃ ሳይጠቁር ሰርጆን ይመስላል።ማዕከላዊ ጣዕም ማለት ደግሞ እንደ ማር ሳይከብድ እንደ ውኃ ሳይቀል ማእከላዊ ጣእም ሲሆን ነው። ውኃና ወተት ሲቀላቀሉም ማዕከላዊ ኅብር ይኖ ረዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆን ግን ከሁለቱም የሆነ ማዕከላዊ ማንነት የለውም። እያንዳንዳቸው የራሳቸውን ባህርያት እንደ ያዙ በአንድ አካል ውስጥ ይኖራሉ እንጅ።ስለዚህ አበው "እንበለ ቱሳሔ" አሉ።

ትድምርት፡- ማለት እንደ ልብስና እንደ እንጀራ ማለት ነው ልብስ ቢደርቡት ይደረባል ቢነጥሉት ይነጠላል የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት ግን የማይደራረቡ የማይነጣጠሉም መለያየት በማይቻል ሁኔታ አንድ ነው በማይመረመር ምስጢር ፍጹም አምላክ ፍጹም ሠው ነው፤፤ሲሉ እንበለ ትድምርት አሉ።እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ሚጠት ፣ያለ ውላጤ ፣ያለ ቱሳሔና ያለ ትድምርት አምላክነቱና ፍጹም ሰውነት በተዓቅቦ ፍጹም ሰው ፣ፍጹምም አምላክ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል ። ክብር ሁሉ ለእርሱ እንዲት ስግደት ጋር ይሁን።

## 4. ደህንነታችን /ጽድቃችን/ በእርሱ ተጠናቋልን?

4.1 ደህንነት:- በእርግጥም ደህንነታችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተጠናቋል። ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት» /ሮሜ 5፥12/ ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔር ክብር ጎድሎአቸዋል» /ሮሜ 3:23/ ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ ... ሁሉ ተሳስተዋል /ሮሜ 3:11/ በማለት የሠው ፍጥረት በሙሉ ኃጢአተኛ ከመሆኑ የተነሳ የኃጢአት ደመወዝ የሆነውን ሞት ተቀብለዋል /ሮሜ 6:23/።

ስለዚህ ሰው በራሱ ጥረት ሊድን እንደ ማይችል መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል /ሮሜ 3:20፣ ገላ 2:16/ «ምንም እንኳ መልካም ሥራ እጅግ የተመሰገነ ተግባር ልዩና የተቀደሰ ሕይወት የሚመስል ቢኖርም ከክርስቶስ ደም በስተቀር ይህ ሁሉ ሰውን ሊያድን አይችልም ... አለበለዚያ መልካም ምግባር ያላቸው ኢ - አማንያን ስለመልካም ምግባራቸው ይድኑ ነበርና።»[28]

ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም በመሆን እርቅ ፈጸመ እንደ አምላክነቱ ከአባቱ ጋር ፍርድን ጽድቅን የሚሰጥ ሲሆን እንደ ሰውነቱ የሁላችንንም በደል ተሸከመ የከፋ ኃጢአት በእንጨት መስቀል ነበርና የመስቀል ሞትን ሞተ። ምክንያቱም የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና /ሮሜ 6፥23/ በዚህም ኃጢአትን በመስቀል ገሎ የእግዚአብሔርን ሠላም ሠጠ «በአንዱም /በአዳም/ በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርቶስ በኩል በሕይወት ይነግሳሉ» ተብሎ ተጻፈ /ሮሜ 5፥17/

---

28. ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት በፓፓ ሹኖዳ ሣልሳዊ ገጽ 9

ይህ የዘላለም ህይወት /ደህንነት/ ለመጡ ጥቂት ሰዎች ብቻ ነውን? አይደለም ክርስቶስ ዋጋ የከፈለው ለዓለም ሁሉ እንደ ሆነ አብም ለሁሉ እንደላከው «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::ዓለም በልጁ እንዲድን ነው... » ዮሐ 3:16-17/ ተብሎ ተጽፏልና ለዓለም ሁሉ ነው::

**4.2 እምነት** :-በ15ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በተነሳው የፕሮቴስታንት ንቅናቄ አስተምህሮ ላይ የመዳን ስጦታ ለዓለም ሁሉ ሲሆን ይህም በክርስቶስ ቤዛነት አምነው ለሚቀበሉ ይሰጣል: የሚለው የአርመናውያን /አርመኒዝም/ አስተምህሮ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሔር ከሞቱት መካከል ለዘላለም ህይወት ይመርጣል ልጁንም የሠጠው ለተመረጡት ብቻ ነው: የሚሉ ካልቬናውያን /ካልቪኒዝም/ ይባላሉ ለዚህ ሃሳባቸው ደግሞ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን ያመጣሉ እስከ ዛሬም ድረስ ክርክሩ አለ::

ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የአርመኒዝም ሙሉ አስተ ምህሮ ሲኖራት ይህም አርመናውያን ሳይወለዱ ገና ጉንት በፍሬምናጦስ የተሰበከላትን ወንጌል በማወቅ ሠው የመዳን ምርጫን የመምረጥም የመተውም ፈቃድ እንዳለውና በክርስርቶስ ቢያምን የዘላለም ህይወት እንደሚያገኝ እንጂ «በተጽዕኖ» ሠዎችን ወደ ዘላለም መንግስት እግዚአብሔር እየመረጠ ወይም«እያዳላ» አያስገባም ብላ ታስተምራለች ለዚህም አገልግሎቱ ሰው ሽፋንና ጉልበት አያገኝ እንጂ ወንጌልን ሠዎች አምነው እንዲድኑ ትሰብካለች::ነገር ግን አንዴ ከዳንን በኋላ መልሰን በኃጢአት ብንኖር እንሞት ዘንድ አለንና/ሕዝ 18:24/ ህይወታችን በስነ ምግባር የታነጸ ሊሆን ይገባል:: የተሰወጠ ባህሪ ፍሬ ይጠበቅበታልና: ብላ ቤተክርስቲያን ከያዕቆብ መልእክት 2:18-26፣ ዕብ 2:1-3፣ ዕብ 10:19-31 /

ተነስታ ታስተምራለች ። «ፍሬ የሌለው ሁሉ» ይቆረጣል /ዮሐ 15፤2፣6/ ይህም ፍሬ ሰዎች ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ መቤዠትና ያለ መንፈስ ቅዱስ ክንዋኔ ምንም አይነት ፍሬ ሊያፈራ አይችልም ትግል ብቻና ውድቀትም ነው፡ትላለች። ይህም አስተምህሮ ኋላ የመጣው የአርመኒዝም አስተምህሮ ሙሉ ለሙሉ ይቀበለዋል። ካልቪኒዝሞች ደግሞ ሠው ምንም የማድረግ አቅም የለውም የሚድነው በእግዚአብሔር ምርጫ /ሮሜ9:13-16/ መለወጥና መንፈሳዊ ፍሬም የሚያፈራው በመንፈስ ቅዱስ ስራ በመሆኑ/ ገላ5:22 ሮሜ 8:11/ የሰው ድርሻ ወንጌል የመስማትና ልብን የማዘጋጀት ብቻ ነው / ምሳ16:1 / ስለዚህ በበደል የሚኖር ካለ ጥንቱም የእግዚአብሔር ልጅ ያልነበረ አስመሳይ ነው/1ዩሐ2:19/ ይላሉ። ይህም ሠው በራሱ ፈቃድና ምርጫ እንደሌለው የሚያመለክት ነው።የሆነ ሆኖ እግዚአብሔር ምርጫ ያድርግም ኤድርግም ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ካላመኑ አሁኑኑ ተፈርዶባቸዋል።/የሐ 3:18 / አርመኒዝም ቅድስናን በተመለከተ እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ብሎ አዟል በሐዋርያትም ተ ሥብካአል /1ጴጥ 1:15/ ይህ ቅድስናችንን እኛው ራሳችን ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ጋር ኃጢአትን በመሸሽ ለመቀደስ በመወሠንና በመኖር የሚፈጸም ነው። ይህ ካልሆነ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ይቀጣል ይላል ይህም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አስተ ምህሮ ነው። ካልቪኒዝም በበኩሉ ቅድስናን በተመለከተ ያለው አቋም ቅድስና የእግዚአብሔር ሥራ እንጂ ሠው በራሱ ሊያመጣው አይችልም በማለት የእግዚአብሔርን የመለወጥ ኃይል ላይ ይመረኮዛል ። ነገር ግን ሁለቱም አስተምህሮቶች ሠው ኢየሱስ ክርስቶስን ቢያምን ይድናል ቅድስናውንም ቢጠብቅ ደቀመዝሙሩ ይሆናል። / ዮሐ 3፤18፣ ዮሐ 3፤36፣ 1ኛቆሮ 6፤9-11/ አንድ ሰው ኃጢአቱን በመናዘዝ በክርስቶስ ደም ሊነጻ ይገባዋል።ደሙ የኃጢአታችን ማስተ ሰሪያ ነውና /1ኛዮሐ 1፤7፣ 2፤2/ እርሱ ክርስቶስ ሠላማችን ጽድቃችን ደህንነታችን መድሃኒታችን ነው።ገላ2:16 -21፣ ኤፌ 2:14፣

ዮሐ 4፥42 / በሚለው ይስማማሉ::

4.3 ምልጃ :- ሌላው ልብ ልንለው የሚገባን እውነት ኢየሱስ ክርስቶስ አስታራቂያችን ከአብ ዘንድ ያለ ጠበቃችን እንደ ሆነ ማመን ነው :: በሰውና በእግዚአብሔር ያለ መካከለኛ አስታራቂ /አማላጅ-ሊቀ ካህናት/ እርሱ ነው::የክርስቶስ ምልጃ በሶስት መንገድ የተገለጸ ሲሆን

1ኛ- በአገልግሎቱ ጊዜ:

"ጌታም:- ስምዖን ስምዖን ሆይ እንሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ: እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ::"/ሉቃ22:31/

"አሁንም አባት ሆይ... እኔ ስለዚህ እለምንሀለሁ ስለ ዓለም ስለምንም ...ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም...በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለእነዚህ ብቻ አለምንም" / ዩሐ17:5-21 /

2ኛ.- በተሰቀለ ጊዜ

«ኢየሱስም:- አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ::" / ሉቃ23:34/

"እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢያት ተሸከመ ስለ ዓመአመጸኞችም ማለደ " /ኢሳ53:12/

3ኛ- አሁን በአባቱ ቀኝ ሳለ : / ከእርገት በኋላ /

"የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ነው" /ሮሜ 8፥34/

"እኔም አብን እለምናለሁ" / የሐ14:15 /

"ስለእነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዝአብሄር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል ::" /ዕብ 7:25/

4ኛ.በሺ. አመት ግዛቱም ጊዜ /ራዕይ 20:4-6/

«በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ::እኔም ስለእናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም» /ዩሐ 16:26 /እንግዲህ የምልጃው ማብቂያ ዳግም ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ቃሉ እንዲህ ይላልና ፍጻሜ ይሆናል :-

«በኋላም መንግስቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል ::» / 1ኛ ቆሮ 15:24 /

ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያኖች ሁሉ የአዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆኗአል:: «የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋውንም ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው » / ዕብ 9:15 /

«በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛ ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ነው »/ 2ጢሞ 2:3 /

መካከለኛ የሚቆም ማለት በደረጃው ከከፍተኛ ነገር ዝቅ ያለ ከዝቅተኛው ነገር ደግሞ ከፍ ያለ በመካከል የሚገኝ ሳይሆን ሁለት ወገኖችን ለማስታረቅ ወይም ለማገናኘት በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚቆም ማለት ነው ::ይህ ትርጉም መጽሀፍ ቅዱሳዊ ነው መካከለኛውም አንድ እርሱም ክርስቶስ እንደሆነም ተጽፏል /2ኛ ጢሞ 2:5/:: ደግሞም በእግዚአብሔርና በእስራኤላውያን መካከል በመሆን በቡልይ ዘሮን ያገለግሉ የነበሩትን ካህናት ከነመስዋእታቶቻቸው ሽሮ ራሱ ሊቀካህናት ተብሎ ተጠርቷል ::ህዝቡንም ወደዚህ መካከለኛ ሊቀ ካህናት ወደሆነው ክርስቶስ ተመልከቱ ተብሎም ታዝዛል::/ዕብ 3:1 / የሊቀ ካህናት ስራ በመካከል በመቆም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማሟላትና የህዝቡን ውድቀት በማቅረብ ምህረት እንዲያገኝ ማድረግ ነው ::ይህን አገልግሎት ክርስቶስ በተሻለ ሁኔታ እንደተረከበው የፊተኛውን እንደሻረው ቃሉ ሲናገር :-

« ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ

ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል ::
/ዕብ 7:26 / "እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ :: ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም » /ዕብ 4:14-15/
« እነርሱ ያለመሐላ ካህናት ሆነዋልና እርሱ ግን አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና ያለመሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል» ይላል::
/ ዕብ10:10 /

« ስለዚህ የምትደክም የማትጠቅም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተ ሽራለች ወደ እግዚአብሔርም ምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል» / ዕብ 7:19 /

<u>አበው በክርስቶስ መካከለኛ ሊቀካህንነቱን ያላቸው እምነታዊ አቋም</u>

በጥንቷ ቤተክርስቲናችን ውስጥ ያለፉ አባቶች ይህን እውነት ቤተ ክርስቲናችን ታምንበት እንደነበረ ዛሬ ያሉ የሚመሰክሩ መጻህፍቶቻቸው ትተውልን እንደሄዱ ይነበባሉ :-

1."ሊቀካህናት ዘይቀውም ሎሙ ለቅዱሳን በደብተራ ስምዕ እንተ እግዚአብሔር ተከላ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ - እግዚአብሔር በተከላት የምስክር ድንኳን ለቅዱሳን የሚቆምላቸው ሊቀካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው »[29]
2.« ወዐረቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀ ካህናቲሁ ለአብ - የአብ ሊቀካህናት የሚሆን እርሱ የሰውን ባህሪ / ወገን / ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ»[30]
3."ወኮነ ዐራቄ ለሐዲስ ኪዳን በዊኂዘ ደሙ ቅዱስ /ትርጉም/ በቅዱስ ደሙ ፈሳሽነት የአዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆነ » [31]

---

29.ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ ገጽ122

30.መጽሐፈ ቅዳሴ ወሥርዓተ ቅዳሴ ቁጥር43 ገጽ 41/አመክንዮ ዘሐዋርት/

31.የእሁድ ውዳሴ ማርያም አንቀጽ አንድ

4. «ወናሁ ደመ መሢህከ ንጹሕ ዘተክው በእንቲአየ በቀራንዮ ይኬልሕ ህየንቴየ ዝንቱ ደም ነባቢ ይኩን ሠራዪ ኃጢአትየ ለገብርከ /ትርጉም/፡- ስለ እኔ በቀራንዮ የፈሰሰ ንጹሕ የሚሆን የመሢሕን ደም እነሆ ስለ እኔ ይጮኻል ይህ የሚናገር ደም የእኔን የባሪያህን ኃጢያት የሚያስተሰርይ ይሆን »[32]

5. «ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ አዓርግ ሰማየ ኀበ አቡየ ኀበ አስእል ምሕረተ በእንተ እሊዓየ - ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የእኔ ስለሆኑት ምሕረትን ወደ ምለምንበት ወደ ሰማይ ወደ አባቴ አርጋለሁ አላቸው »[33]

5. <u>በኢየሱስ ክርስቶስ ስም</u> /በኩል/ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ

በርግጥም መጸለይና መቀበል ለሚሻ የተዘጋጀለት መንገድ ቢኖር የጌታችን የመድሃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከመሆኑም በላይ ጠንካራ ትእዛዝ ተሠጥቷል። ቃሉ እንዲህ ይላልና።

«እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።»/ ቆላ3:17/

«በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል» / ዕብ 7:25 /

«ሁል ግዜ ስለሁሉ በጌታችን <u>በኢየሱስ ክርስቶስ ስም</u> አምላኝችንንና አባታችንን ስለሁሉ አመስግኑ»/ኤፌ 5:20/

«አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ » /ሮሜ 1:8/

«እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል » /ዩሐ16:23/

አጋንትንም እንኳን የምንቃወመው ወይም በአጋንት ስቃይ ስር ያሉትን ጸልየን የምንገላግላቸው «በኢየሱስ ስም » እና ስልጣን

---

32. መጽሐፈ ቅዳሴ ሐዋርያት ቁ.106 ገጽ54

33. መጽሐፈ ዚቅ ዘሰኔሚካኤል ገጽ189

ነው / ሐዋ 16: 18 /:: ሐዋርያት እንኳ በዚህ ስም ከፈውሱ እኛማ እንዴታ!

## አበው በክርስቶስ አስታራቂነት/አማላጅነት/ የነበራቸው አቋም

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ እግዚአብሔር/አብ/ ዘወትር ለዘላለም እንዲያስታርቀን፣ እንዲያቀርበን እንዲያማልደን አበው ያምኑ እንደነበረ ከዚህ በታች ከትበው ያስቀመጡትን ቅርሳቸው ያስረዳል ። በተለይ የተሰመረባቸውን ሐረጋት ልብ በል::

"ወኮነ ዐራቂ ለሐዲስ ኪዳን /ትርጉም/ ለአዲስ ኪዳንም አስታራቂ ሆነ" /ኤፍሬም በእሑድ ውዳሴ ማርያም/

"ወአቅረበነ ኀበ እግዚአብሔር አቡሁ /ትርጉም/ ወደ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አቀረበን" /ቅዳሜ ውዳሴ ማርያም/

" ፍቅረ ለነ ኀበ አቡከ ገብርከ ወአረቀ ማዕከሌነ /ትርጉም/ በእኛና በአባትህ መካከል ፍቅርን አደረግህ በመካከልም ሆነህ አስታ ረቅኸን" /ኪዳን /

" ... እስመ ውእቱ ይተነብል በእንቲአነ ለእለ አጥርየነ ሎቱ ሕዝበ ጻድቀ ቀናዔ ለምግባረ ሠናይ /ትርጉም/ በጎ ሥራ ለመሥራት የምንቀና ደግ ወገን አድርጎ ገንዘብ አደረገን ለእኛ ማልዷልና የምናምንበት ሊቀ ካህናት / አስታረቂ/ አለው » / ዮሐንስ አፈወርቅ ሃይማኖተ አበው ም 63፣26/

"ወአራቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀካህናቲሁ ለአብ / ትርጉም/ የአብ ሊቀ ካህናት የሰውን ወገን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ" /አመክንዩ ዘሐዋርያት/

"ወመጽአ ክርስቶስ አራቂ ማዕከለ እግዚአብሔር ወእጓለ እመሕያው ወዐረቀሙ ለእልኢሆሙ" /ትርጉም/ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስማማ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሁለቱንም አስታረቃቸው" ::
/ ሃይማኖተ አበው ዮሐንስ አፈወርቅ ምዕ 68፣21/

" ወአኮ ይኩነነ እንወ ባህቲቶ አላ ተሣሃለነ ፈድፈደ ወፈቀደ ዓዳ

. ይኩን ሊቀ ካህናት ለኀበ አበ ከመ ይስረይ ኃጢአተነ ወበእንተ ዝንቱ ወስከ በዲበ ነገሩ ወይቤ ከመ ይኩኖሙ መሐሬ ለኩሉ ምዕመን ሊቀካህናት ለመንገለ እግዚአብሔር ከመ ይስረይ ኃጢአተ ሕዝበ -/ *ትርጉም*/ሰው የሆነም ዘመድ ሊሆነን ብቻ አይደለም ፈጽሞ ይቅር አለን ኃጢአታችን ለማስተሰረይ ከአብ ጋር ለማስታረቅ ሊቀ ካህናትም ይሆነን ዘንድ ወደደ እንጅ::ስለዚህም ሰዎችን ሊመስላቸው ይገባል ባለው ነገሩ ላይ ጨምሮ በሁሉ አዛኝ የሕዝቡንም ኃጢአት ለማስተሰረይ በእግዚአብሔር ዘንድ የታመነ አስታራቂ ይሆናቸው ዘንድ ነው::»/ሃይማኖተ አበው ዮሐንስ አፈወርቅ ምዕ 62፤13/

« ወሰአሎ ለአብ ያኀልፍ እምኔነ መዓተ ዘረከበነ እምቅድም ከመዘለሊሁ ይኄልቁ ስእለተ ሎቱ እስመ ውእቱ ነስአ እምሳሊነ ከመ ይስአሎ ለአብ በእንቲአነ /*ትርጉም*/ እርሱ ራሱ ልመናን የሚሻ መስሎ ከጥንት ጀምሮ ያገኘን ፍዳ ከእኛ ያርቅ ዘንድ አብን ማለደው እንደገና ደግሞ እንዲያስበን ከእርሱም እንዳይለየን ስለ እኛ አብን ይማልደው ዘንድ» / ሃይማኖተ አበው ቄርሎስ ምዕ. 79:38 /

እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊራራልን የሚችል፣ /ዕብ 4፤15/ የማይለወጥ ክህነት ያለው /ዕብ 7፤23-24/ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው የሚችል የሚሻል አስታራቂ /አማላጅ/ በአብ ቀኝ አለን /ዕብ 7:25/

## 3. ምስጢረ ጥምቀት

መጠመቅ ማለት መነከር፣ መዘፈቅ፣ ውኃ ውስጥ ገብቶ መውጣት ማለት ነው:: ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር መሞትና መቀበር በትንሳኤም በተገኘው አዲስ ህይወት ወደ ፊት ለመኖር አንድ አማኝ ውሳኔውን የሚገልጽበት ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ነው /ሮሜ 6:3-6/ ይኸውም ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈፀም ሥርዓት እንጂ የሚደጋገም አይደለም /ኤፌ 4:5/:: በሚታየው የጥምቀት ሥርዓት የማይታየውን ጸጋ እንቀበላለን /ሐዋ 2:38/

የጥምቀት አስፈላጊነት፡- ጥምቀት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ይጠቅማል:

1. የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመፈጸም በረከትን ለማግኘት /ማቴ 28፤19፣ ማር 16፤15-16/
2. ከክርስቶስ ጋር ተባባሪና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አንድ ለመሆን በህዝብ ፊት ለመመስከር /ሐዋ 2፤41-42፣ ሮሜ 6፤8፣ ገላ 3፤27/
3. የክርስቶስ አርአያነት /ምሳሌ/ ለመከተል /ማቴ 3፤13-17/

በአዲስ ህይወት ለመኖር /ሮሜ 6፤4፣ ቲቶ 3:5፣ ኤፌ 5:26፣ ሐዋ 22:16፣ ሐዋ 2:37-38/ ይጠቅማል::

## የጥምቀት ምሳሌ በብሉይ ኪዳን

በዘመነ ኦሪት ሲኖሩ ሰዎች የእግዚአብሔር ህዝብ ለመሆን መገረዝ ሐይማኖታዊ ግዴታ ነበር:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ መጠበቂያ እንዲሆን የግዝረት ምልክትን በትእዛዝ ሰጥቶ ነበር:: /ዘፍ 17:9-14/ አህዛብ በቁልፋት እስራኤል በግዝረት ይታወቁ ነበርና ያልተገረዙ ሁሉ ተለይተው ይጠፉ ነበር :: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለኢያሱ ከግብጽ ምድር ለወጣው ለእስራኤል ህዝብ የተ ስፋይቱን ምድር ከነቁልፋታቸው /ከነነውራቸው/ እንዳይገቡ እንዲገ ረዙ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር :: /ኢያ 5፤2-9/

ይህ ግርዘት ሊመጣ ላለው ለጥምቀት ምሳሌ እንደ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላ. 2:11-13 ጽፏል::

ኖህና ቤተሰቡ ከጥፋት ለመዳን በመርከብ ውስጥ እንደ ገቡና እንደ ዳኑ ወደ መርከቡ ያልገቡ ሁሉ እንደ ጠፉ ይህም ደግሞ የጥምቀት ምሳሌ እንደ ነበረ ሃዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ጥቂቶች ማለትም ስምንት ነፍስ በውሃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትእግስት በኖህ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም :: ይህም ውኃ ደግሞ ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም :: ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው» /1ኛጴጥ3:20-22/

ስለዚህ ግዝረት ለእግዚአብሔር ህዝብ ግዴታ እንደ ነበረ ሁሉ የጥምቀትም ለክርስቲያኖች ሊፈጽሙት የሚገባ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው /ማቴ 28፤19/ ሌላው የጥምቀት ምሳሌ የእራኤል ህዝብ ባህረ ኤርትራን ማቋረጡ ሐዋርያው ጳውሎስ ከጥምቀት ስርዓት ጋር አያይዞ ጽፏል።ይህም«ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ አባቶቻችሁ ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባህር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባህር ተጠመቁ» /1ኛቆሮ 10፤1-2/ ከሙሴ ጋር የእራኤል ህዝብ ተባብረው እንደ ተጠመቁ እኛም ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ጋር ተባብረን እንጠመቃለን /ሮሜ 6፤4-5/ ብላል።አንድ ሠው የጥምቀት ስርዓት ከመውሰዱ በፊት በጌታችን በመድሐኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይጠበቅበታል /ሐዋ 2፤41፣ ሐዋ 8፤36-39፣ ሐዋ 10፤44-48፣ ሐዋ 16፤14-15/ ወይንም ደግሞ ቤተሰቦቹ የልጁን ህይወት አደራ ተቀብለው በክርስትና እውነት ለመውለድና ለማሳደግ ቃል ገብተው ሲረከቡ አብያተክርስቲያናት ያጠምቃሉ።ይህ ሳይሆን አንድ ሠው ሳያምን የጥምቀት ስርዓት ቢወስድ ገላ እንደ መታጠብ ይሆናል።ልባቸው የግብጽን ዱባና ሽንኩርት በማሰብ ጊዜያቸውን ያባክኑ የነበሩ በጥምቀት ምሳሌ በሆነው በኤርትራ ባህር የተሻገሩ በምድረ በዳ ወድቀው ቀርተዋል እንጂ ጥምቀቱ በራሱ ብቻውን ሊያድናቸው አልቻለም፡ የተስፋይቱንም ምድር አላዩም /1ኛቆሮ 10፤1-10/[34]

## አጥማቂው ማነው?

የጥምቀት ስርዓት መፈጸም ያለበት የቃሉ ታማኝ መምህር የሆነ መሪ ሊሆን ይገባዋል። ጌታ ያዘዘውም ከእግሩ ስር ተምረው ስልጣንና ኃላፊነት በመስጠት ወደ ዓለም ለላካቸው ለደቀመዝሙርቱ ለሐዋርያት ነበር /ማቴ 28፤19/ በመጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ክፍሎች ሠዎች ከሩቅ ወደ ተሾሙት ሐዋርያት እየመጡ ይጠመቁ እንደ ነበርና ሐዋርያትም የተጣለባቸውን ኃላፊነት በሚገባ በማወቅ ማጥመቃቸው ተገልጾአል

34. መራሔ ድኅነት በብርሃኑ ገብና ገጽ 36 እና መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 3

እንጂ ያመነ ሁሉ የገዛ ቤተሰቡን አሊያም ሌላውን ሲያጠምቅ በመጽሐፍ ቅዱስ አናነብም::/ሐዋ 8፤12/

አጥማቂው ሰው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነና የወንጌልን እውነት የሚያስተምር ሰዎችንም ወደ ዘላለም መንግስት የሚያመጣ ሊሆን ያስፈልገዋል:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ስናነብ አጥማቂዎች ወንጌልን የሚሰብኩና ስለ ወንጌል መከራ የሚቀበሉ አማኞች ነበሩ:: /ሐዋ 2፤37-42፣ ዮሐ 3፤22/ የጌታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ትዝዛዝ «ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተ ማራችኋቸው» ይላል እንጂ በመዝፈቅ ሥራ ላይ ብቻ የተሰማሩ የወንጌልን መልእክት ማስተላለፍ ያልቻሉትን በፈጹም አያዛቸውም::/ ማቴ 28:19/

## <u>በማን</u> ስም ልንጠመቅ ይገባና<u>ል?</u>

ጌታ ራሱ «ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ... ደቀ መዝሙርቴ አድርጓቸው» ብሎ በሰጠው በስላሴ ስም መሰረት ጥምቀት ይከናወናል፤፤ /ማቴ 28፤19/ በአንዳንድ ክፍሎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የሚል እናገኛ ለን /ሐዋ 2፤38/ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መሞትንና መቀበርን / መተባበርን/ የሚያመለክት እንጂ የጥምቀት ስርዓት ማከናወኛ የትእዛዝ ስምን አያመለክትም::

## 4 ምስጢረ ቁርባን /የ<u>ጌታ እራት</u>/

ቁርባን የሚለው ቃል ከእብራይስጥ ቋንቋ የመጣ ነው:: ይህም «ቁርባን ማለት መቅረቢያ፣ መቀራረቢያ፣ መገናኛ ማለት ነው:: አማንያኑ ምስጋና ይዘው ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉ እግዚአብሔ ርም ስጦታውን በልጁ በተከፈለው ዋጋ በኩል በመቀበል ይቀርባል ::

ስለዚህ መቀራረቢያ፣ መገናኛ ተባለ[35] ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ለብዙ ቤዛ /ምትክ/ ሆኖ መቅረቡን ለሌላም ተላልፎ መሞቱን ያሳያል። በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር መቀራረባችንን ያመለክታል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት በተያዘበት ማታ ከደቀመዝሙርቱ ጋር እራት ሲበላ «እንጀራን አንስቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዝሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋየ ነው አለ ጽዋንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህ አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች በኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» አላቸው። /ማቴ 26፤26-28/ በዚህ ቃል መሰረት እንጀራው በመስቀል ላይ የተቆረሰውን የጌታ ሥጋ ምሳሌ ሲሆን ጽዋው ደግሞ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ያፈሰሰው የደሙ ምሳሌ ነው ።

«ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመስገነ ቆርሶም፤- እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋየ ነው ይህን ለመታሰቢያየ አድርጉት አለ፤፤ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንን ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪ መጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ» ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ ቁርባን የጌታን ሞት የምናስብበት ስርዓት እንደ ሆነ ገልጾአል።/1ኛቆሮ 11:23-26/

ደግሞም ቁርባን /የጌታ እራት / ከክርስቶስ ጋር ሕብረት እንዳለው እና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የመተባበር ምልክት እንደ ሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር «የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን ? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለ ሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለን በሥጋ የሆነውን እስራኤልን ተመልከቱ መስዋዕቱን የሚበሉ የመሰዊያው ማህበርተኞች አይደሉምን?» ይላል /1ኛቆሮ 10፤16-18/

35. የኢ.ኦ.ተ.ቤ. እምነትና ትምህርት በአባ መልከ ጸዴቅ ሊቀጳጳስ ገጽ 271

ቤተክርስቲያን ይህን የቁርባን ሥርዓት በማዘጋጀት ሁልጊዜ ሞቱን ትናገራለች:: ሕዝቡም ከአንድ ማዕድ ይቆርባል /ይካፈላል/:: ይህን ማዕድ ምእመናን በመቀበላቸው ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዓላማ ይረዳሉ ሕማሙን ሞቱን ያስባሉ :: አዳኝ እርሱ ብቻ የዘላለም ሕይወት እርሱ ብቻ እንደ ሆነ ያምናሉ፣ ይመሰክራሉም ::

## ቁርባን /የጌታ እራት / የምንወስደው ለምንድ ነው?

ቁርባንን /የጌታን እራት / የምንወስድበት ምክንያት

1. ክርስቶስ እንድንወስደው ትዕዛዝ ስለሰጠን /1ኛቆሮ11፤24/
2. የክርስቶስን ፍቅርና ያደረገልንን ሁሉ የምናስታውስበት ስለ ሆነ /1ኛቆሮ11:24-25/
3. በክርስቶስ ሞት ሕይወት እንዳገኘን በሰዎች ፊት ሞቱን የምንመነሰክርበት ስለሆነ /1ኛቆሮ11፤26 /
4. ክርስቶስ ዳግመኛ ተመልሶ እንደ ሚመጣ በጥልቅ የምናስብበትና የምንዘክርበት ጊዜ ስለሆነ ነው:: /1ኛቆሮ 11፤26 / በቅዳሴ ሠዓትም "ንዜኑ ሞተከ እግዚአ ወትንሣኤከ ቅድስተ - አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሳኤህን እንናገራለን" የሚለውም ይህን ቃል መሠረት ያደረገ ነው::

5.በሚታየው አገልግሎት የማይታይ ጸጋ ለማግኘት ይህም ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ጋር እንዲሁም ከክርስቲያኖች ጋር የበለጠ የመፈንስ የአንድነትና ፍቅርን ያስገኛል ወዘተ./1ቆሮ 10:16 1ቆሮ 11:20/

## ቁርባን /የጌታ እራት የሚወስዱ እነማን ናቸው?

ቁርባን ወይም የጌታ እራት መውሰድ የሚገባቸው

1. በጌታችን በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ያመኑ ሁሉ መቀበል ይገባቸዋል:: ላላመኑ ሰዎች ግን ምንም ትርጉም

ሊሰጣቸው አይችልም ላመኑት ግን "ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ" ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ተናገረ ሁሉም መውሰድ ይገባቸዋል /ማቴ 26፤27/

2. ሌላው ደግሞ የጌታን እራት /ቁርባን/ መውሰድ የሚችሉት በብርሃን የሚመላለሱ በቅድስና የሚኖሩ እንጂ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች አማኞች ጋር ያላቸውን ህብረት ያቋረጡ በእርኩሰት ህይወት ውስጥ ያሉ መውሰድ የለባቸውም ቢወስዱም ዕዳ ይቀበላሉ /1ኛቆሮ 11፤28፣ 1ኛዮሐ 1፤6/

## ቁርባን /የጌታ እራት/ መውሰድ ያለብን እንዴት ነው? /1ቆሮ 11፤28-31/


ሁላችንም ብቃት የሌለን ደካማ ሰዎች ነን ብቃታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሆነ "እኔ ብቁ ነኝ » የሚል ትዕቢት ወይም «እኔ ብቁ አይደለሁም» የሚል ፍርሃት እንዲኖረን አያስፈልግም። የጌታን እራት ከመውሰዳችን በፊት ራሳችንን በመመርመር ያልተናዘዝነው ኃጢአት እንዳለ መናዘዝና የእርስ በርስ ቂምም ካለ ማስወገድ ያስፈልጋል /1ቆሮ 11:28/ በልማድ እንደሚበላ ምግብ ሳይሆን በክብር የጌታን መከራ እያሰብን ከምስጋና ጋር መሆን አለበት /1ኛቆሮ 11፤29/ ምክንያቱም መልእክቱ ሊገባን የሚያስፈልግ ከመሆኑም ባሻገር ቅጣት ስላለው ነው /1ኛቆሮ 11፤30/

## <u>ቁርባን / የጌታ እራት /</u> እንዴት ይዘጋጅ ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፎ በሚሰጥባት ሌሊት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ከስንዴና ከወይን ተዘጋጅቶ ፋሲካን በማሰብ ይመገቡት የነበረውን ህብስትና ወይን አንስቶ ለመታሰቢያየ አድርጉት እንዳለ ከፍርሃትና ከክብር ጋር ከማያስከር ወይንና ከንጹህ ስንዴ ቢዘጋጅ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ነው።/ ሉቃ 22 :1-20/

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለጌታ እራት /ቁርባን/ የሚሆን ህብስት ከንጹህ ስንዴ ካዘጋጀች በኋላ የአቆራረሱ ሥርዓት (ሥርዓተ ፈትቶ ዘጽርስፎራ) ከዚህ በታች እንደተቀመጠው የክርስቶስን ማንነትና አገልግሎት በሚገልጽ ሁኔታ በአክብሮት ካህኑ እንዲቆርስ ታዛለች ::

## ሥርዓተ ፈትቶ ዘጽርስፎራ




## የሥዕሉ መግለጫ

1. ከ፡ ሀ - ሆ =ክርስቶስ ከሰማይ ወደምድር መውዱን (ርደት)
2. ከ፡ ለ - ሎ =ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ይሁዳ፣ ከይሁዳ ወደ
ገሊላ መመላለሱን፣ (አስተምህሮ)

3.ከ: መ - ሞ = ክርስቶስ 3 ዓመት ከ3 ወር ዙሮ ማስተማሩ (ዑደት)

4.ከ: ሠ - ሦ = ክርስቶስ ትኩስ ደሙንና ስጋውን ይዞ አሁን በአብ ዘንድ እንዲታይ /እንዲማልድ / ከምድር ወደ ሰማይ መውጣቱን ወይም ማረጉን (ዕርገት) ያመለክታል:: /ዕብ 9 :24 ዕብ7 :24-25 / ::

እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም ከምላክ መሆኑን ለመግለጽ ከላይ ወደ ታች መደረጉ መለኮት ያለመለወጥ ሰው መሆኑን: ከታችም ወደ ላይ መደረጉም ደግሞ ሥጋ ያለመለወጥ አምላክ መሆኑን ያስረዳል:: በመጀመሪያ ኅብስቱን ለሁለት እንዲነቃና-ታቹን ( ዘባኑን ) አይለይም:: ይህም ከሁለት ማንቃቱ የፍጹም መለኮትና የፍጹም ሰውነት (ትስብእት) ሁለት ባህሪን ሲገልጽ፣ ታቹን (ዘባኑን) አለመለየቱ የተዋህዶ ምሳሌ ነው::

በአጭሩ የዚህ ስርዓት ሚስጥር ዘወትር የምናመልከው የወደደንና ስለበደላችን የሞተልን ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርየ መኮቱና ባሕርየ ትስብእቱ ሳይቀላቀሉና ሳይጠፋፉ በተአቅቦ : ሳይለያዩ በተዋሕዶ ፀንቶ የሚኖር አንድ ጌታ መሆኑን የሚገልጽ ነው ::[35]

ይህ ከተዘጋጀ በኋላ ሁሉም የክርስቶስን ሞት በማሰብ በማያቋርጥ ዝማሬ ከፍርሃትና ከአክብሮት ጋር ይወስዱታል::

ይህም ስርዓት አንዳንድ አብያተክርስቲያናት የጌታን እራት ለማዘጋጀት ሲያስቡ ከገበያ ቦታ ዳቦና ለመጠጥ የተዘጋጀ የጠርሙስ ወይን ገዝቶ በትናንሽ ብልቃጥ ከዝማሬ ጋር ከማቅረብ ይልቅ በእጅጉ የሚሻል ይሆናል::

መጽሐፈ ቅዳሴ አዲስ አበባ 1918 ዓ.ም ገጽ 29 ዐምድ 2 እና ገጽ 127 ምዕራፍ 3::
መጽሐፍ ኪዳን አዲስ አበባ 1963 ዓ.ም ገጽ 21 ::
መጽሐፈ አሚን መ/ብ አድማሱ ጀንበሬ አዲስ አበባ 1954 ገጽ 227::

በዚህ አስተምህሮ ላይ የጥንት አባቶች ያላቸው እምነታዊ አቋም :-

"ጌታየ ናፍቆቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! በዚህ መቅደስ ቁርባን በሥጋ በደም መለኮትህ እንደተዋሐደው አውቃለሁ ። ይህንም ስላወቅኩ ከክብር ሁሉ ጋር የከበረ ሥጋህን ከሰማያዊ ክብሩ ሁሉ ጋር አከብራለሁ በዚህ በሚታየው ኅብስት መልክ እንድቀበል አምናለሁ። ከክብር ሁሉ የከበረ ደምህን ከሰማያዊ ክብሩ ሁሉ ጋር አከብራለሁ። በዚህ በሚታየው እንድቀበል አምናለሁ ስግደት የሚገባው ግሩም መለኮትህንም እንድቀበል በፍጹም ልብ አምናለሁ እንዲሁም ከሆን አንድ ቀን ፈጣሪየን ጠባቂየን፣ ፈራጄን ፣ መድሃኒቴን እቀበላሁ። ዳግመኛም ይህንን ቅዱስ ቁርባን በኅብስትና በወይን አካል እንዳገኘሁ አምናለሁ ኅብስትና ወይን ብቻ መሆን እንደ ሌለበትም አምናለሁ።

የዓለም ሁሉ ፈጣሪ በመንግስተ ሠማይ ኪሩቤል ሱራፌል የሚሰግዱልህ ንጉሠ ነገሥት አንተ ተሠውረህበት እንዳለህ አውቄ አምኜ እቀበልሃለሁ።

አምላኬ ሆይ! ይህ ቃል እንደ ተናገርከው ነውና፤፤ የአንተ ቃል ነው እንጅ የሌላ ቃል አይደለም ያንተ ቃል ስለ መሆኑ እናታችን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ሁሉ አምናለሁ እውነተኛ ምሥጢር አይደለም ለሚለኝ ነፍሴን ለሞት እሰጥበታለሁ።"[36]

## 5 ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን

ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን ማለት በአጭሩ ሙታን በዓለም መጨረሻ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምተው ነፍስና ሥጋቸው ተዋሕዶ ከመቃብር የሚነሱና እኩሉ ለዘላለም ህይወት እኩሉም ለዘላለም ኀሳር የሚያገኙ መሆናቸውን የሚነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ነው። ምሥጢር የተባለው ቃል ጽርጊቱ የመለኮታዊ ኃይልና ሥልጣን ተግባር በመሆኑና በተፈጥሮ አእምሯችን

36. የቂሳርያ ኤጲስቆጶስ ባስሊዮስ የውዳሴ አምላክ ድርሳን

በቀላሉ ለመረዳት ስለ ሚያዳግት ነው። ነገር ግን ሠው ከአፈር እንደ ተፈጠረ /ዘፍ 2:7/ እንዲሁ ወደ አፈር እንደ ሚመለስ /ዘፍ 2፤19፣ ዕብ 9:27/ ደግሞም የጌታን ድምፅ ሠምቶ እንደ ሚነሳና መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ክፋም ያደረጉ ለፍርድ እንደሚነሱ መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ ይናገራል/ዮሐ 5፤28-29/።

በብሉይ ኪዳን፡-

"በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ህይወት እኩሌቶቹም ወደ እረፍትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና ጥበበኞቹም እንደ ሠማይ ፀዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ፅድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ" /ዳን 12:1-3/

"ሙታንህ ህያዋን ይሆናሉ ሬሳዎችም ይነሣሉ በምድር የምትኖሩ ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩም" /ኢሳ 26፤19/

"መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም የምድርንም ፊት ታድሣለህ" /መዝ (104)፤30/ ተብሎ ተጽፏል።

<u>በሐዲስ ኪዳንም</u>፡-"በዚያን ቀን፡- ትንሳኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ ቀረቡ እንዲህም ብለው ጠየቁት፡- መምህር ሆይ ሙሴ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ አለ። ሰባት ወንድማማች በእኛ ዘንድ ነበሩ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ ዘርም ስለ ሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት እንዲሁ ደግሞ ሁለተኛው ሦስተኛውም እስከ ሰባተኛው ድረስ ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች ሁሉ አግብተዋታልና በትንሳኤ ቀንስ ከሰባቱ ለማንኛው ሚስት ትሆናለች? አሉት።ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ። በትንሳኤ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሠማይ ይሆናሉ እንጅ አያገቡም አይጋቡምም ስለ ትንሳኤ ሙታን ግን እኔ የአብርሃም አምላክ

የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም ሕዝቡም ይህን ሰምተው በትምህርቱ ተገረሙ» /ማቴ 22:29-33/

«በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፅን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደረጉ ለህይወት ትንሳኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ» /ዮሐ 5:28-29/

«በመጨረሻው ቀን በትንሳኤ እንዲነሳ አውቃለሁ አለችው» /ዮሐ 11:24/

«ባህርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፣ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ» /ራዕ 20፤13/

«ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሳ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ፤- ትንሳኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? ትንሳኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሳማ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፣ ደግሞም:- ክርስቶስን አስነስቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለመሰከርን ሃሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል:: ሙታን ግን የማይነሱ ከሆነ እርሱን አላስነሳውም ሙታን የማይነሱ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሳማ ፡ ክርስቶስም ካልተነሳ እምነታችሁ ከንቱ ናት እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ:: እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋላ:: በዚች ህይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን » /1ቆሮ 15፤12-19/ በማለት ትንሳኤ ሙታን የክርስትና መሰረታዊ የተስፋ ቃልና እምነት እንደሆነ አስረግጦ ይናገራል::

## የትንሳኤ ምልክት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!

"አሁኑ ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቶአል:: ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሳኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኗልና ሁሉ በአዳም እንደ ሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና::" በመቀጠልም ሐዋርያው ጳውሎስ ምስክርነቱን በአጽንኦት ሲናገር "እንዲያማ ካልሆነ ... እኛስ ዘወትር የሚያስፈራ ኑሮ የምንኖር ስለ ምንድን ነው? ወንድሞች ሆይ ዕለት ዕለት እሞታለሁ:: እንደ ሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር ከታገልኩ ሙታንስ የማይነሱ ከሆነ ምን ይጠቅመኛል" /1ቆሮ 15:20-32 / በማለት ያስረዳል:: ሐዋርያት ስለ እርሱና ስለወንጌል እውነት እሳትን መከራን ሳይሰቀቁ እስከ ሞት ድረስ ትንሳኤውን ያስተማሩትና ሞትን ያልፈሩበት ምክንያት እነርሱም የክርስቶስ ትንሳኤ ተካፋዮች እንደሚሆኑ ስላመኑ ነበር::/ ፊሊ 3:11 / ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ እንዲቀር መቃብሩን ቢያስጠብቁም እንኳ እንደ ተናገረው በሦስተኛው ቀን ተነስቶ መቃብሩን ባዶ አስቀርቶ የተቸነከሩ እጆቹንና በጦር የተወጋውን ጎኑን እያሳየ ለሐዋርያቱና ለተከታዮቹ ሁሉ ራሱን የገለጸላቸው በርካታ ትርጉም ቢኖረውም አንዱ ትንሳኤ ሙታን እንዳለ ምልክት ለመስጠት ነበርና ሠላም ለእናንተ ይሁን ብሎ አወጀላቸው::/ዮሐ 20:1-29፣ ሉቃ 24:1-32፣ማቴ 27:62፣ 28:1-10/

ይህ ደግሞ ለሐዋርያትና ለተከታዮቹ ታላቅ ደስታ ኃይል ነበር :: / ማቴ 28፤8 / ዓለምንና ሞትን በመናቅ ትንሳኤውንም በድፍረት አወጁ /ሐዋ 2:32/ ቢሆንላቸው እንካአ ወደ ትንሳኤ እንዲደርሱ በሞቱ እንዲመስሉት ተመኙ /ፊሊ 3:11/ ለእነርሱ ህይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነበር /ፊሊ 1:21/:: ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንካአ ሕያው ይሆናል ህያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም» በማለት ሙታን እንደ ሚነሱ አስረግጦ ተናግሯል /ዮሐ 11:25-26/ ነፍሱንም በተወ

ሠዓት መቃብሮች ተከፍተው ሞተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች እንደ ተነሱ ከትንሳኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎች እንደታዩና በርካታ ሰዎች ኢየሱስ በእውነት የእግቢአብሔር ልጅ እንደ ነበረ አይተው እንደፈሩ መጽሀፍ ቅዱስ ይናገራል /ማቴ 27፤51-54/

## ትንሳኤ ሙታን እንዴት ይፈጸማል

የሙታን የመነሳት ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ምሥጢር ይገልጽልናል "እነሆ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ አይን እንለወጣለን መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን" /1ኛቆሮ 15፤51-52/ መለከት ይነፋል ሲል የመለከታዊውን ትእዛዝ የሚያመለክት እንደ ሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። አልዓዛር የክርስቶስን ቃል ሰምቶ ወደ ውጭ እንደ ወጣ እንዲሁ ሙታን የጌታን ድምጽ ይሠማሉ። /ዮሐ 11:43-44/ "ድምፁን የሚሠሙበት ሠዓት ይመጣል" ተብሎም ተጽፏልና የመለከት መነፋት ይህን ያመለክታል /ዮሐ 5፤28/

ደግሞም ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና እኛ ህያዋን ሆነን ጌታ እስኪ መጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላዕክትም አለቃ ድምጽ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ" ይላቸዋል።

ደግሞም ሌላ ምሥጢር ሐዋርያው ጳውሎስ ስለትንሳኤ ሁኔታ አንድ ምሳሌና በትንሳኤ ጊዜ ምን ዓይነት ሥጋ እንደ ምንለብስ

ይገልጽልናል "ነገር ግን ሰው፡- ሙታን እንዴት ይነሳሉ? በምን ዓይነት አካል ይመጣሉ? የመል ይኖር ይሆናል ፡፡ አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ህያው አይሆንም፡፡ የምትዘራው ስንዴ ቢሆን ከሌላው ዓይነት የአንዱ ቢሆን ፣ ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም እግዚአብሔር ግን እንደወደደ አካልን ይሰጠዋል፡፡ ከዘሮችም ለእያንዳንዱ የገዛ አካሉን ይሰጠዋል ... የሙታን ትንሳኤ ደግሞ እንዲሁ ነው፡፡ በመበስበስ ይዘራል፣ ባለመበስበስ ይነሳል፣ በውርደት ይዘራል፣ በክብር ይነሳል፣ በድካም ይዘራል፣ በኃይል ይነሳል፣ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፣ መንፈሳዊ አካል ይነሣል፡፡ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ" /1ኛቆሮ 15፣35-44/ በአጭሩ እንደ ክርስቶስ ዓይነት ትንሣኤ ዘአካል ይዘን እንነሳለን ቃሉ እንዲህ ይላልና "ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" /ሮሜ 6፣5/፡፡ አንድ የጥንት የቤተ ክርስቲያኗ መጽሐፍ ከመቃብያን 3ኛ ክፍል ወስዶ የጻፈውን አቋም እንግለጽና ይህን ንዑስ ክፍል በሃይማኖት መግለጫ ርእስ ስር የቀ ረውን ነገረ-ትንሳኤ ደግመን በተጨማሪ ስለምናነሳው ለጊዜው እንጨርስ፡፡

<u>በዚህ</u> አስተምህሮ ላይ የጥንት አባቶች ያላቸው እምነታዊ አቋም ፡-

"ሙታን እንደ ሚነሱ ካላመንክ የሚቀጥለውን ቃል ስማ በሩካቤ ዘር ከእናት ከአባት የሚወለዱ ሳይሆን በክረምት ጊዜ ከውኃ የሚወለዱ ስንት ህዋሳቶች አሉ ... ሙታን ከፈረሱ ከበሰበሱ በኋላ አይነሱም የምትል አንተ ልበ ዕውር አስተውል አንተ ከእናት ከአባትህ ሳትወለድ እነርሱ በእግዚአብሔር መንፈስና በቃሉ ያለ እናት ያለ አባት ይወለዳሉ እንደሚወለዱ እወቅ ተረዳ አንተ አስተዋይ ልቡና አዋቂ አዕምሮ ያለህ ስትሆን ሙታን ከፈረሱ ከበሰበሱ በኋላ በፈጣሪያቸው በእግዚአብሔር ቃል አይነሱም ለምን ትላለህ? በል

ንስሐ ግባና ወደ ጥንተ እምነትህ ተመለስ ሞተው በመሬት ውስጥ አመድ ትቢያ የሆኑ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ ሕያዋን ሆነው ይነሣሉና፡፡ ለይኩን (ይሁን) ብሎ ሁሉንም በቃሉ ሲፈጥረው እምኀበ አልቦ ኀበቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ አምጥቶ እንደፈጠረው አሁንም በርሱ ጠለ-ምሕረት ማለት በርሱ ከሃሊነት ይነሳሉ ለይኩን ያለው ቃሉ ሁሉን ያጠቃልላልና፡፡ ስለዚህ እርሱ ባወቀና በፈቀደ ጊዜ ያስነሳቸዋልና ትንሳኤ ሙታን እንዳለ እመን፡፡ አንተም ከሞት ተነስተ ህ በፊቱ እንደ ምትቆም እወቅ፡፡ እንደ አስተሳሰብህ ሳትነሳ መቃብር ውስጥ ፈርሰህ በስብሰህ የምትቀር አይምሰልህ፡፡ አንተ እንደ ምትለውና እንደ ምታስበው ሳይሆን ከሙታን ተነስተህ እንደ ሥራህ አካአኋን ማለት በክፉ ስራህ ፋዳህን በመልካም ሥራህ ዋጋህን ትቀበላለህ"፡፡[37]

## 4.ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላላት የተለያየ የአገልግሎት ክፍሎች የምትጠቀምባቸው የተለያዩ የቤተክርስቲያኗ ስርዓቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ይባላሉ እነርሱም

ምሥጢረ ጥምቀት

ምሥጢረ ሜሮን

ምሥጢረ ቁርባን

ምስጢረ ክህነት

ምሥጢረ ተክሊል

ምሥጢረ ንስሐ

ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ምሥጢረ ጥምቀትን በገጽ 27 እና ምሥጢረ ቁርባንን በገጽ 28 የገለጽን ሲሆን በሌሎቹ ቀሪ ምስጢራት ዙሪያ ያላቸውን የጥንቱን መሠረታዊ እውነት ብቻ በማተኮር እናያለን፡፡

---

37. መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 26

## 1. ምሥጢረ ሜሮን

« ሜሮን » የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ «ቅዕባት» /ቅባት/ ማለት ነው ይህም ከጥምቀት ቀጥሎ መንፈስ ቅዱስን እንደ ተቀበልን በእምነት መወለዳችንን እና ለእግዚአብሔር የተለየን ሰዎች እንደ ሆንን ለማሳየት ቤተ ክርስቲያን የምትቀባው ቅባት ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ከገበያም ይሁን ከሌላ ስፍራ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚመጡትን ሰዎችም ይሁኑ ዕቃዎች ተቀብተው እንዲያገለግሉ እግዚአብሔር ደንግጎ ነበረ። ቅባቱም ከተለያዩ ሽቶነት ካላቸው እጽዋቶች ይቀመም ነበር / ዘጸ 30 :22-31 / የብሉይ ኪዳኑ ቅብዓት ሰዎችን ለእግዚአብሔር የተለዩ ለአገልግሎቱም የተመረጡና የተቀደሱ ብቻ ለማድረግ ሳይሆን ሁሉን የሚቀድሰው መንፈስ ቅዱስ በሐዲስ ኪዳን ለመሰጠቱም ጭምር ጥላነት ነበረው፤፤ይህንንም በኢሳያስ መጽሐፍ በምዕራፍ 61:1 «የእግዚአብሔር መንፈስ» ካለ በኀላ መልሶ «ቀብቶኛል» በማለት መንፈስ ቅዱስን በቅብዓት መስሎ ተናግሯል።

በሐዲስ ኪዳንም ደግሞ «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ ... እናንተስ ከእርሱ የተቀባችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም። ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉእንደ ሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ» እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተም እንዳስተ ማራችሁ በእርሱ ኑሩ» በማለት ሐዋርያው ዩሐንስም መንፈስ ቅዱስን «ቅዱሱ ቅባት» በማለት ይጠራዋል። /1ኛዮሐ 2:20-27/ እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን ቅባት በማለት ሲገልጸው «በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው። ደግሞም ያተመን የመንፈስንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው ።»ይላል ። /1ኛቆሮ 1፤21-22/

## በሚታየው ሥርዓት የማይታየው ጸጋ

በሚታየውም የቅብዓት ስርዓት የማይታየውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ስጦታ እንቀበላለን በማለት ቤተክርስቲያን ታምናለች:: ለምሳሌ ሳሙኤል በሳኦል ራስ ላይ የዘይት ብርሴ ወስዶ እንዳፈሰሰው ስናነብ /1ኛሳሙ 10 :1/ የነብያት መንፈስ በኃይል ወርዶበት ትንቢት እንደ ተናገረና ሠዎች ሁሉ «የቂስን ልጅ ምን ነካው? እርሱ ደግሞ ከነብያት ወገን ነውን» እንዳሉ በዚሁ በአንዱ ምዕራፍ ውስጥ እናገኛለን /1ኛሳሙ 10፤9-13/ እንዲሁም ሳኦል በእግዚአብሔር ፊት በተናቀ ጊዜ በቅባቱ አማካኝነት የተቀበለውን መንፈስ ቅዱስ እንደራቀበት ስናነብ በሚታው ቅባት የማይታየውን መንፈስ ቅዱስ እንደተቀበለ መረዳት ይቻላል :: /1ሳሙ 16:14/

ዳዊት ሳኦል ጠላቱ ሆኖ በተነሳበት ጊዜ በአጋጣሚ ሳኦል ሳያውቅ በዳዊት እጅ ሲወድቅና አብረውት የነበሩት ሃያላን እግዚአብሔር በእጅህ ጥሎልሀልና በሰይፍ ውደቅበት ቢሉት “እግዚአብሔር የቀባው ነውና እግዚአብሔር በቀባው በጌታየ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር አደርግ ዘንድ እጄንም እጥልበት ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው» በማለት ስለቅባቱ ይጠነቀቅለት እንደ ነበር ተገልጾአል ይህም በሚታየው ቅባት የማይታየውን መንፈስ ቅዱስን እንደ ተቀበለ ዳዊት በሚገባ ተረድቶ ነበር ማለት እንችላለን::/1ኛሳሙ 24፤6/ ራሱ ዳዊት ዘይቱን ከተቀባ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ከዚያ ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል እንደ መጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል /1ሳሙ 16:13/::

እንዲሁም በብሉይ ኪዳን እንደነበረው ሁሉ በሐዲስ ኪዳንም መንፈስ ቅዱስ በኃይልና ስጋ በለበሰው ሁሉ ላይ ወርዶ የሚሠራበት ዘመን ሐዋርያት የግድ ባይሆንም እንኳ ብዙ ጊዜ በቅባት ሳይሆን እጅ

በመጫን መንፈስ ቅዱስን ይሰጡ ነበር::ለምሳሌ :-

«ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው» /ሐዋ 19፤5-6/

«በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ» /ሐዋ 8፤17/

«ስለዚህ ምክንያት እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጆቼን መጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ» /2ኛጢሞ 1:6/ አንድ መጽሐፍ እንዲህ ይላል «በጥንት ስብከት ምዕመናን ገና ባልበዙበት ወቅት ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በምዕመናን ላይ ያሳድሩ የነበሩት በአንብሮተ እድ /እጅን በመጫን/ ነበረ:: ዳሩ ግን የምዕመናን ቁጥር ዕለት በዕለት እየጨመ ረና እጅን በመጫን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ማሳደር አድካሚና ሁሉንም ለማዳረስ የማይቻል ሆኖ በመገኘቱ በአንብሮተ እድ ፋንታ በቅብዓ ሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ማሳደር አማራጭ የሌለው ሆኖ ተገኘ:: ስለዚህ ከሐዋርያት በኋላ የተነሱ የቤተክርስቲያን አባቶች ካጠመቁ በኋላ ሜሮን በመቀባት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ማሳደር ጀመሩ::»[38]

በአሁኑ ጊዜ በተለየ መልኩ በቤተክርስቲያናችን ስርዓት መሰረት የሜሮን ቅባት የሚቀቡት በቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ ሥልጣን የሚያገኙት የሃይማኖት አባቶች ናቸው::

## 2. ምሥጢረ ቀንዲል

«ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር፤፤ ከእናንተ ዺታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም

---

38. መርሐ ደኅነት በብርሃኑ ጎበና ገጽ 76

እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ፡ ጌታም ያስነሳዋል፡ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰ ረይለታል» /ያዕ 5፤13-15/።

በዚህ ቃል መሠረት ለበሽተኞች እየተጸለየላቸው የሚቀቡት የቅባት ስርዓት ምሥጢረ ቀንዲል ተብሎ ይታወቃል። «ቀንዲል» የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ «በዘይት የሚበራ መብራት ወይም ማብሪያ» ማለት ሲሆን ሥርዓተ ጸሎቱ ሲፈጸም በታመመው ሰው አጠገብ የሚበራውን መብራት ያመለክታል። ይህም መብራት የመዳን ተስፋን ለማሳየት የሚደረግ ነው።

ሐዋርያት በበሽተኞች ላይ ዘይት እየቀቡ ይፈውሱ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር:- «አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠራ ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀመር፣ በእርኩሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሠጣቸው፣ ... ወጥተውም ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ፣ ብዙ አጋንንትንም አወጡ፣ ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው» ይላል ። /ማር 6፤7 እና 12-13/ ደግሞም ክርስቶስ ስለ መልካም ባልንጀርነት በተናገ ረው ምሳሌ ውስጥ ለበሽተኛው /ለቆሰለው ሰው/ ዘይት ቀብቶ እንደ ረዳው ሲገልጽ "አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወርዶ በወንበዴ ዎችም እጅ ወደቀ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሔዱ ... አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቁስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው በራሱም አህያ ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደሪያ ወሰደው ጠበቀውም» ይላል / ሉቃ 10፤30-34 / ።
እንደጥንቱ የቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ ብዙም አገልግሎቱ ቢቀንስም ዛሬም ቤተክርስቲያናችን ይህን ሥርዓት በመከተል የሐይማኖት አባቶች የታመሙትን ምዕመናን በመጠየቅና ጸሎት በማድረስ ቅብዓ ቅዱስን በመቀባት ከስጋ ደዌያቸው እንዲፈወሱ

እግዚአብሔርን የሚለምኑ አባቶች ይኖራሉ። ምክንያቱም «ድውዮችን ፈወሱ» በማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ይህን ኃላፊነት ሰጥቷታል በማለት ያምናሉና።

## በሚታየው ሥርዓት የማይታየው ጸጋ

የቀንዲል ሥርዓተ - ቅብዓት በሚታይ አፈጻጸም /ዘይት አቀባብ/ የማይታየውን የእግዚአብሔርን ማዳን መቀበልን እንደሚያስገኝ ቤተክርስቲያን ታምናለች።«ድውዩም ይድናል ...ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል» ሲባል የድውይን ወይም የበሽታውን መዳን በበሽተኛው ላይ የሚታይ ሲሆን የማይታየው ደግሞ ምህረት ወይም የኃጢአትን ስርየት ማግኘት እንደሆነ ሐዋርያው ያዕቆብ ያስተምረናል ። /ያዕ 5፤15/ ደግሞም ጴጥሮስ በ1ኛጴጥ 4:2 «በሥጋ መከራን የተቀበለ ኃጢአትን ትቷልና» ሲል ኃጢአትን የማስተው ተግባር የመንፈስ ቅዱስ ድርጊት ብቻ ሲሆን ይህም አሰራር ደግሞ ማንም በስጋ አይኑ ሊያየው እንደማይችል መረዳት ይቻላል። በስጋ መከርን መቀበል ደግሞ በዓይን ሊታይ የሚችል ነገር ነው።

እንግዲህ ከምንግዜዉም በበለጠ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት ህመምተ ኞችን መደገፍ ስለእነርሱ መጸለይ የሚያስፈልግበት ወቅት ከመሆኑም በተጨማሪ የቤተክርስቲያን ከፍተኛ ተግባሯ ሊሆን ይገባል ። ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበ ረበት ወቀት ህመምተኞችን በመጠየቅና በመፈወስ ይዞር እንደነበ ረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል /ማቴ 9:35/ ።ከዚህም በላይ የህዝቡን ሁሉ በሽታና ሃጢያት በመሸከም የራሱ እንዳደረገው « በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ህመማችንን ተሸክሟል » ተብሎ ተጽፏል ። /ኢሳ 53:4/ ።

እንግዲህ ይህንን አገልግሎት በመጀመሪያ ለሐዋርያት ቀጥሎም ለቤተክርስስቲያን ሰጥቶት ሄዳል :: በመጨረሻው ሰዓት በክብር ለፍርድ ሲመጣ ለህመምተኞች የሚጸልዩትን «የአባቴ ብሩካን» ብሎ ይጠራቸዋል ::ምክንያቱም «ታምሜ ጠይቃችሁኛልና» ይላል /ማቴ 25፤34-36/ ::

## ይህን ሥርዓት የሚፈጽመው ማነው?

«የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት» /ያዕ 5፤14/ በማለቱ በሽተኛው የቤተክርስቲያንን መሪዎች በመጥራት እንዲጸልዩለት ማድረግ አለበት:: ይህም የሆነበት ምክንያት ኃጢአቱን እንዲናዘዝና ቤተ ክርስቲያንን ይቅርታ ጠይቆ ህብረቱን እንዳያስተካከል ነው:: ያን ጊዜ ም ከኃጢአቱ ይሠረያል::

ይህ በሽታ አይነት በተደጋጋሚ ኃጢአት በማድረጉ ምክንያት የመጣ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደ ሆነ ክፍሉ ስለ ሚናገር መናዘዝና ቤተክርስቲያንን እንደ በደለ ለመግለጽ የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች መጥራት ይገባዋል እነርሱም በማንም ስም ሳይሆን «በጌታ ስም» ይጸልዩለታል: ኃጢአቱም ትፈወሳለች /ያዕ 5:16/::

## 3. ምሥጢረ ክህነት

ይህ ምሥጢረ ክህነት በአሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ለውጥ ያለው ይመስላል ምክንያቱም ክህነት አሰጣጡ ከወንጌል ጋር ያልተያያዙ መጽሐፍት መሽምደድና ስርዓተ አፈጻጸሙን በማወቅ የሚሰጥ ሰፊ ተግባር እየሆነ በመምጣቱ ነው:: ይሁን እንጂ የአገልግሎቱ ክፍል ህዝቡን ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ የማስተማር የመምከር የመጸለይ ሐላፊነትን ያካተተ አገልግሎት እንደ ሆነ ደብዛው አልጠፋም:፤ ነገር ግን ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደ ተናገረው ከጨለማ

ወደ ሚደነቅ ብርሃን የተጠሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ካህናት ናቸው ። /1ኛጴጥ 2፤9-10/። ደግሞም በክርስቶስ የሚያምንና ኃጢአቱም በክርስቶስ ደም የታጠበ ሁሉ ካህን እንደ ሆነ ዮሐንስም ይነግረናል / ራዕ 1፤6/። በሌላ ክፍልም ራሳቸውን መንፈሳዊ መስዋዕት አድርገው የሚያቀርቡም ካህናት ተብለዋል /1ኛጴጥ 2፤5/ ካህን ማለት አገልጋይ ማለት ነው። ይህም የክህነት አገልግሎት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለን አገልግሎት የሚገልጽ ነው። የእግዚአብሔር ቃልና በረከት ወደ ህዝቡ የህዝቡንም በደልና ኃጢአት /ሸክም/ ወደ እግዚአብሔር የማቅረብ ተግባር በቤተክርስቲያናችን ያለ ተግባር ነው። ይህም ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ዘመን የክርስቲያን ሁሉ ተግባር ይመስላል። ይሁን እንጂ በቤተክርስቲያን የሥልጣን ተዋረድና የስራ ድርሻ እንዳለ አይዘነጋም ከዲቁና እስከ ጵጵስና ድረስ ሁሉም እንደ ጸጋውና ቤተክርስቲያን እንደ ምትሰጠው ኃላፊነት ሊያገለግል ይችላል ይህም ሊሆን የሚችለው መመዘኛው ቃሉን ማወቅና መኖሩ ላይ ሊሆን ይገባል /1ጢሞ 3:1-13/ ።

ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ካህን ሳይሆን ሊቀ ካህናችን ነው /ዕብ 3:1/ ዛሬም የሁላችንም ሊቀ ካህን ሲሆን በእውነተኛይቱ ድንካአን ሊያገለግል ቀዳሚ ሆኖ ወደ ሰማይ እንደ ገባና በአብ ቀኝ እንደ እንደተቀመጠ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል /ዕብ 4፤14፣ ዕብ 6፤20፣ ዕብ 8:1-3/

## 4. ምሥጢረ ተክሊል

ምሥጢረ ተክሊል ማለት የሙሽራውና የሙሽራይቱ የጋብቻ ቃል ኪዳን በቤተክርስቲያን የሚጸናበትና የጋብቻ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸውን ፣ በፍቅር የሚተሳሰሩበትን ዘላቂ

አንድነትን የሚያገኙበት ሥርዓት ነው "ተክሊል ተከለለ ዘውድ ተ ቀዳጀ የሚል ዘር ሲሆን የአረቦን ክብር የተቀበለ ለማለት የሙሽራውና የሙሽራይቱ ራስ ላይ የሚጸፈውን የአረቦን አክሊል በመመልከት የወጣም ስም ይመስላል"[39] ይህም ሙሽራውና ሙሽራት ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደደበትንና የተቆራኘበትን ያህል አንድ እንዲሆኑና እንደተሳሳሩ ለመግለጽ ምሥጢር የሚለውን ስያሜ አግኝቷል ::መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና:-"ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደ ምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና፤፤ ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደ ምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ፡፤ ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጠ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነውር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ:: እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ስጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባቸዋል፤፤ የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል:: ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለ ሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል ይንከባከበውማል፤፤ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው" /ኤፌ 5፤22-32/::

ይህ ክፍል ባል ከሚስቱ ጋር ክርስቶስ ከቤተክርስቲያን ጋር መጣበቅ አንድ ሥጋ መሆን መቻል ታላቅ መለኮታዊ ምሥጢር ስለ

---

39. የኢ.ኦ.ተ.ቤ. እምነትና ትምህርት ከአባ መልከ ጸዴቅ ሊቀጳጳስ ገጽ 289

ሆነ ምሥጢር እንዲሆን ይገልጻል፡፡ የተባረከ ቤተሰብ ማለት ባል ሚስቱን የሚወድ ሚስት ለባሏ የምትገዛ ልጅ ለወላጆቹ የሚታዘዝበትና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሲሆን ነው፡፡ ይህ የሚመጣው ደግሞ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ሲኖረው ብቻ ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገውና ክብሩን የገለጠው በሠርግ ቤት በመገኘት ነበር /ዮሐ 2፤1-11/ በአገልግሎቱም በርካታ ጊዜ ስለ ጋብቻ አስተ ምሯል፡፡ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት ብቻ እንደሚመሠረት / ማቴ 19፤4-5/ በጋብቻ ውስጥ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት እንደማይገባ / ማቴ 19፤5/ ባልና ሚስት አንድ አካል መሆን እንዳለባቸው : /ማቴ 19፤6/ ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነትና መመኘት ኃጢአት ስለ መሆኑ / ማቴ19፤9፣ ማቴ 5፤27-30/ ስለ ፍች መከልከል /ማቴ 19፤6-8/ ከጥንትም ትምህርት እንደነበረ /ዘፍ 1፤27፣ ዘፍ 2:2:24፣ ዘዳ 24:1/ በሚገባ ጌታችን አስተምሯል ፡፡ በመሆኑም « ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» በማለት የጋብቻ መስራች ራሱ እግዚአብሔር ነውና ሔዋንን ፈጠረ፡፡ /ዘፍ 2:18-25 / ስለዚህ ጋብቻ የእግዚአብሔር እቅድ እንጂ ሠው ፈልጎት የፈጠረው አይደለም፡፡ እቅዱም ቅዱስ ጋብቻ ነውርም የሌለበት አድርጎ ሰርቶታል፡፡ /ዕብ 13:4/ የጋብቻ ዓላማው ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ሠው በማንነቱ ጎደሎ በመሆኑ ሙሉ ለመሆን /ዘፍ 2:21/ ከዚያም ሃላፊነትን በትክክል ለመወጣት /ዘፍ 1፤26/ እንዲሁም ዘር ለመተካት ያስችል ዘንድ ነው /ዘፍ 1፤28/፡፡ይህ ደግሞ ድንቅ ምስጢር ነው፡፡

## 5. ምሥጢረ ንስሐ

« ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም::» /1ኛዮሐ 1፤8/ በሚለው ቃል መሠረት ሠው ሁሉ በኃጢአት በየቀኑ ሊበከል ይችላል:: « ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜ ይነሳል» /ምሳ 24:16/ ተብሎ እንደ ተጻፈ ክርስቲያን ሊወድቅ ቢችልም በዚያው በኃጢአቱ ገፍቶና ተደላድሎ አይኖርበትም ከወደቀበት ይነሳል::ደግሞም ክርስቲያን በአላማ ሁሉጊዜ በደልንም በማሰብ ሊያደርግ አይችልም:: /1ኛየሐ 3:6/ ካልተሳሳተ በቀር:: ለመሳሳቱ ደግሞ መናዘዝና ሃጢያትን መተው መፍትሄው ነው::ምክንያቱም ቃሉ «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛልና » ይላል :: /ምሳ 28:13/::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ሠዓት የንስሃን ጥሪ ያስተጋባ ነበር /ማቴ 4፤17/:: ምክንያቱም እግዚአብሔር መፍቀሬ ሰብእ /ሰው ወዳጅ/ ነውና "ንስሐ ግቡ ሐጢያትም እንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ተመለሱ ... የእስራኤል ቤት ሆይ ስለምን ትሞታላችሁ የሟቹን ሞት አልፈቅድምና ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ"ይላል/ህዝ 18፤30-32/

በመሆኑም «ንስሐ» እግዚአብሔር ከሰጠው ዳግም እድል መካከል ዋነኛውና አንዱ ጸጋ ነው:: አንድ ሰው በደለኛ ከሆነና በኃጢአቱ መኖር ከወሰነ ለራሱም ለቤተክርስቲያን ማህበረሰብም እንዲሁም በውጭ ላሉት ለአገሪቱ ህዝብም እንካአ ከፍተኛ ኪሳራን ያስከትላል፤፤ ለምሳሌ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አካን እርም ከሆነው ነገር በመውሰዱ የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ልጆች ሁሉ ላይ ነደደ ሰላሳ ስድስት የእስራኤል ሃያላን እንደተራ፡ የእግዚአብሔር ሃይልእንደሌላቸው ሆነው ወደቁ::በጠላቶቻቸው ፊት በርካቶቹም ሸሹ በዚህም ምክንያት የህዝቡ ልብ ቀለጠ እንደ ውኃም ሆነ::

ኢያሱም ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር ሆኖ እስከ ማታ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት በግንባሩ ተደፍቶ ቢጠይቅ እግዚአብሔር ኢያሱን « ለምን በግንባርህ ተደፍተሃል? ቁም እስራኤል በድሏል ያዘዝን ቸውንም ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋል እርም የሆነውንም ነገር ወሰዱ ሰ ረቁም ዋሹም በዕቃቸውም ውስጥ ሸሸጉት። ስለዚህም የእስራኤል ልጆች በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም የተረገሙ ስለሆኑ በጠላቶቻቸው ፊት ይሸሻሉ እርም የሆነውንም ነገር ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም ተነሣና ህዝቡን ቀድስ» አለው ። እንግዲህ የአካን ኃጢአት በእግዚአብሔር ህዝብ መካከል ከፍተኛ ኪሳራ ራዕዩም እንዲዘገይ የህዝቡም ልብ እንዲፈራ ምክንያት ሆኗል ። ይህም እርም አካንን ከነቤተሰቡ የሞት ፍርድ አስፈረደበት። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ሆኖ ራዕዩ ወደ ፍጻሜ መገስገስ ጀመረ ጠላቶቻቸውንም በቀላሉ ማሸነፍ ቻሉ / ኢያሱ 7 /። ከዚህ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ኃጢአት ግለሰቡን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ህዝብና ራዕይ ምን ያህል እንደ ሚፈታተን ያስረዳናል ። በበርካታ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም ይህን የመሳሰሉት ትምህርታዊ እውነታዎች ተጽፏል /መሳ 4:1-3፣ መሳ 6:1፣ ዘኍ 25፤1-13፣ 2ሳሙ 24-1-25/፡፤በመሆኑም እግዚአብሔር ንስሐ ግቡ ኃጢአትም እንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ያለው ለዚሁ ምክንያት ነበ ረ ። /ሕዝ 18፤30/ ስለሆነም የአንድ ሰው በደል በርካታ ነገሮችን ስለሚጎዳ የቤተክርስቲያን አባላት «እርስ በእርሳቸው ሊተያዩ ይገባቸዋል። ሐዋርያው ያዕቆብ «በኃ ቢአታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ» ብሏል /ያዕ 1፤16 / ደግሞ መከፋፋት ቂም በደል እንዳይኖር በንስሐ ሰዎች እንዲመለሱ «ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና ፡ለሰዎች ግን ኃጢአታችሁን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም» በማለት ስለ መቻቻልና ስለ ፍቅር

መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል /ማቴ 6፤14-15፣ ሮሜ 12፤14-21/፡፡

እንግዲህ ንስሃ ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅበት ከሞት ወደ ህይወት ከጨለማ ኑሮ ወደ ብርሃን ኑሮ የምንሸጋገርበት ረቂቅ ምሥጢር ነች፡፡ እዚህ በምድር ላይ አንድ ሰው ንስሐ ቢገባና ከኃጢቱ ቢመለስ በሰማይ ያሉ ሰራዊተ መላእክት እንካአ ሳይቀሩ ይደሰታሉ «እላችኋለሁ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል»ተብሎ ተጽፏልና፡፡ /ሉቃ 15፤10/፡፡

ነገር ግን ንስሐ ባለመግባት የህይወቱን ለውጥ ለማድረግ ለማይፈልግ ክርስቲያን ቢኖር ግን ቤተክርቲያን ልትፈርድበት ከጉባኤ ውም እስከ መለየት ልታደርስው ይችላል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዝሙት የተከሰሰውን የቆሮንቶስ ሰው «እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጀበታለሁ፣ ... መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለስጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዬ ነው» በማለት በሥጋው እንዲቀጣ አድርጓል /1ኛቆሮ 5፡1-5/፡፡ ደግሞም ኃጢአተኛው ቅጣቱ በቅቶት ንስሐ ገብቶና ተቃንቶ ከተመለሰ ቤተክርቲያን በእልልታ እንደቀራጭ ሳይሆን እንደ ወንድም ትቀበለዋለች ሐዋርያው ጳውሎስ ለሁለተኛ ጊዜ በጻፈው መልዕክቱ ከላይ የፈረደበትን ሰው ቅጣቱ የሚበቃው በመሆኑ ክርስቲያኑ ህብረተሰብ ይቅርታ እንዲያደርግለት «እንደዚህ ላለ ሰው ይህ ከእናንተ የሚበዙት የቀጣችሁት ቅጣት ይበቃዋልና እንደዚህ ላለው ከልክ በሚበዛ ኃዘን እንዳይዋጥ ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል፡ ስለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ እለምናችኋለሁ ስለዚህ ደግሞ ጽፌ ነበርና»በማለት ጠይቋል፡፡/2ኛቆሮ 2፤6-9/ በመሆኑም የቤተክርስቲያን መሪዎችም ሆኑ እያንዳንዱ ክርስቲያን ኃጢአትን የመጸየፍና በቅድስና የመኖር ቁርጥ አቋም አላቸው፡፡ምክንያቱም የሚያገለግሉና የሚያመልኩት ጌታ ኃጢአትን የሚጠላ ኃጢያተኞችንም ከቶ የማያነጻ ቅዱስ

አምላክ ስለሆነ ነው /ዘኅ 14፤18/ ደግሞ እርሱ ራሱ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ብሎ አዟል /ዘሌ 19:2/ ሐዋርያው ጴጥሮስም ይህን ይዞ «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ቅዱሳን ሁኑ» ብሏል /1ኛጴጥ 1:15/:: ምክንያቱም ያለ ቅድስና ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና ነው /ዕብ 12:14/ በአጠቃላይ ክርስቶስ ራሱን የሰጠላት ቤተክርስቲያን እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነውር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነች ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ስለሚፈልግ /ኤፌ 5:27/ የቤተክርቲያን መሪዎችና የክርስቲያን ማህበረሰብ ሁሉ ኃጢአትን ሊዋጉትና ከኃጢአቱ ጋርም ለመኖር ለወሰነም ግለሰብ የማሰርና ደግሞም ከተመለሰ የመፍታት ስልጣን ለእያንዳንዱ ክርስቲያን በነፍስ ወከፍ በጌታ ዘንድ ስልጣን ተሰጥቶታል /ማቴ 18:15-20/እንግዲህ ንስሐ በሚታይ የእርስ በርስ ኃጢአት የመናዘዝ ስርዓት የማይታየውን የእግዚአብሔርን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ስለሚያስገኝ ምሥጢረ ነገሩን ለመግለጽ ምሥጢረ ንስሐ ተብሏል::

## 5.ሥርዓተ አምልኮና አስተዳደራዊ አደረጃጀት

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ በሁለት ዓበይት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ይህም በቤተ መቅደስ በሚመራ የቅዳሴ ስርዓትና በቅኔ ማህሌት ውስጥ በያሬዳዊ ዜማ እግዚአብሔር የሚመሠገንበት ሥርዓት ነው:: ከእነዚህ ከሁለቱ ውጭም በአውደ ምህረት የጸሎት የዝማሬ፣ የስብከት ስርዓት ሲካሄድ በሠንበት ትምህርት ቤትም የመዝሙርና የስብከት አገልግሎትም ይከናወናል:: የጥምቀት: የልደት የስቅለት እና የመሳሰሉት በአላት እንዲሁም የጋብቻና የሞት ጊዜም አነስተኛ የአምልኮና የጸሎት ስአቶች

በአደባባይ የሚከናወንበትም ጊዜ አለ።

በተለይ የቅዳሴ ሥርዓት የቤተክርስቲያኗ የአምልኮ ዋና ስርዓት ሆኖ ጎልቶ ይታያል። ቅዳሴ ማለት ምስጋና ማለት ሲሆን ስርዓተ ቅዳሴ ማለት ደግሞ የምስጋና ስርዓት ማለት ነው ። የቅዳሴ ስርዓቱ በውስጡ በርካታ የጸሎት ርዕሶችንና ሥርዓቶችን ያካተተ ነው።

በዚህ በቅዳሴ ክፍለ ጊዜ የኅብረት ጸሎት የሚካሄድበት ስለሆነ ይበል ካህን (ካህኑ ይበል)፣ ይበል ዲያቆን (ዲያቆን ይበል) ፣ ይበሉ ሕዝብ (ሕዝቡ ይበል) የሚሉ የቅብብሎሽ ምስጋና ሲሆን ዛሬ በፕሮቴስታንቱ የአምልኮ ሁኔታ እንደ ሚታየው ዓይነት አስመላኪ መሪና አምላኪ ህዝብ ወይም ፕሮግራም መሪዎችና ተከታዮች እንደሚለው ዓይነት ተመሳሳይ አካሄድ አለበት ። በእርግጥ በዛሬው ጊዜ ስርዓተ አምልኮው መሪው ካህንና ተቀባዩ ህዝብ በጥሞና እየተ ቀባበሉ ማመስገን እየቀረ ቀዳሽና አስቀዳሽ እየሆነ የሄደ ይመስላል ። ለዚህም ምክንያቱ በአብዛሀኛው ጊዜ ሥርአቱ በግእዝ ስለሚመራ ለቋንቋው በርካታ ህዝብ ባዳ ከመሆኑ የተነሳ በዝምታ የተዋጠ ነው ። ይህን በተመለከተ በቁጥር ሁለት መጽሀፍ የተዳሰሰ በመሆኑ ለአንባቢ እያመለከትን በዚህ ርዕስ ስር ግን ቅዳሴው መሠረታዊው ሀሳቡና አካሄዱ መልካም ነው ማለት ይቻላል።

ጸሎተ ቅዳሴው በ3 ታላላቅ ክፍሎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ግብዓተ መንጦላዕት /የዝግጅት ቅዳሴ/ ሲባል ሁለተኛው የትምህርት /የንባብ/ ቅዳሴ ይባላል። ሦስተኛው ደግሞ ፍሬ ቅዳሴ ይባላል። የመጀመሪያው ግብዓተ መንጠላዕት የዕለቱ ቀዳሽ ካህን መቅደስ ውስጥ እንደ ገባ ከመጋረጃ ውጭ አንድ ጊዜ መጋረጃውን አልፎ ሦስት ጊዜ ይሰግድና ካህናቱንና ዲያቆናቱን ሠላምታ ከሰጠ በኋላ በጸሎት እንዲያስቡት ይነግራል። ከዚያም ልብሰ ተ ክህኖውን ባርኮ ይለብስና ሁሉ አገልጋዮቹን ወክሎ «አ እንተየ ሀሉ በዝንቱ ልቡና ...»ሲል ጀምሮ የንስሐ ጸሎት ይጸልያል

በርካታ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎችን ለምሳሌ መዝሙር 24(25) ኀቤከ እግዚኦ አንቃዕደኩ "የሚለውን፣ 66(67)» ስምዓኒ አምላኪየ ስእለትየ የሚለውን፣ 101(102) ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ ..." ወዘተ የሚለውን ይጸልያል (ይደግማል) ከዚህ በኋላ "እግዚአብሔር አምላክነ አንተ ውእቱ ባሕቲትከ ቅዱስ" ከሚለው ጀምሮ በንዋየ ቅዱሳቱ ላይ ጸልዮ እስከ ሁለተኛው ክፍል /ጸኡ ንዑሰ ክርስቲያን እስከ ሚለው ድረስ/ ይቀጥላል:: ይህ ከላይ ያነበብነው የግእዝ ቃል በተጠቀሱት የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎች የምዕራፎቹ የመጀመሪያ ቁጥሮች ሲሆኑ ሌላው ደግሞ ከመጽሀፈ ቅዳሴ የተጠቀሰ ነው ::

በሁለታኛው ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት የሚቀርቡበትና የወንጌል ትምህርት የሚሰጥበት በጋራ በቅብብሎሽ ስርዓተ ቅዳሴው የሚከናወንበት ነው :: «አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» አንዱ አብ ቅዱስ ነው : አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው : መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ቅዱስ ነው: በማለት ተጀምሮ ጸሎተ አኩተት /የምስጋና ጸሎት/ እና ለቤተክርስቲያኑ የጡዋፍ፣ የሻማ፣ የዕጣን፣ የዘቢብ፣ የዘይት፣ ያልባሳት መጽሐፍትና ልዩ ልዩ ንዋየ ቅዱሳት ይዘው ለሚመጡ ጸሎት (ጸሎተ መባዕ) ተደርጎላቸው ስለተዘጋጀው ህብስትና ወይን ጸሎት /ጸሎተ እንፎራ/ ተደርሶ ለህዝቡ ሁሉ ከእግዚአብሔር ምህረት እየጠየቀ ጸሎተ ፍትሐት ዘወልድ ይደ ረሳል:: ከዚህ በኋላ ከሃዲስ ኪዳን /መጽሐፍ ቅዱስ/ ተነበና ጸሎተ ኪዳንና ጸሎተ ወንጌል ተደርሶ ለሕዝብ ሁሉ ጸሎት /ጸዋትው/ ተ ደርጎ በመጨረሻም የሃይማኖት መግለጫ ተብሎ ጸሎተ አምኅ ቅድሳት አድርጎ ዲያቆኑ «ጸልዩ በእንተ ሰላም ፍጽምት ወፍቅር ተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት- በፍጹም ፍቅር በፍጹም ሰላም ሰላም ተባባሉ ብሎ ያዝና የፍቅርና የሰላምታ እጅ መንሣት ተደርጎ» ሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ይጠናቀቃል ::

ቀጥሎ ሦስተኛው ክፍለ ጊዜ ፍሬ ቅዳሴ ነው ። ይህም ስለተ ዘጋጀው ህብስትና ወይን እንዲሁም የቡራኬ ጸሎት የሚደረግበት ነው።

በአሁኑ ጊዜ በቤተክርትቲያኗ ዐሥራ አራት ዓበይት ቅዳሴ ዎች አሉ ። እነርሱም ቅዳሴ እግዚእ፣ ቅዳሴ ዘጎርጎሪዮስ፣ ቅዳሴ ማርያም፣ ቅዳሴ ዘቄርሎስ፣ ቅዳሴ ዘአትናቴዎስ፣ ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምዕት፣ ቅዳሴ ዘዲዮስቆሮስ፣ ቅዳሴ ዘባስሊዮስ፣ ቅዳሴ ዘያዕቆብ ዘሥሩግ፣ ቅዳሴ ዘዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዳሴ ዘኤጳፋንዮስ፣ ቅዳሴ ዘዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ፣ ቅዳሴ ዘጎርጎሪዮስ ካልዕ እና ቅዳሴ ዘሐዋርያት ናቸው።

በእርግጥ አብዛሀኛዎቹ መልካም መልእክት የሚኖራቸው ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በርካታ መለኮታዊ የአስተምህሮ ተፋልሶ በውስጣቸው ይገኝባቸዋል ይህን ደግሞ በሁለተኛ መጽሐፋችን አስቀምጠናል ። ነገር ግን ቅዳሴ ዘሐዋርያት ከሁሉ ጥንታዊ በመሆኑ ቅዳሴው «ነአኩተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ - በተ ወደደ ልጅህ ጌታ ሆይ እናመሰግንሃለን» በማለት በወልድ መንገድነት ምስጋና ያደርሳል። ይህ ቅዳሴ በምስጋና የተሞላና ከሌሎቹ ቅዳሴያት ይልቅ አጭር በመሆኑ ቀሳውስቱም ህዝቡም ይወዱታል። ይህ የቅዳሴ ክፍል በቅዳሴ ሐዋርያት መንገድ ብናየው ጸሎተ አስተብቁዖ /የምልጃ ጸሎት/ ይጀምርና የቡራኬ ጸሎትን ወይኑንና ህብርስቱን እያዘጋጀ ጸሎተ ፍታትን ፣ የንስሐ ጸሎትን አድርሶ ቁርባኑን /የጌታ እራትን/ በአንድነት ይዘው ከቤተ መቅደሱ ወደ ህዝቡ ይወጣሉ ከዚያም የጌታን እራትአካፍለው አኩቴት ቅድስት ተደርሶ የህዝብ ስንብት ይደረጋል። ወይም «እተው በሰላም» ይላል።

ይህ ከላይ ያየነው ሁሉ በቅዳሴ አካሄድና አልፎ አልፎም ያካተ ታቸው ቃላት ሲሆኑ በውስጡ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች ተ ጠቅሰው እናገኛለን:: ነገር ግን የቅዳሴ መጻህፍት ሁሉ ሙሉ በሙሉ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት ግን በአሁኑ ጊዜ አስቸጋሪ ይመስላል::

ሌላኛው የአምልኮ ዓብይ ክፍል ቅኔ ማሕሌት ነው ::ይህ ክፍል የመዘምራን ክፍል ነው ከበዓላት ዋዜማ አንስቶ እስከ በአሉ ፍጻሜ ድረስ እንዲሁም በአዘቦት ቀንም የሚዜምበት /የሚቆምበት/ ጊዜ አለ:: ቅኔ ማህሌትን በምናነሳበት ጊዜ ዋናው የሚታወሰው ቅዱስ ያሬድ ነው::ያሬድ በዜማ ከመነሳቱ ከ523 ዓ.ም በፊት በኢትዮጵያ የተ ለመደ ደንበኛ ዜማ እንደ አለ በታሪክ ተጽፎ አይገኝም:: ነገር ግን ያሬድ ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን በርካታ ቃልና ታሪክ አውጣጥቶ በአራት ክፍለ ዘመን ከፍሎ ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ ጾም፣ ፋሲካ በማለት ሰየማቸው::በእያንዳንዱም ዘመን (ወራት) ውስጥ ለሚገኙት ሰንበታት (ሳምንታት) ከወቅቶች ጋር ተስማሚ የሆነ ስያሜ በመስጠት ዕለታት፣ ሳምንታት፣ ወራት ሁሉ የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራዎች የሚታሰቡባቸው እንዲሆኑ አደረገ :: ይህንንም በሦስት ዓይነት ዜማ ይሄውም ግዕዝ፣ ዕዝል ፣ አራራይ በማለት ወሰን አደረገ::

ቅኔ ማህሌት ማለት ከግዕዝ የተገኘ ቃል ሲሆን ቀነየ ገዛ፣ ተ ቀንየ ተገዛ፣ ቅኔ መገዛት፣ አገዛዝ ማለት ነው:: እንዲሁም ሐለየ - በዜማ አንጎራጎረ፣ ዘፈነ፣ ዘመረ፣ አዜመ:: ማሕሌት - በሥርዓት የሚዜም የዜማ ድምጽና ስልታዊ አገባቡ ማለት ነው:: በተገናኝ «ቅኔ ማሕሌት» ሲባል መዘምራን በውዝዋዜ በሽብሸባና በዜማ መሳሪያዎች ታጅበው ወይም ሳይታጀቡ በማዜም ለአምላክ በዝማሬ የሚገዙበት ሥርዓት ነው:: «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት፣ ወተሐሰዩ ሎቱ

በረዓድ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ ለርሱ በመንቀጥቀጥ ደስ ይበላችሁ /መዝ 2:11/» እንደተባለው ማለት ነው::[40]

ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው የዜማ መጽሐፍት ከመጽሀፍ ቅዱስ ያልወጣ ሲሆን ከእርሱ ዘመን በኋላ የተወሰኑ የነገረ መለኮት አስተ ሳሰቦች እና የገድሎች ታሪክ ተጨምረው መገኘታቸው ሲታይ የራሱን የዜማ ስልት ተከትለው በየጊዜው የተነሱ ሌሎች ሊቃውንት የጨመሩት እንዳለ ያረጋግጣል[41]

እንግዲህ ቅኔ ማህሌት ሊሊቱን ሙሉ አሊያም ከቅዳሴ በፊትና በኋላም ቢሆን በዜማ ምስጋናና አምልኮ የሚቀርብበት አንዱ የቤተ ክርስቲያኗ አምልኮተ ሥርዓት ነው::

እንግዲህ ቅኔ ማህሌት ሊሊቱን ሙሉ አሊያም ከቅዳሴ በፊትና በኋላም ቢሆን በዜማ ምስጋናና አምልኮ የሚቀርብበት አንዱ የቤተክርስቲያኗ አምልኮተ ሥርዓት ነው::

ከዚህም የአምልኮ ክፍል በተጨማሪ በየአውደ ምህረቱ: በልዩ በዓላት ጊዜም /እንደ ጥምቀት በዓል/ የህብረት እግዚኦታ /ልመና/ ወይም የስብከትም የአጫጭር የጸሎትና የዝማሬ ጊዜያቶችም ይኖራሉ:: ይህ የአውደ ምህረት /የውጭ አደባባይ/ስብከት እና የሰንበት ትምህርት ቤቶች ጊዜያት የተጀመሩት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምናልባትም በ1981 ዓ.ም ሳይሆን አይቀርም:: በእነዚህ የህብረት ጊዜ ያት ቤተክርስቲያኗ መናፍቅ መፈልፈያ ሆኑ በሚል ብዙ ጊዜ ታማቸዋለች: ትዘጋቸዋለችም: ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ጉልበት የላቸውም::

---

40. ጮራ መጽሔት ቁጥር 12 ገጽ 18 በማህበረ በኩር


41. መርህ ልቡና ከሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቁርቆስ ገጽ 16

ከዚህ በተጨማሪ ምዕመናን በየፊናቸው በግል የጸሎት ጊዜ ያቶቻቸው በአንቃአዶ ህሊና /ህሊናን በማንሳት/ የጸሎት መጽሀፍትን በማንበብ አልያም ከልባቸው በመጸለይ በቅጽረ ቤተክርስቲያን ይገኛሉ።

ከዚህ ውጭ ቤተክርስቲያኗ በዓመት የመደበቻቸው 7 ዓበይት የአፅዋማት ወራትና ቀናት አሉአት። ሁሉም ምዕመናንም በነዚህ ወቅቶች እንዲሳተፉ መመሪያና ትምህርት ይተላለፋል።ከእነዚህ አፅዋማት መካከል ታላቅ የሆነው «ዓብይ ፆም » የተባለው ሲሆን በዚህ የጾም ወራት በርካታ የሃዲስ ኪዳን መጽሐፍት የሚነበብበትና ትምህርት የሚሰጥበት ጊዜ ነው።

## አስተዳደራዊ አወቃቀር

ወደ ቤተክርስቲያኗ አስተዳደራዊ አደረጃጀት ስንመጣ የጥንቱ ምን እንደሚመስል በበቂ ሁኔታ መረጃ ባይኖርም በየዘመናቱ እየተ ሻሻለና እየጎለበተ ሄዶ በአሁኑ ጊዜ አወቃቀሩ ከዚህ በታች እንደ ተገለጸው ይመስላል ።


ቅዱስ ሲኖዶስ
ቋሚ ሲኖዶስ
ሀገር አቀፍ ሰበካ አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ
ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤ
ሀገር አቀፍ ሰበካ አጠቃላይ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ
የጠቅላይ ቤተክህነት አስተዳደር ጉባኤ
- ሊቃውንት ጉባኤ
- የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መመሪያ
- የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ
- የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ
- የካህናት አስተዳደር መመሪያ
- የቅርስ ጥበቃና ምዝገባ መምሪያ
- የገዳማት አስተዳደር መምሪያ
- የዕቅድና ልማት መምሪያ
- የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃመምሪያ
- ሒሳብና በጀት መምሪያ
- የስርዓት ተክሊል መምሪያ
- መንፈሳዊ ፍርድ ቤት
- የሕግ አገልግሎት
- የቁጥጥር አገልግሎት
- ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
- የሕጻናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት
- ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት
- ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
- ጉፋ እደጥበብ ማሰልጠኛ ድርጅት
- የቁልቢ ገብርኤል ንዋያተ ቅዱሳት ማደራጃ
-ንዋያተ ቅድስትማዘጋጃ
- ቅድስተ ስላሴ መ/ኮሌጅ
- ሰ/ብ/ቅ/ጳ/ከ/መ/ት/ቤት
- ከሳቴ ብርሃን ሰላማ መ/ኮ
ሀገረ ስብከት
- የውጭ ግንኙነት መምሪያ
- የቅዱስ ፓትሪያሪኩ ልዩ ጽ/ቤት
ወረዳ ቤተ ክህነት
አጥቢያ ቤተክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ስርአተ አምልኮቷንና ያላትን ሠማያዊ ተልእኮ ለመፈጸም አስተዳደር አደረጃጀት በእጅጉ ያስፈልጋታል:: የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ከነበረባት በርካታ ችግሮችና የመንፈሳዊ ውድቀቷ ዋነኛ ችግር የአስተዳደር ድክመት ነበር:: ፍትህ በቤተክርስቲያኗ ስለታጣ ምዕመናን ወደ ዓለማዊያን ፍርድ ቤት ይሄዱ ስለ ነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እየነቀፈ "ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፍረድ ፈንታ በአመጸኞች ፊት ሊፈርድ ይሄዳልን? ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን? በዓለምስ ላይ ብትፈርዱ ከሁሉ ይልቅ ትንሽ ስለ ሚሆን ነገር ልትፈርዱ አትበቁምን? ... የፍርድ ቤት ቢያስፈልጋችሁ በቤተክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጆች አድርጋችሁ ታስቀምጣላችሁን? አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ እንደዚህ ነውን? በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው ከእናንተ ዘንድ አይገኝምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል ይህም በማያምን ፊት ያደርጋል?" በማለት ሰፊ ወቀሳ አቅርቦባታል /1ኛቆሮ 6:1/:: ቤተ ክርስቲያን አስተዳደሯ ወጥና ግልጽ ሁሉን ያቀፈና ቀልጣፋ አሰራር ከሌላት መንፈሳዊ ታሪካአንና ተልዕኮዋን ዘንግታ አላስፈላጊ ሙግት ጀምራ እስከ መበተን ልትደረስና ምዕመናን ያለ እረኛ መቅረትን ያስከትላል:: የቆሮቶስ ቤተክርስቲያን ያስተዳደርና የአደረጃጀት ችግር የሰፋ በመሆኑ መንፈሳዊ ህይወቷና አገልግሎቷ የተነቀፈ ስለ ነበር ሐዋርያው «ሁሉ በአግባብና በስርዓት ይሁን» በሚል አስተዳደራዊ መዋቅሯንና መንፈሳዊ ህይወቷን እንድታስተካክል መክሯል::

አስተዳደር ማለት አንዱ ገዢ ሌላው ተገዢ ሲሆን ይህም ሰው ሲፈጠር አብሮ እግዚአብሔር አምላክ የፈጠረው የባርኮት ሥርዓት መሆኑን ቃሉ "እግዚአብሔርም ሰውን ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ግዟትም የባህርን አሳዎችና የሰማይንም ወፎች በምድርም

ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዟቸው» /ዘፍ 1፤27፣28/ ይላል። ከዚህም በላይ ሰው ለእግዚአብሔር ተገዢ እንዲሆንም አባታዊ ህግ ሰጥቶታል /ዘፍ 2:16-17/ ከዚህ ትዕዛዝም ወጥቶ አለመታዘዝን በመ ረጠ ጊዜ እግዚአብሔር አስተዳደራዊ እርምጃም ወስዶበታል /ዘፍ 3፤1-24/።

ከሰው ጅማሬም በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እንደምንገነዘበው እስራኤላውያን በነገድ በነገድ ተደራጅተው በአለቆቻ ቸው ይመሩ ነበር ።

ከሙሴ እስከ ሳሙኤል ዘመን ድረስ ደግሞ ነብይነትን ከንግስና ከመስፍንነት ጋር አጣምረው ብሔራዊ አስተዳደር አከናውነዋል። ሙሴም ደግሞ ከእስራኤላውያን አዋቂዎችን ሁሉ መርጦ ለህዝቡ ሾሞላቸዋል /ዘጻ 18፤25/። ከዚያም በኋላ በበርካታ መሳፍንት፣ ነገስታትና ነብያት የእግዚአብሔር ህዝብም ሆነ ሌላው ተመርተዋል።

ሰው ያለአስተዳደር በፍጹም በህብረት አልያም በግል መኖር አይችልምና በዘመነ ሐዲስም የፖለቲካ መሪዎች እንካእ ሳይቀሩ በእግዚአብሔር እንደተሾሙ ህዝቡም ለባለስልጣናቱ እንዲገዛ ባይገዛ ደግሞ የእግዚአብሔርን ስርዓት እንደ ተቃወመ እንዲሁም ባለመገዛት ጠንቅ ባለስልጣናቱ የሚወስዱት አስተዳደራዊ ቅጣት ሁሉ ትክክል እንደሆነ ፍንትው ተብሎ ተጽፏልናል /ሮሜ 13፤1-7/። ቤተ ክርስቲያንም መሪዎች እንዲሁት የአስተዳደር ሁኔታዋን እንደእግዚአብሔር ቃል አድርጋ እንድትደራጅና እንደተደራጀችም በእነዚህ ጥቅሶች በትክክል መረዳት ይቻላል። /ሐዋ 14፤23፣ ኤፌ 5፤21-33፣ 1ጢሞ 3፤1-13፣ ሐዋ 20፤28፣ ኤፌ 4፤10-11፣ ዕብ 13፤17/

«ቅዱስ ሲኖዳስ»

በመሆኑም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ብሔራዊ ሐይማኖት ሆና ለረጅም አመታት የቆየችበት ዋነኛ ምክንያት የአስተዳደር አደረጃጀቷ ጠንካራ በመሆኑ ነው። የአስተዳደሯ ይዘት የጵጵስና አስተዳደር ወይም የኤጵስ ቆጳሳዊ አስተዳደር ሆኖ ሉአላዊውን ባለስልጣን «ቅዱስ ሲኖዳስ» በማለት የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ለማሳየት የመካከለኛ ወንበሩ ክፍት ሆኖና መጽሐፍ ቅዱስ ተ ቀምጦበት /ፍት.ነገ አንቀጽ ቁ188/ ቤተክርስቲያኗን በበላይነት የሚመራትና የሚጠብቃት ስርዓቶች ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች የሚያወጣ የሚያሻሽል የሚሽም ጉባኤ ነው። በዚህ ጉባኤ ውስጥም ፓትሪያሪኩ ሊቀጳጳሳት ጳጳሳት ይገኙበታል ።ይህም ስብሰባ በፓትሪ ያሪኩ ሰብሳቢነት ይመራል።

«ቋሚ ሲኖዶስ»

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ባለስልጣን «ቋሚ ሲኖዶስ» ሲሆን በየሶስት ወሩ አባላቱ እየተተኩ ህጉን የመተርጎምና የማስፈጸም ስልጣን ያለው አካል ነው /ህገ ቤተክርስቲያን 1991 አንቀጽ 7/ በፓቲያሪኩ ሰብሳቢነት ስብሰባው ይመራል።

የዚህ የቋሚ ስኖዶስ አባላት በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ - ጉባኤ የተመረጡ አራት ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት እና ኤጲስ ቆጳሳት ናቸው ።

«ፓትሪያሪክ»

«ፓትሪያሪክ» በሦስተኛ ደረጃ ያለ የስልጣን ደረጃ ነው። ለፓትሪ ያሪክነት እጩዎች ከሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጳሳት፣ ይመ ረጣሉ። «ፓትሪያሪክ» የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን የመጀመሪያ ዋና አባት እንደ ማለት ነው። ፓትሪያሪኩ ከተሸሙበት ጊዜ አንስቶ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ እገሌ ፓትሪያሪክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት

ዘኢትዮጵያ ይባላል /ህገ ቤተክርስቲያን 1991/ ፓትሪያሪኩ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ ስብሰባዎችን መምራት፣ ኤጲስ ቆጶሳትን መሾም መዓረግ መስጠት፣ በሲኖዶስ የተወሰኑ ሕጎችና ደንቦች መመሪያዎች ውሳኔዎችን በተግባር መዋላቸውን ይቆጣጠራል።

«የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት»

ከዚህ ቀጥሎ ያለው የስልጣን ተዋረድ «የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት» ሲሆን የሥራ አስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ከፍተኛ አካል ነው። በአንድ ሥራ አስኪያጅና በአንድ ምክትል ሥራ አስኪያጅ በሲኖዶስ የሚሾም ይኖሩታል። የመምሪያ ኃላፊዎች የጠቅላይ ቤተ ክህነት የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ናቸው። ሲኖዶሱ ያስተላለፋቸውን ሕጎች ደንቦች መመሪያወችን በሥራ ይተረጉማል። ከሀገረ ስብከቱ በይግባኝ የሚመጡ የአስተዳደር ጉዳዮችን ውሳኔ ይሰጣል።

«የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት»

ቀጥሎ «የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት» ነው ። ይህ ጽ/ቤት በቅዱስ ሲኖዶስ በተሾመ ሊቀጳጳስ ወይም ኤጲስቆጶስ ይመራል በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙ የቤተክርስቲያኗ አስተዳደሮች /ገዳማት፣ አድባራት፣ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም በየደረጃው የሚቋቋሙ ሰበካዎችን ወረዳ ቤተክህነት ጽ/ቤት/ የሥራ አስፈጻሚ አካል ነው። የራሱም የአስተዳደር ጉባኤ አለው። ሊቀጳጳስም ስብሰባውን በሰብሳቢነት ይመራሉ በሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ተመርጦ ለጠቅላይ ቤተክህነት ሥራ አስኪያጅ ቀርቦ ፓትሪያሪኩ ሲስማማ በጠቅላይ ቤተክህነት ስራ አስኪያጅ ፊርማ ይሾማል።

« የወረዳ ቤተክህነት ጽ/ቤት»

ከዚያም የወረዳ ቤተክህነት ጽ/ቤት ሲሆን ይህም በወረዳው ክልል ሥር ለሚገኙ ገዳማት፣ አድባራት፣ አጥቢያዎች ከፍተኛ ኃላፊነት

ያለው ጽ/ቤት ነው። ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ በሆነ ሥራ አስኪያጅ ይመራል ። ከሀገረ ስብከቱ የሚተላለፉ መመሪያዎችን ያስፈጽማል በቃለ ዓዋዲ አንቀጽ 35 በተደነገገው መሰረት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍፍሎች ይኖሩታል ስልጣኑ በቃለ ዓዋዲ/አስተዳደራዊ መመሪያ መጽሀፍ/ ከአንቀጽ 4 እስከ 37 ተዘርዝሯል።

« አጥቢያ አቢያተ ክርስቲያናት»

ከዚህ በኋላ ወደ አጥቢያ፣ አድባር፣ ገዳም በተናጠል የየራሳቸውን ደብር አለቃ፣ አበምኔት/በወንድ ገዳም ያለው አስተዳዳሪ ስያሜ/፣ እመምኔት /በሴት ገዳም ያለች አስተዳዳሪ ስም/ በሚል የአስተዳደር ስያሜ በተሾሙ ሰዎች ይመራሉ፡፤ ከወረዳ ቤተክህነት ጽ/ቤት የሚተላለፍ መመሪያዎችንና ቃለ ዓዋዲ በሚያዘው መሠረት ያስፈጽማሉ ከዚህ ስር ደግሞ በርካታ መዓረጋት ባላቸው አገልጋዮች በተለይ ደግሞ በመምህረ ንስሐ አማካኝነት አንድን ቤተሰብ ሲዘልቅም አንድን ግለሰብ የምትመራበት አስደናቂ አስተዳደር ዘይቤ ትጠቀማለች። ይህ የአስተዳደር መዋቅር እጅግ መልካም እንደሆነ ማሰብ አያቅትም በእርግጥ በአፈጻጸም ሂደት ላይ ከፍተኛ ድክመት እንዳለ የታወቀ ቢሆንም መዋቅሩ ግን መልካም ነው ።የአፈጻጸሙን ድክመት በተመለከተ በሁለተኛው መጽሐፍ ስለተጠቀሰ ማየት ይቻ ላል እንላለን።

6. የሐይማኖት መግለጫ /ፀሎተ ሐይማኖት/

በ325 ዓ.ም ስለሐይማኖት በኒቂያ የተሰበሰቡ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሊቃውንት የሃይማኖትን ነገር ተናግረው በሐይማኖተ አበው መጽሐፍ በግልጽ አቋማቸውን አስቀምጠዋል ። ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት አሪዮስን አውግዘው ከለዩ በኋላ ከዚህ በታች ያለውን አቋም በአንድነት የሀይማኖት መግለጫ በማለት አስፍረዋል።

ይህንንም የሃይማኖት መግለጫውን የጥንቷ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስስቲያን ሙሉ በሙሉ ሳትጨምርና ሳትቀንስ ተቀብላዋለች::ይህ የእምነት አቋም መግለጫ የመሰረተ እምነቷ ዋናና ታላቅ ስፍራ የሚሰጠው ሲሆን በአሁኑ ጊዜም ለእኛ ምን ያህል መሰረቷ እውነት እንደነበረም ለማወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው:: አንድ ምእመንም በጥምቀትም ሆነ በሌሎች ሁኔታዎች ስትቀበል ይህን የሀይማኖት መግለጫዉን በማመን ድምጹን አሰምቶ እንዲናገረው ታደርጋለች ::

ሕጻናት እንኳ ለጥምቀት ስርዓት በሚመጡበት ወቅት ወላጆቻቸውና የክርስትናዉን ኃላፊነት የሚሸከመው ሰው / የክርስትና አባት ወይም የክርስትና እናት / ድምጹን አሰምቶ እንዲናገረው ታደርጋለች ::

<u>ግእዝ</u> /ዘሰለስቱ ምእት ምእራፍ 17

1ኛ. ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜኩሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ

2ኛ. ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋህድ ዘህልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም

3ኛ.ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ:: ዘዕሩይ አምላክ ምስለ አብ በመለኮቱ ::

<u>በአማርኛ</u>

1ኛ.ሁሉን በያዘ ሰማይና ምድርን የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን::

2ኛ. ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን በአንድጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን::

3ኛ. ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል::

4ኛ. ዘቦቱ ኩሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይነ ወዘበምድርኒ፡፡

5ኛ. ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት፡፡ ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈ ስቅዱስ ወእማርያም ቅድስት ድንግል

6ኛ. ኮነ ብእሴ ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ፡ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት፣በከመጽሐፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት፡፡

7ኛ. ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ፡፡ዳግመ ይመጽእ በስብሐትይኴንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ መኀለቅት ለመንግስቱ፡፡

8ኛ. ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረፀ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንስብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት፡፡

9ኛ. ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን እንተ ላዕሌነ ኩሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት፡፡

10ኛ. ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት

11ኛ. ወንሴፎ ትንሳኤ ሙታን፡፡

12ኛ. ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለም ዓለም አሜን፡፡

4ኛ. ሁሉ በርሱ የሆነ ያለ ርሱ ግን ምን ምንም የሆነ የለም ፡፡ በሰማይም ያለ ምድርም ያለ

5ኛ. ስለእኛ ስለሰዎች ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ ከቅድስት ድንግል ማሪያም በመንፈስ ቅዱስ ግብር ፈጽሞ ሰው ሆነ፡፡

6ኛ. ሰው ሆኖ በጴንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለኛ ተሰቀለ ታመመ ሞተ፡ ተቀበረም፡፡ በሶስተኛዉም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ፡፡

7ኛ.በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፡፡ዳግመኛምበሕያዋንና ሙታንንም ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፡፡ ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም፡፡

8ኛ. ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሰረጸ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን እንስገድለት እናመስግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነብያት የተናገረ፡፡

9ኛ. ከሁሉ በላይ የምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን እናምናለን ፡፡

10ኛ. ኃጢአትን ለማስተሠረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን፡፡

11ኛ. የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን፡፡

12ኛ. የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ አሜን ፡፡

የክርስትናን እምነት ምን እንደሆነ ለመረዳት ስህተትን ለመለየት የጠለቀው ሰፊ ትምህርቱን በአጭሩ ለማገለጽና እንደ አቋም የሚያገለግል ሆኖ የተዘጋጀው አንቀጽ ከዚህ በላይ የተገለጸው የሐይማኖት መግለጫ ወይም ጸሎተ ሐይማኖት ተብሎ የሚታወቀው ባለ 12 አንቀጽ ነው:: አንዳንድ ጊዜም ይህ አንቀጽ የሐዋርያት ጸሎተ ሐይማኖት በሚል ይጠራል:: ባለ 12 አንቀጽ መሆኑም የ12ቱን ሐዋርያት ቁጥር ያገናዘበ ነው ብለው ይናገራሉ::[43]

ማንም ቢሆን «አምናለሁ» ሲል ለሚያምነው ነገር ራሱን የሰጠ ማለት ነው ። በጋራ አንድ ነገር ለመደገፍ ወይም ለመከተል ሁሉንም ለአንድ አይነት የእምነት መግለጫ የሚያስተገብር የጋራ የሆነ እምነት ቋንቋ የግድ አስፈላጊ ነው፡፤ ይህ የሐይማኖት መግለጫም ከቅዱሳት መጽሐፍት ከፍተኛ ጠቀሜታ /ዶክትሪን/ ያላቸውን ነጥቦች ያሰባሰበ፣ ልክ አንዲት ስናፍጭ በጣም ብዙ ቅርንጫፎችን ከቅንጣት ፍሬዋ እንደምታበቅል ሁሉ፣ በብሉይና በአዲስ ኪዳን የሚገኘውን የእምነት ፍሬ ሃሳብ ሙሉውን የእውነተኛውን ሃይማኖተ እውቀት በጥቂት ቃላት አካቶ የያዘ ነው::

---

43. የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ገጽ 64 ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ ይፋ ካደረጉት ከዋናው የላቲን መጽሐፍ ቅጅ ወደ አማርኛ የተተረጎመ::

የሐይማኖት መግለጫው

1ኛ. የእግዚአብሔር መለኮታዊ አካልና ድንቅ ስለሆነው የፍጥ ረት ስራው

2ኛ. አንደኛው መለኮታዊ አካል ስለሆነው ኢየሱስ ክርስቶስና ስለፈጸመው የማዳን ሥራ

3ኛ. ሌላኛው መለኮታዊ አካል ስለሆነው ስለመንፈስ ቅዱስ

4ኛ. ስለአንዲት የማትታይ ቤተክርስቲያን

5ኛ. ስለአንዲት ጥምቀት እና

6ኛ. ስለትንሳኤ ሙታንና ስለዘላለም ህይወት ያካተተ ነው። እነዚህም የክርስትና መሠረተ እምነት ተብለው የሚጠሩ ናቸው።

ይህ የሐይማኖት መግለጫ /ጸሎተ ሐይማኖት/ ታሪካዊ አነሳሱ መናፍቃንን ለመለየትና ምዕመናንም በትክክለኛው ሐይማኖት እንዲጸኑ ለማድረግ ታስቦ በጉባኤ ኒቂያ /325 ዓ.ም/ እና በጉባኤ ቁስጥንጥኒያ /381 ዓ.ም/ የተወሰነ ቀኖና ነው።[44]

የሐይማኖት መግለጫው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርቲያን በካቶሊክ ቤተክርስቲያን[45] በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት[46] ሁሉ ተቀባይነት ያለው ነው። ሁሉም በጥምቀት ተ ከታይ ሲያደርጉ፣ የሹመት ስርዓት ሲፈጽሙ፣ ወይም የአጠቃላይ ስብሰባ /ሲኖዶስ/ ሲያደርጉ እንደ አቋም የማሳወቅ ሁኔታ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ይደግሙታል ። አንዳንድ ጊዜም ልክ እንደመደበኛ ጸሎት ሆኖ በማንኛውም የጸሎት ሰዓት በቃል እንዲያዝና እንዲባል ያደርጋሉ። ስለዚህ ነው "ጸሎተ ሐይማኖት" ተብሎ በሌላ ስሙ የሚታወቀው።

---

44.ትምህርተ ሐይማኖት ክርስቲያናዊ ሕይወት በሲቀ ጉባኤ አበራ በቀለ 1996ገጽ 59

45. የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ገጽ 60

46. የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ መተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ 1991 ዓ.ም ገጽ 39

የኢትዮጵያ ቤተክርቲያን በቅዳሴ ሠዓት ዲያቆኑ «ንበል ኵልነ በጥበበ እግዚአብሔር ጸሎተ ሐይማኖት፤- በእግዚአብሔር ጥበብ ሆነን ሁላችን የሃይማኖትን ጸሎት እንበል «ሲል ቀዳሽ አስቀዳሹ ሁሉ ድምፃቸውን አሰምተው ወይ በዜማ አሊያም በጥሬ ቃሉ እንዲያግሙት ታዛለች :: /ሥርዓተ ቅዳሴ 31/

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ይህን ጸሎተ ሃይማኖት /የሐይማት መግለጫ/ ተመሳሳይ ሀሳብ ያለው አመክንዮ ዘሐዋርያት /የሐዋርያት አመክንዮ/ የሚባል ሌላ አላት::: እርሱም በግዕዝና በአማርኛ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል::

## አመክንዮ ዘሐዋርያት በግዕዝና በአማርኛ

| በግዕዝ | በአማርኛ |
|---|---|
| ነአምን በአሐዱ አምላክ ገበሬ ኵሉ ፍጥረት አብ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ አልቦ ውስተ ሀላዌሁ አመክንዮ በከመ አቅደምነ ነገረ አላ ባሕቱ ሀልው በኵሉ መዋዕል አልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት :: | የጌታችንና የአምላካችን የመድሃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሚሆን ፍጥረቱን ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ እናምናለን:: ባሕሪው ምክንያት የለበትምና አስቀድመን እንደተናገርን በዘመኑ ሁሉ ይኖራል እንጂ ጥንት ወይም ፍጻሜ የለውምና:: |
| ወቦቱ በርሃን ዘኢይጠፍእ ወአልቦ ዘይከል ቀሪበ ኀቤሁ ኢኮነ ክልዔተ ወኢሠለስተ ወኢይትዌሰክ አላ አሐዱ ውእቱ ባሕቲቱ ዘይነበር ለዓለም:: እስመ ኢኮነ ሥውረ ዘኢይትአምር ዳዕሙ ጥዩቀ አእመርናሁ በኦሪት ወበነቢያት ከመ ውእቱ አኃዜ ኵሉ ወስሉጥ ላዕለ ኵሉ ፍጥረት አሐዱ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእነ | የማይጠፋ ብርሃን አለው ወደ እርሱም መቅረብ የሚቻለው የለም:: ሁለተኛ አይደለም ሦስተኛም አይደለም፣አይጨመርበትም፣ ብቻውን ለዘላለሙ የሚኖር አንድ ነው እንጅ:: የማይታወቅ የተሠወረ አይደለምና ሁሉን የያዘ ከፍጥረቱም ሁሉ በላይ ሰለጠነ መሆኑን በኦሪትና የበነብያት ፊጽመን አወቅነው እንጂ:: |

ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተወልደ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ወልድ ዋህድ ዘዕሩይ ምስሌሁ ገባሬ ኩሉ ሠራዊት ወሚመታት ወሥልጣናት ዘሠምረ ይኩን ሰብአ በደኀሪ መዋዕል። ወነሥአ ሥጋ እማርያም እምቅድስት ድንግል ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ወተሐፅነ ከመሰብእ ዘእንበለ ኃጢአት ወአበሳ ወአልቦ ጉህሉት ውስተ አፋሁ ነሣ። ወእምዝ ሐመ ወምተ በሥጋ ወተንሥአ እሙታን በሣልስት ዕለት ወአረገ ሰማያተ ኀበ አብ ዘፈነዎ ወነበረ በየማነ ኃይል።ወፈነወ ለነ ጳራቅሊጦስሃ መንፈስ ጽድቅ ዘወጽአ እምኀበ አብ ወአድኀነ ዓለመ ።

ዘህልው ምስለ አብ ወወልድ።

ንብል እንከ ከመ ኩሉ ሠናይ ፍጥረተ እግዚአብሔር ወአልቦ ግዱፍ ወመንፈስሰ ሕይወተ ሥጋ ይእቲንጽህት ወቅድስት በኩሉ።ወንሕነስ ንብል ኪመ ስብሳብ ንጹሕ ውልደት ዘአልቦ ርኩስ እስመ ፈጠሮሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለሔዋን ከመ ይብዝኁ ሕዝብ። ንለቡ እንከ ከመቦ ውስተ ሥጋነ ነፍስ

የጌታችንና መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር እንድነው።ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ ከእርሱ ጋር የተካከለ የሚሆን አንድ ልጅ ሠራዊትንና ዓመታትን ፣ ሥልጣናትንም ሁሉ የፈጠረበኋለኛው ዘመን ሰው ይሆን ዘንድ የወደደ ያለ ወንድ ዘር ቅድስት ከምትሆን ከድንግል ማርያም ሥጋን ያለ ኃጢአትና ያለ በደል እንደ ሰው አደገ፣በአንደበቱም ሐሰት የለበትም። ከዚህ በኋላ በሥጋ ታመመ ሞተም በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። ወደ ላከውም ወደ አብ ወደ ሰማይ ዐረገ፣ ኃይል ባለውም ቀኝ ተቀመጠ። ከአብ የሠረፀ ጳራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን ሰደደልን።ዓለሙንም ሁሉ አዳነ።ከአብና ከወልድ ጋር ሕልው የሚሆን። እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደሆነ የሚጣልም እንዳሌለ እንናገራለን።የሥጋ ሕይወት የምትሆን ነፍስ ግን ንጽህት ቅድስት ናት። እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ልደትም ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን ። ሕዝቡ ይበዙ ዘንድእግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፈጥሮአቸዋልና። ከሥጋ ጋር የማትሞትና የማትበሰብስ ነፍስ በሥጋችን እንዳለ እናስተውል።

አንተ ኢትመውት ወኢትማስን ምስለ ሥጋ ንሕነሰ ናስቁርር ኵሎ ግብሮሙ ስዕልዋነ ሕግ ሃይማኖት ወኵሎ ፍልጠተ ወአሲወ እስመ ርኵሳን እሙንቱ በንቤነ::
ወዓዲ ነአምን ትንሳኤ ሙታን ጻድቃን ወኃጥአን ወዕለተ ኵነኔ እመ ይትፈደይ ኵሉ በከመ ምግባሩ::
ወዓዲ ነአምን ከመ ክርስቶስ ኢኮነ ሕፀፀ እምትስብዕቱ ወአምንተኒ አላ ውእቱ እግዚአብሔር ቃል ዘኮነ ሰብአ በጽድቅ ወዐረቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀ ካህናቲሁ ለአብ:: ኢንትገዘር እንከ ከመ አይሁድ ነአምር ከመ መጽአ ዘይፌጽም አሪተ ወነብያተ ዘኪያሁ ይሴፈው ምጽአቶ ኵሎሙ አሕዛብክርስቶስ ዘሠረፀ እምይሁዳ ወእምሥርወ ዕሤይ ዘሥልጣኑ ዲባ መትከፍቱ ሎቱ ስብሐት ወአኮቴት ዕበይ ወባርኮት ውዳሴ ወማኅሌት ይእዜኒ ወዘልፈኒ ለለዓለመ ዓለም አሜን::

እኛስ የሃይማኖት ለዋጮች ሥራቸውን እንጸየፋለን መለየታቸውንም ሁሉ ሕግ መለወጣቸውንም እነርሱ በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና:: ዳግመኛም የሞቱ የጻድቃንና የኃጥአን ትንሳኤ እንዳለ እናምናለን::ሁሉ እንደሥራው ፍዳውን የሚቀበልበት የፍርድ ቀንም እንዳለ እናምናለን::
ዳግመኛ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ የተነሳ ምንም ምን ሕፀፅ እንደሌለበት እናምናለን በእውነት ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ:: የአብ ሊቀ ካህናት የሚሆን እርሱ የሰውን ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ:: እንግዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር አሪትንና ነብያትን ኢየሱስ የሚፈጽማቸው እንደመጣ እናውቃለን አሕዛብ ሁሉ የእርሱን መምጣት ተስፋ የሚያደርጉት ኢየሱስክርስቶስ በይሁዳ በዕሤይም ሥር የተገኘ ሥልጣኑ በትከሻው ላይ የሆነ ነው:: ክብር ምስጋናና ገናንነት ቡራኬና ውዳሴ መመስገን ለእርሱ ይገባዋል:: ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን::

ከላይ እንደተገለጸው ጸሎተ ሃይማኖትና /የሃይማኖት መግለጫውና/ የሐዋርያት አመክንዮ በመሠረተ ሃሳባቸው ልዩነት አይታይባቸውም:: ይልቁንም በሃይማኖት መግለጫ የተጠቀሱትን የሐዋርያት አመክንዮው የማጉላት ነገር ያሳያል::

የሐይማኖት መግለጫው አራት አንቀጾች አሉት። ይህም አንቀጽ አንድ ላይ ስለ አንድ አምላክ እርሱም ፈጣሪነቱ አባትነቱና ሁሉን ቻይነቱን ያሳያል። አንቀጽ ሁለት ሦስትና አራት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለመሆኑና ሁሉን በእርሱ እንደፈጠረ ይናገራል፡፤ አንቀጽ ኣምስት ስድስትና ሰባት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ለማዳን ስላከናወናቸው ድርጊቶችና አንቀጽ ስምንት መንፈስ ቅዱስን ሲያሳይ፤፡ ስለቤተክርስቲያንና ክርስቲያንነት ስለሚያስገኘው ተስፋ ከአንቀጽ ዘጠኝ እስከ አስራ ሁለት ድረስ ያሳያል። በዚህም የአንቀጽ አከፋፈል መሠረት በስፋት ባይሆንም በአጭር በአጭሩ ውስጣቸው የያዙትን የጥንቱን ሃይማኖታዊ የትርጉም አቋሞችን ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

## አንቀጽ አንድ

## "ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ

## በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን"

### 1. አንድ አምላክ

ይህ አንቀጽ በአንድ አምላክ ብቻ ማመንን በግልፅ ያሳያል። አንዳንዶችና ሙስሊሙ ህብረተሰብ ቤተክርስቲያን በአንድ አምላክ እንደማታምን ይገልጻሉ ።[48] ነገር ግን አንድ አምላክ እንዳለ እርሱም ዓለምንና በዓለም ያለውን መልካም ነገር ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር እንደሆነ የምታስተጋባው እውነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በመሆኑ የቤተክርስቲያን መፈክር ሆኖ ኖሯል ። ደግሞም ይኖራል።[49]

---

48. ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን በአህመድ ዲዳት እና በሥላሴ ማመን ይገባሃልን ቡሮሹር መጠበቂያ ግንብ በዋችታወር

49. እምነት ክፍል 1 በኤርምያስ ዘመነ ገጽ 25

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርት፡- «እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ የለም ./ኢሳ 45፤18/ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» /ዘጸ 20፤3/ «እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» /ዘዳ 6፤4/ «ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማነው? ከአምላካችን በቀር አምላክ ማነው?» /መዝ (18)፡31/«እግዚአብሔር ግን አንድ ነው»/1ቆሮ 12:6/የሚለውን ክፍል በማመን በሰማይና በምድር አንድ አምላክ እንዳለ የሚያስረዳ ነው።

ይህ የቤተክርስቲያኗ ትምህርት በብሉይ ኪዳን በዓለም ላይ ሰፍኖ ከነበረው ልዩ ልዩ አምልኮተ ጣኦትና አህዛብ ከሚገዙላቸው ብዙኀን አማልክት ሁሉ የእስራኤል ህዝብ በአንድ አምላክ ብቻ እንዲያምን ከሙሴ ጀምሮ የተነሱት ነቢያት በአጽንኦት ያስተማሩት እውነት ነው። ይህም ትምህርት፡-

«እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ። እኔም ዛሬ አንተን የማዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ ለልጆችህም አስተምረው በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ ስትተኛም ስትነሳም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሠረው፣ በአይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።»/ዘዳ 6:4-9/ የሚል ነበር ።

ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አምላክ የሚለዉን ትምህርት የመጀመሪያውና ታላቁ ትዕዛዝ እንደሆነ አስተ ምሯል /ማር 12:29-30/ ይህም እግዚአብሔር አንድ ብቻ እንደሆነና አምልኮታችንም እምነታችንም ይኸው ብቻ ሆኖ ፈጣሪያችንን እንድንወደው ያስተምረናል ከእርሱ በበለጠ ሁኔታ (በማስቀደም) የምንወደው ነገር ካለ እርሱ ጣኦትና ሌላ ባዕድ አምልኮ ስለሚሆን «በፍጹም ልብህ» እግዚአብሔርን ውደድ ይለናል።

እንዲህ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለና /ኤር 4:6/ የኢትዮጵያ ቤተክርቲያን በሃይማት መግለጫዋ "አንድ አምላክን እናምናለን" በማለት አቋሟን ዝንት አለም አስተላልፋለች ::

**2. የእግዚአብሔር አባትነት**

የእግዚአብሔር አባትነት ለወልድ የባህሪ አባቱ፣ ለፍጥረት ሰራኢና መጋቢው፣ ለክርስቲያንም በመንፈሱ የሚመራውና የርስቱ ወራሹ ነው:: ይህንንም ዘርዝር ስናደርገው እግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ አባት የሆነበትን ሁኔታ በምስጢረ ስላሴ ርዕስ ስር ዘርዝር ያደረግን ሲሆን ይህም በግብር የሚገለጽ ተፈጥሮአዊ እኩልነት ያለው አስገኝው እንደሆነ የሚገልጽ ነው:: ይህንንም አባባል በዚሁ ሃይማኖት መግለጫው "ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ" በማለት ይገልጸዋል::

አብ ወልድን ልጄ ብሎ ይጠራዋል /ዕብ 1:5/ ወልድ አብን አባቴ ብሎ ይጠራዋል /ዮሐ 5:18፣ ዮሐ 17/ ሐዋርያትም "የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ" ብለው ይጠሩታል:: /ዮሐ 3፥16/ አጋንንትም እንኳ ሳይቀሩ "የእግዚአብሔር ልጅ" ይሉታል::፤ ይፈሩታል ይንቀጠቀጡለታልም /ማር 5፥7/ ይህ አባትነትና ልጅነት አጠራር የተለየ በስላሴ አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚተነተነው የጠለቀ ትስስርን የሚያመለክት ነው:: ያለ አንዱ ሌላኛው አይኖርም ይህም በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም:: "በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት"/1ኛዮሐ 1፥9/: "ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው" /1ኛዮሐ 1:23/:: "ወልድን የሚያከብር የላከውን አብን አያከብርም" /ዮሐ 5:23/:: "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን"/ዮሐ 14:23/::በማለት ያለ ልዩነት አንድነት ተገልጾአል::

እንግዲህ ይህ ማለት የእግዚአብሔር አባትነት ለእግዚአብሔር ወልድ የባህሪ አባቱ ነው። ይህ ያልገባው ሰው ክርስትና አይገባውም፡ አምላክም የለውም /2ኛዮሐ 1:9/።

እግዚአብሔር ለፍጥረት ሠራኢው እና መጋቢው አባቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ በስድስት ቀናት ውስጥ ደ ረጃ በደረጃ እግዚአብሔር አምላክ ብቻውን እንደፈጠረ ከእርሱ በቀር ሌላ ፈጣሪ እንዳልነበረ ሁሉንም ፈጥሮ መልካም ነው፡ እና እጅግ መልካም ነው በማለት ግምገማውን የሰጠ ያለ እርሱ ምንም ምን የተ ፈጠረ እንደሌለ ሁሉ በእርሱ እንደሆነ በግልጽ ፈጣሪነቱ ተጽፏል። ሌ ሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም ያብራሩታል /ኢሳ 44፤24፣ ዮሐ 1:3/ ፈጠረ የሚለው ቃል ያለመነሻና ያለ ጥንተ ነገር "አምኀበ አልቦ ኀበ ቦ" ካለመኖር ወደ መኖር መምጣትን ያመለክታል። ሰማይና ምድር ሲባል /ዘፍ 1:1/ የሚታዩትና የማይታዩትን ረቂቁንና ግዙፉን መንፈስንና ሥጋን ሌሎችንም ፍጥረታት የሚታወቁትና የማይታወቁትን ሁሉ ያካትታል። ለምሳሌ ሰማይ ተፈጠረ ሲባል ሠማይ ስንት ነው በውስጡስ ምን አለ? እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሊነሱ ይገባል በሌሎች የመጽሐፍ ክፍሎች ሠማይ ብዙ እንደሆኑ ሰማያት ተብሎ ተገልጾአል /2ጴጥ 3:12፣2ኛቆሮ 12:3/ ። በዚያ ውስጥም በርካታ ፍጥረታት እንዳሉ ተጠቅሷል /ዕብ 12:22-24/።ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ የሁሉም አባት መባሉ እርሱ በሰ-ማይም በምድርም ከምድርም በታች በባህር ውስጥ ላሉ በምድር ለሚርመሰመሱ በሰማይ ለሚበሩ ሁሉ ሰራኢና መጋቢ ለሕዝብና ለአሕዛብ ሁሉ መሪና ጠባቂ ነው። እርሱ ያለ አድሎ በክፉዎችና በበጎ ዎች ላይ ፀሐይን ያወጣል በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናብን ያዘንባል /ማቴ 5፤54/። ይህ አባትነቱንና ሉዓላዊነቱን ይገልጻል።፤ ሁሉም የእጆቹ ስራዎች ናቸውና በሚገርም ሁኔታ ይጠብቃቸዋል ይመራቸዋል ይንከባከባቸዋል። የሠማይ ወፎች ተመልከቱ አይዘሩም

አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም የሰማዩ አባት ይመግባቸዋል፤፤ የሜዳ አበቦችንና የሜዳውን ሳር ሁሉ በልዩ ልዩ ኅብረ ቀለም እንዴት አድርጎ እንደሚያለብሳቸው በጥንቃቄ የሚያስተውል ቢገኝ በእግዚአብሔር አባትነት ይደነቃል:: እነርሱ አይደክሙም አይፈትሉም ነገር ግን ደስ ብሏቸው ፈገግታቸውን ይሰጣሉ፤፤ እግዚአብሔር መጋቢና ጠባቂ አባት ነውና /ማቴ 6፤26-30/ ሐዋርያው ጳውሎስ "ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው ... እርሱም ህይወትና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና፤ አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም ...የሠውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው ... በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖራለን" በማለት እግዚአብሔር ብቸኛ የሁሉ ፈጣሪ የሁሉ አባት እንደሆነ ገልጾአል:: /ሐዋ 17:24-23/

በሌላ አንጻርም እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ እንደ ሐሳቡ ለተ ጠሩና ፈቃዱንና ትእዛዙን ተከትለው ለሚኖሩ የላከውን ልጁን አምነው ለተቀበሉ አባት ነው:: ይህ ደግሞ ከፍጥረት ሁሉ ጋር እኩል በሚሆን አባትነት የተለየና የአባትና የልጅ ትስስር ያለበት ሁኔታ ነው:: በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩ በአባታቸው ስልጣን የሚኖሩና የመንግስቱም ወራሾች ናቸው:: ቃሉ እንዲህ ይላልና:: «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከስጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም» /ዮሐ 1፤12/ ይህ የልጅነት ሥልጣን ሲሆን በመንፈስ የሚከናወን ነው::" በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና:: አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና ... ልጆች ከሆንን

ወራሾች ደግሞ ነን አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራን ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን" /ሮሜ 8:15-17/።

"ልጆችም ስለሆናችሁ አግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም። ልጅም ከሆንክ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ።" /ገላ 4:6-7/ ይላል። እንግዲህ ከአህዛብ ሁሉ በተለየ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምተው በሃጢአት ምክንያት ለዲያብሎስና ለፍርድ ተሸጠው ከነበሩበት የጨለማ ህይወት በክርስቶስ ብቸኛ አዳኝነት ተስማምተው ውሉድ የተሠኙ እግዚአብሔር በመንፈሱ የወለዳቸውና የሚመራቸው የመንግስቱም ወራሾች ናቸው። አለዚያ "ሠው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያያትም ሊገባባትም አይችልም" /ዮሐ 3:3/። ልጆቹ ግን በሰማያት የሚኖር አባታችን ሆይ ብለው ይጠሩታል ከእርሱም ጋር ይገናኛሉ /ማቴ 6:9/ ። እንግዲህ ከፍጥረት በተለየ ማዕረግ ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ታድለዋል። "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ እንዲሁም ነን" በማለት የእግዚአብሔር አባትነቱንና የፍቅሩን ታላቅነቱን የክርስቲያኖችም ልጅነትን ይገልጻል /1ዮሐ 3:1/

## አንቀጽ ሁለት

### " ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን"

ዓለም ገና ሳይፈጠር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር ያለቀዳሚና ተከታይ በተካከለ መለኮት ይኖር እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱሳችን ይገልጻል።

"በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ" /ዮሐ 1:2/ ቃል ሲባልም ዝርው ቃል ሳይሆን

እውነተኛ አካላዊና መለኮታዊ ቃል ማለት ነው በጽርዕ ቋንቋ «ሎጎስ» ይባላል ትርጉሙም ቃል ማለት ሲሆን ጥበብን ወይንም አዕምሮን ይጨምራል ::ይህም የእግዚአብሔር ቃሉ ጥበቡ ኃይሉ ማለት ነው /1ኛቆሮ 1:24/:: «የማይመረመር የአብ ሕሊናው እርሱ ነው የአብ ጥበቡ እርሱ ነው የአብ ኃይሉ እርሱ ነው:: የአብ ክንዱ እርሱ ነው፡ ቀኝ እጁም እርሱ ነው»[50] ይህ ጥበብ የሆነ ክርስቶስ እንዲህ ተጽፎለታል ::

«እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ በቀድሞ ሥራው መጀመሪያ ከጥንቱ ከዘላለም ጀምሮ ተሾምሁ ምድር ከመፈጠሯ አስቀድሞ ቀላያት ገና ሳይኖሩ እኔ ተወለድሁ የውኃ ምንጮች ገና ሳይፈልቁ ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ ምድሪቱንና ሜዳውን ገና ሳይፈጥር የመጀመሪያውንም የዓለም አፈር ስማዮችን በዘረጋ ጊዜ አብሬ ነበርሁ ::በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ ደመናትን በላይ ባዘጋጀ ጊዜ የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ በባሕርም ዳርቻን በወሰነ ጊዜ ውኃ ከትዕዛዙ እንዳያልፍ የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ የዚያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ» /ምሳ 8፤22-31/ በማለት የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን /1ኛ ቆሮ 1:24/ በጥበብ መስሎ ይገልጸዋል :: እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎት ወራቱ ከአይሁዶች ጋር በነበረው ክርክር «አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ አየም ደስም አለው» ባለ ጊዜ ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት:: ኢየሱስም እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው::» /ዮሐ 8፤56-58/ ደግሞም በጸሎቱ «አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ ብሏል /ዮሐ 17፤5/ በመቀጠልም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ የሰጠኸኝ ክብሬን

---

50. ሃይማተ አበው አልመስጠአግያ ምዕ 2፤12

እንዲያዩ ... » ይላል /ዮሐ 17፤24/ ይህ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ጋር የመኖር ሁኔታ መለኮታዊነትን ያሳያል:: መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር በመተካከል ይኖር እንደ ነበረ ያስረዳል /ፊል 2:6/:: በሌላ ክፍል «አንችም ቤተልሔም ኤ ፍራታ ሆይ አንች በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንች ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል::» ይላል /ሚክ 5:5-2፣ ማቴ 2:5-6/:: ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ ፊተኛ/አልፋ/ ነው:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን እንደ አቋም አድርጋ ሁለት ልደታትን ታምናለች ::[51]ይህም ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ በመተካከል ያለ እናት ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት እንደ ተወለደ ታምናለች::« ቀዳማዊ ልደቱን በድኅ ራዊ ልደቱ ገለጠው ስለዚህ ወልድ መባልን ያለመነሻ ገንዘብ አደረገ በአንድ በኩል የአብ የባሕሪይ ልጅ እንለዋለን እርሱም ነው:: እንዲሁም የሰው ልጅ ይባላል እርሱም ነው::
/ዮሐ 1፤18፣ ማቴ 16፤15፣ ማቴ 25፤31፣ ማቴ 26-64፣ማቴ16:26/»[52]
«ደግሞም ወልድ ከመወለዱ አስቀድሞ እርሱ ሳይኖር ዘመን ቀን ነበ ረ የሚል ቢኖር ከዕለት ከዘመን በኋላ ካልተፈጠረ ከአብ ተገኘ የሚል ወይም ከሌላ አካል ወይም ከሌላ ባሕርይ የተገኘ የሚል ወይም ያልፋል ይለወጣል የሚል ሰው ቢኖር ሐዋርያት የሰበሰቧት ቤተ ክርስቲያን ክብርት ናትና ታወግዘቸዋለች ትለያቸዋለች::»[53]

## 1. የአብ አንዲያ ልጅ

የአብ አንድያ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ይህንን አንድያ

---

51 ሃይማኖተ አበው ዘኤፍሬም ም. 4፥30

52.ትምህርተ ክርስትና ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅ ነህ 1979 ዓ.ም ገጽ 13

53. ሃይማኖተ አበው ዘሠለስቱ ምዕት ምዕ 17፤14

የአብ ልጅነት ምስጢሩ እና ሊባል የተፈለገው ሳይገባቸው ዋች ታወሮችና ሙስሊሙ እንዲሁም መሠሎቻቸው የእግዚአብሔር ልጆች ክርስቲያኖችም፣ መላእክትም ... ወዘተ ተብለዋል ይሉና አንዱን ከአንዱ አጠረማምሰው ሊያቃልሉት በከንቱ ይደክማሉ:: ነገር ግን የአብ አንድ ልጅ ወይም አንድያ ልጅ የሚለውን አላስተዋሉም::
አንድያ ማለት ቀዳማዊና ተከታይ የሌለው ማለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር ኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳማዊም ተከታይም የሌለው የአብ አንድያ ልጅ እንደሆነ ይናገራል / ዮሐ 3፤16፣ ዮሐ 1፤18/::

ስምኦን ጴጥሮስ ኢየሱስን «አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ ሲመሰክር ክርስቶስ ይህን አባባል በቀላሉ አላለፈውም «በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ስጋና ደም ይህን አልገለጠልህም» በማለት እርሱ ልጅ አብም አባቱ እንደሆነ እንዲሁም ይህ ምስጢር ምጡቅ በመሆኑ ከአብ እርዳታ በቀር በፍልስፍና መንገድ እንደማይገባን አስታውቋል:: በዚህም እውነት «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም» አለው / ማቴ16፤16-17/ እንዲሁም ጳውሎስ በደማስቆ ጎዳና ላይ ይህን እምነት መቀበሉን ሲገልጽ «በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር ፣ በአህዛብ መካከል እርሱን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ...» በማለት አንድያ ልጅነቱን « ልጁን » ሲል ገልጦታል:: /ገላ 1፤15-16/ «ወዲያውም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በምኩራቦቹ ሰበከ» /ሐዋ 9፤20/

ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሸንጎው ፊት ቀርቦ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን?» ለሚሉት ከሳሾቹ ሲመልስ « እኔ እንደሆንሁ እናንተ አላችሁ » ብሏል /ሉቃ 22፤70/ ::እርሱ ከመላዕክት ይበልጣል / ዕብ 1፤5፣7 /:: በእግዚአብሔር ዙፋንና ባህሪ እቅፍ ውስጥ የሚገኝ አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ነው /

ዮሐ1፤18/ ፡፡ እርሱ ከመላዕክትና ከክርስቲያን ልጅነት ራሱን ሲለይ "ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ » በማለትም ልዩነቱን አሳይቷል /ዮሐ 20:17/ ፡፡ ስለዚህ እርሱ ከአብ ጋር እኩል ባህሪ /ዮሐ 10፤30/ እኩል አስገኝነትና ሉአላዊነት አለው፡፡ በአጭሩ አብ ያለው ሁሉ ለወልድ ደግሞ አለው /ዮሐ 16:15/ ይህም ቃል /ወልድ/ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚገልፅ በመሆኑ በምስጢረ ሥጋዌ ርዕስ ስር በስፋት ያየነው ነገር ነው፡፡/ገጽ 16ን ያንብቡ / ከመጀመሪያ ጀምሮ ይህን የክርስቶስን መለኮታዊ ልጅነትን መቀበል የቤተክርስቲያን ዋነኛ መሠረት ነው /ዮሐ 20:31፣ 1ዮሐ 4:15/፡፡

**2. አንድ ጌታ**:-ይህ ስም ለኢየሱስ ተሰጥቷል /ሮሜ 10:9/ በግሪክ ቋንቋ የብሉይ ኪዳን ትርጉም እግዚአብሔር ራሱን ለሙሴ የገለጠበት ያህዌ የሚለውና በቃላት ሊገለጽ የማይቻለው የዕብራይስጥ ስሙ ኪሪዮስ "ጌታ" በመባል ይታወቃል፡፡ ከዚያም ወዲህ የእስራኤልን አምላክ መለኮታዊነት ለማመልከት "ጌታ" የሚለውን ስም መጠቀም የተለመደ ሆነ፡፡ አዲስ ኪዳን ይህን የክብር ማዕረግ በተሟላ ትርጉሙ ለአብና እንደ ራሱ እንደ እግዚአብሔር ለታወቀው ለኢየሱስም ይጠቀምበታል" /1ኛቆሮ 2፤8/፡፡እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መዝሙረ ዳዊት 109(110) ትርጉም ከፈሪሳዊያን ጋር በተከራከረ ጊዜ ጌታ የሚለውን የማዕረግ ስም ለራሱ ተጠቅሞበታል /ማቴ 22፤41-46/፡፡ « ጌታ እኮ ነው » "ጌታየ እና አምላኬ" የሚሉ ቃላቶችም ክርስቲያኖች/ላመኑበት አምላክ/ ለክርስቶስ የሰጡት የፍቅርና የጥልቅ ስሜት አምልኮ የያዙ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጹ ቃላት ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ጌትነቱን በበርካታ ክፍሎች ያነሳል፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ "እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ" /ሐዋ 2፤36/ ብሏል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሳው

በልብህ ብታምን ትድናለህና።» /ሮሜ 10፤9/ ብሏል። ማርያምም «አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ» ብላለች /ዮሐ 11:27/። በመልእክታት ውስጥም «ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሠክር ዘንድ ነው።» / ፊሊ. 2፤11/ይላል ። « ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንዳሌለ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይቻል አስታውቃችኋለሁ።» /1ኛቆሮ 12:3-4/

«ከዚችም ዓለም ገዥዎች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም አውቀውስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር።» /1ኛቆሮ 2፤8/ ይላል ። በራዕይ መጽሐፍ ደግሞ «እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ። እነዚህ በጉን ይወጋሉ በጉም የጌቶች ጌታና የነገስታት ንጉሥ ስለሆነ እነርሱን ድል ይነሣል። ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም ደግሞ ድል ይነሣሉ» ይላል /ራዕ 17፤13-15/። አጋንትን ድል ማድረግም ስብከትም ቅድስናም በኢየሱስ ጌትነት ስር ያደረ ነው። ቃሉ እንዲህ ይላልና «ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጅ ራሳችንን አንሰብክምና» /2ኛቆሮ 4፤5/ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ያለ እድፍና ያለነቀፋ ሆነህ ትእዛዙን ጠብቅ ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፅዕና ብቻውን የሆነ ገዥ የነገስታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ያሳያል፡ እርሱ ብቻ የማይሞት ነው። ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም። ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን አሜን »/1ጢሞ 6:14-16/።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም «ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘሀልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር

ዓለም:: ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ ተቀዳሚና ተከታይ በሌለው በአብ ልጅ በአንድ ገዥ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን::» በማለት የጸና አቋም አላት::[54] «ጌታችን ሆይ ና» /1ኛቆሮ 16 :22/

## አንቀጽ ሦስት

## «ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምልክ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል»

### 1. ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ ...

ከዚህ በፊት በምስጢረ ሥላሴ አምዳችን ስር ትክክለኛ ነገሩን ይገልጣል ባንልም ለሠው አዕምሮ ሲባል የተፈለገውን ሃሳብ አባቶች ለማስረዳት ሥላሴን በፀሃይ መስለው እንዳስቀመጡልን አይተናል:: ይኸውም በፀሐዩ ክበብ አብን ፣ በጨረሩ ወልድን ፣ በሙቀቱ / በዋእዩ/ መንፈስ ቅዱስን:: እንግዲህ ሦስት ፀሐይ ሳይሆን አንድ ሆኖ ነገር ግን ከፀሐዩ ጨረር እንደ ሩሚወጣ ጨረሩም ራሱ ፀሐይ እንደ ሚባል ግልጥ ነው: ጨረሩም ሙቀቱም የፀሐይ አካሎች ናቸውና ራሳቸው ከክበቡ እኩል ማንነት ኖራቸው ፀሐይ ተብለው የሚጠሩ ቀዳሚና ተከታይ የሌለባቸው ናቸው:: የወልድ ከአብ መገኘት ከፀሐይ እንደሚፈነጠቅ ጮራ ነው ወልድ በረቂቅ ልደቱ አብን አህሎና መስሎ ከአብ እንደተገኘ በሰው ቋንቋና ምሳሌ ለማስረዳት ያክል ነው :: ለዚህም መነሻ የሚሆነው ክርስቶስ የእግዚአብሔር የክብሩ መንጸባረቂያ ሆኖ ስለተጻፈ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን እንደ ሆነ ቤተክርስቲያን ትመሰክራለች /ዕብ 1:3/ ደግሞም ስለክርስቶስ «ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ» /መዝ (110):3 በማለት ቅድመ ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ አካላዊ ቃል እንደ ሆነና በእርግጥነም ከእርሱ እንደተወለደ ስለሚገልጽ «ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ» በማለት አበው የክርስቶስ ግኝቱን የተገኘ

---

54. ሃይማኖተ አበው ዘሠለስቱ ምዕት ምዕራፍ 17:4

ብለው ትክክለኛ እምነት አስቀምጠዋል ::ይህም ከብርሃን የሚገኝ ብርሃን እንጂ ሌላ እንዳልሆነ ከእውነተኛ አምላክም የሚገኝ አምላክ እንጂ ሌላ ፍጥረት እንዳይደለ ወልድ ከእግዚአብሔር የተገኘ እግዚአብሔር ነው /ዮሐ 1:1-2/ ከመንፈስ የሚወለድ መንፈስ ነው ከስጋ የሚወለድ ስጋ ነው እንደተባለ /ዮሐ 3:6/ «ከእውነተኛ ባህሪ አባት የተገኘ እውነተኛ የባህሪ ልጅ ነው ከማይታይ የተገኘ የማይታይ: ከማይለወጥ የተገኘ የማይለወጥ :ከማይሞት የተገኘ የማይሞት ከቀዳማዊ የተገኘ ቀዳማዊ ነው»/1ኛዮሐ5:20፣ሮሜ 1:20/[55]

## 2. የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ

«ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ» / መዝ (110):3 /
«እግዚአብሔር አለኝ አንተ ልጀ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ» / መዝ 2:6 /
«አንተ ዛሬ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጀሃለሁ :: ደግሞም እኔ አባት ሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል» /ዕብ 1:5/

እነዚህና የመጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ክፍሎች ክርስቶስ እንደተ ወለደ የሚናገሩ ናቸው:: መወለድ ማለት ከባህሪ ባህሪ ከጌትነት ጌትነት ከእግዚአብሔር እግዚአብሔር እንደተገኘ ለማሳየት ነው:: አበው «አካል ዘእም አካል ባህሪ ዘእምባህሪ ተገኘ» ይላሉ:: ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ « ስለ ልጁ ግን አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል ይላል:: ደግሞ « ጌታ ሆይ አንተ ከጥንት ምድርን መሰረትህ ሰማዮችም የእጆችህ ስራ ናቸው::እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ፀንተህ ትኖራለህ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል:: አንተ ግን አንተ ነህ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም::» ይላል /ዕብ 1:8-12/:: ይህ ክፍል ስለ ልጁ አምላክነት፣ ሁሉንፈጣሪነት ጸንቶ ዘላለማዊ ኗሪነቱን ይናገራል::

---

55. ሃይማኖተ አበው ዘሠለስቱ ምዕት ምዕ 19፣3

ይህን ስለ ልጁ የተነገረውን ክፍል በመዝሙር (102):25-28 ለእግዚአብሔር የተነገረ ሆኖ እናገኘዋለን::

በ325 ዓ.ም በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አሪዮስ "ወልድ ፍጡር ነው" በማለት የጠቀሳቸው ጥቅሶች ተወለደ የሚለውን ቃል ተፈጠረ በሚል እና ሥጋ በመልበሱ ራሱን ባዶ ያደረገባቸውን ባህሪያት በራሱ አይቶ ሩቅ ብእሲ ፍጡር መስሎት በአሳቡ በመመራቱ አበው አስተምህሮቱን ከቤተክርስቲያን አጥር ውጭ አውግዘው ለዩት " በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰኑ የሚነገርባቸው ... አናቅጽ ነገሩ ሰው ስለመሆኑ የተነገረ ፍጹም ሆኖ እናገኘዋለን ዳግመኛም የስጋን መንሳት /መውሰድ/ የማያምነውን እናወግዛለን እንረግማለን ይህችንም ሐይማኖት የማያምኑ መናፍቃንንም ሁሉ አውግዘናል ረግመናል የረከሰች አርዮሳዊያንን ሐይማኖት አስቀድመው የጻፉትን አውግዘናል ረግመናል እኛስ ቃል ወልደ እግዚአብሔር እንደተወለደ እንጂ እንዳልተፈጠረ አምነን እንናገራለን" አሉ /1ኛቆሮ 12:3፣ 1ኛዮሐ 5:9-20/ [56]

ይህን በ325 ዓ.ም የወደቀ ትምህርት ከተጣለበት ቅርጫት /መቃብር/ አንስተው ስለልጁ ተፈጠረ ለማስኘት የሚንደፋደፉ አስገራሚዎች አይጠፉም:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን በግልጽ ልጁ ከእግዚአብሔር የተወለደ ብቸኛ አንድያ ልጅ እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል /ዮሐ 1:1-2፣ 1ኛዮሐ 5፥20፣ ሮሜ 9፥5፣ ማቴ 1፥23/ ሌሎች ደግሞ ይህን የአርዮስን አስተምህሮ ዘመናዊነት አልብሰው አርቅቀው አምላክ መባሉን ተቀብለው እግዚአብሔር አይደለም የሚሉ ደግሞ ተወለደ የሚለውን ይዘው እንደ ሰው በሩካቤ ስጋ /በጾታዊ ግንኙነት/ እንደሚወለድ ሩቅ ብእሲ አድርገው የሚቆጥሩ ሌሎችም መጽሐፍ ቅዱስ አላስኬድ ቢላቸው ራሱን መጽሀፉን ተሳስቷል ያሉ አልያም

---

56 ሃይማኖተ አበው ዘሠለስቱ ምዕት ምዕ 19፥27-28

ለመቀየር የሞከሩም አያሌ ናቸው:: ሁሉም የቤተክርስቲያንን አሳብ አልተረዱም መጽሐፍ ቅዱስም አልገባቸው:: ስለዚህ ወድቀውም ቀሩ:: ግማሾቹም የጣር ድምጻቸው ቀርቷዋል::ክርስቶስ ግን በአባቱ እቅፍ በዙፋኑ ላይ የነበረ እግዚአብሔር/ ዮሐ 1:1-2 ፤ ዮሐ 1:18 ፤ ዮሐ 17፤5 ፤ዮሐ 16፤28፤ ፊሊ 2:6 /ከቅድስት ድንግል ማርያም ሲወለድ እግዚአብሔር : ከእኛ ጋር የተባለ / ማቴ 1:23 / ሲያገለግልም በመዋዕለ ስጋዌው ጊዜ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ እግዚአብሔር ብሎ የተናገረ/ዮሐ 5፤17-18፤ማር 2:7-12፤ ማቴ 22-41-46/ ወደ ሰማይ ሲያርግም እግዚአብሔር ተብሎ / መዝ (68)፤32፤ መዝ(47)፤5፤ 1ጢሞ 3፤16/ ያረገ የክብር ጌታ ነው::

### 3. በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል

እስከ አሁን መለኮታዊ ምስጢር እንደተገለጸው ከአንድ ነገር የተገኘ ነገር ያንኑ አስገኚውን መስሎና አህሎ ከአስገኚው ጋር እኩልነት ይኖረዋል :: እስኪ ከዚህ በታች ያሉትን ዝርዝር እኩልነት እንመልከት ::

| አብ እግዚአብሔር | ወልድ እግዚአብሔር |
| --- | --- |
| 1.«እግዚአብሔር ብርሃን ነው» /1ዮሐ 1፤5፤ መዝ (27) :1/ | 1. «ደግሞም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ . . .» /ዮሐ 8:12፤ 2ጢሞ 6:13-16/ |
| 2. «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ» / ኢሳ 44:6 / (አልፋና ኦሜጋ) | 2. «... እንዲህም አለኝ አትፍራ ፊተኛና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ::» «ያለውና የነበረው የሚመጣውና ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ:: አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል» / ራዕ 1፤8 ራዕ 1፤17-18 / |

| | |
|---|---|
| 3.«እኔ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም» /ኢሳ 43:11/ | 3. እርሱ ህዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» /ማቴ 1:21/ |
| 4.«ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ » /ኢሳ 45:21/ | 4.«እርሱም በእውነት ክርስቶስ የአለም መድኃኒ እንደሆነ እናውቃለን» / ዮሐ 4:42 / |
| 5.«እግዚአብሔር እረኛየ ነው» / መዝ (23):1 / | 5. «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» / ዮሐ 10:11 / |
| 6.«እግዚአብሔር ዓለቴ ... ነው» /መዝ (23):1/ | 6. «ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ» /1ኛቆሮ 10፤4/ |
| 7.«እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» / ሚል 3:6 / | 7.« ኢየሱስ ክርስቶስ ትላትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነው » / ዕብ 13:8 / |
| 8. «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል... እኔ ምድርን ሠርቻለሁ ሰውንም በእርሷ ላይ ፈጥሬያለሁ እኔ በእጄ ሰማያትን ዘርግቼአለሁ ሠራዊታ ቸውንም ሁሉ አዝዣለሁ።» /ኢሳ 45:11-12/ | 8.«...የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይምአለቅነት ወይምሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልናሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል እርሱም ከሁሉ በፊትነው ሁሉም ለእርሱ ተጋጥሞአል ...ከሙታንም በኩር ነው » /ቆላ 1:15-20/ |
| 9.«እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን ...» / ዮሐ 17፤3 / | 9. እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ህይወትነው። / 1ኛዩሐ 5:20 / |

| | |
|---|---|
| 10.«አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም ለሚወዳቸው እንደሚሰጣቸው...» /ዮሐ 5:21/ | 10. እንዲሁ ወልድ ደግሞ ሕይወትን ይሰጣቸዋል /ዮሐ 5:21 / |

## 4. የአብና የወልድ አንድ የመሆናቸው ንባብ

« ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም፡፡ ... ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም እኔና አብ አንድ ነን» / ዮሐ 10:29-30 /

« ኢየሱስም ጮኾ እንዲህ አለ፡- በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል»/ዮሐ 12:44/

« እኔን ያየ አብን አይቷል ...እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? ... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ» / ዮሐ 14፤9-11/

«የሚወደኝም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም ገልጥለታለሁ »/ዮሐ 14፤21/

« የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» /ዮሐ 14:23/

« ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው» /ዮሐ 16:15/

« ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም ከወልድም በቀር ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም» /ማቴ 11:27/

« ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም ወልድን የሚታመን አብ ደግሞ አለው፡፡ ... በወልድና በአብ ትኖራላችሁ፡፡» /1ኛዮሐ 2:23-24/

« በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት» /2ኛዮሐ 1፤9-11/

« በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም »/ማቴ 28፤19/

እንግዲህ ከላይ ያለው የአብና የወልድ በመለኮት አንድ መሆን ከብዙ በጥቂቱ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን ዳግሞ ማስታወስ ያለብን አብ

ማለት ወልድ ማለት አይደለም::ይህም በምሥጢረ ሥላሴ አካል በሚል ርዕስ ስር አትተናል::

## አንቀጽ 4

## «ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለ እርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም በሰማይም ያለ በምድርም ያለ»

"ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" /ዮሐ 1:3/ ::

"እግዚአብሔር ሁሉን ለእርሱ ለራሱ ፈጠረ" /ምሳሌ 16:4/

"እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና ... ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው " /ኤር 10:16/::

"ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና ..."/ሐዋ 17:24/::

"የሚታዩና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና" /ቆላ 1:16/ ::

እነዚህና በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚያስረዱን እግዚአብሔር ብቻ ነገሮችን ሁሉ እንደፈጠረ ያሳያሉ:: የሥነ ፍጥረት አጀማመር በምንመለከትበት ጊዜ በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ እና ሁለት ስናነብ፡- በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ

- ምድር ባዶ (ቅርጽ የለሽም/ ነበረች
- ጨለማም ነበረ
- ብርሃን ይሁን ብሎ ብርሃን አደረገ
- ብርሃኑንም ቀን ጨለማውንም ሌሊት አለው

2. ከዚያም በውሆች መካከል ጠፈር ይሁን ብሎ ጠፈር አደረገ

- ውሆችን ከፈለ /ከጠፈር በላይ ከጠፈር በታች/
- ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው

ማለት ወልድ ማለት አይደለም፡፡ይህም በምሥጢረ ሥላሴ አካል በሚል ርዕስ ስር አትተናል፡፡

## አንቀጽ 4

## «ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለ እርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም በሰማይም ያለ በምድርም ያለ»

"ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" /ዮሐ 1:3/ ፡፡

"እግዚአብሔር ሁሉን ለእርሱ ለራሱ ፈጠረ" /ምሳሌ 16:4/

"እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና ... ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው " /ኤር 10:16/፡፡

"ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና ..."/ሐዋ 17:24/፡፡

"የሚታዩና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና" /ቆላ 1:16/ ፡፡

እነዚህና በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚያስረዱን እግዚአብሔር ብቻ ነገሮችን ሁሉ እንደፈጠረ ያሳያሉ፡፡ የሥነ ፍጥረት አጀማመር በምንመለከትበት ጊዜ በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ እና ሁለት ስናነብ፡- በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ

- ምድር ባዶ (ቅርጽ የለሽም/ ነበረች
- ጨለማም ነበረ
- ብርሃን ይሁን ብሎ ብርሃን አደረገ
- ብርሃኑንም ቀን ጨለማውንም ሌሊት አለው

2. ከዚያም በውሆች መካከል ጠፈር ይሁን ብሎ ጠፈር አደረገ
   - ውሆችን ከፈለ /ከጠፈር በላይ ከጠፈር በታች/
   - ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው

3. የብሱም ይገለጥ ዘንድ አዝርእቶችንም አበቀለ

- ከሠማይ በታች ያለውን ውሃ በአንድ ስፍራ ሰበሰበ
- የብሱንም ገለጠ
- የውሃ መከማቻውንም ባህር አለው
- ዘሩን በየወገኑ በውስጡ ያለበትን ዛፎችን ቡቃያዎችን አበቀለ

4. ቀንና ሌሊትን ለየ

- ቀንና ሌለትን የሚለዩ ብርሃናትን በሰማይ ፈጠረ
- ትልቁን ብርሃን በቀን ትንሹን ብርሃን በሌሊት አሰለጠናቸው
- ብዙ ከዋክብትንም አደረገ

5. ተንቀሳቃሽ እንስሳትን ፈጠረ

- ውኃው ውስጥ ታላላቅ አንበሪዎችን አንስቶ እስከ ታናናሽ ፈጠረ
- በሰማይ የሚበሩ በየወገኑ ወፎችን ፈጠረ
- በምድር የሚንቀሳቀሱ እንደ ወገኑ አራዊቶችን እንስሳትን ፈጠረ

6. በመጨረሻም ሰውን ፈጠረ

- ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ
- ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት
- ህያው ፍጥረትም ሆነ
- ሴትንም ከጎኑ አጥንት ወስዶ ፈጠረ
- እንዲገዛ ስልጣን ሰጠው በማለት ያስተምረናል።

እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር /እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ/ አምጥቶ እንደፈጠረና /ዕብ 11 : 3/ መልካም መሆኑን ያይ እንደ ነበረ እንዲሁም ስራውንም በመመዘን እንደአረጋገጠ ክፍሉ ያስረዳናል። ሰውን በፈጠረ ጊዜ ግን እጅግ መልካም በማለት ከሁሉ በላይ ክቡር እንደሆነ አረጋግጧል። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ «እግዚአብሔር» የሚለውን የፈጣሪ ስም በእብራይስጥ « ኤሌሂም »

የሚል ሲሆን ይህ ስም ብዙ ቁጥርን የሚገልጽ ግስ ነገር ግን ነጠላ ጥምር ስም ሆኖ የተገለጸ ነው፡፡ ይህም « ኤሌሂም » የሚለው ቃል ከአንድ በላይ ነገር ግን ጥምር አንድ ስም ነው፡፡ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ደግሞ ይህን ጥምር ስም በተናጠል አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይገልጻሉ /ማቴ 28፤19/ በፍጥረት ውስጥ አብ እንደፈጠረ /1ቆሮ 8:6/ ወልድ እንደፈጠረም / ዩሐ 1:3 ኤፌ 2:10 ቆላ 1:17 / መንፈስ ቅዱስም እንደፈጠረ /ኢዮብ 33፤4፣ ዘፍ 1፤2/ ያስረዳናል፡፡ ይህም በፍጥረት ስራ ውስጥ ሦስቱም በአንድነት እንደፈጠሩ ሲያረጋግጥልን « ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» በማለት በብዜት ስም ራሳቸውን ጠርተዋል፡፡ በአንድነት ስም ደግሞ በዚያው ምእራፍና አንቀጽ ውስጥ እግዚአብሔርም አለ ወይም እግዚአብሔርም ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ይላል፡፡» አለና ፈጠረ የሚሉት ቃላት የአንድነት ስያሜ እንጂ የብዜትን ቃል የማገልጹ አይደሉም ፡ /ዘፍ 1፤26-27/

እንግዲህ ፈጣሪ ስላሴ /እግዚአብሔር/ ብቻ እንደሆነና ብቻውን እንደፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ ስፍራዎች ይናገራል ፡፤ከነዚህም ውስጥ :-

« ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር እርሱ ምድርን የሠራና ያደረገ ያጸናትም መኖሪያም ልትሆን እንጂ ለከንቱ እንድትሆን ያልፈጠራት አምላክ እንዲህ ይላል:- እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፡፡» /ኢሳ 45፤18/

« ሰማይንና ምድር የሠራ እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ » /መዝ (134)፤3/

« ሰማያትን ፈጠረ ምድርንና በውስጧ ያለውን ያጸና በእርሷም ላይ ለሚኖር ህዝብ እስትንፋስን ፣ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር ነው » /ኢሳ 42፤5-7/

« ሰማያትን በጥበብ የሠራ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና ብቻውን

ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና::/መዝ (136): 4-9/

ሐዋርያትም በጸሎታቸው ጊዜ "ጌታ ሆይ አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእርሱም የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ" ብለዋል /ሐዋ 4:24/ መላዕክትም በሰማያት ሲያመሠግኑት "ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ:: /ራዕ 4:11/

## አንቀጽ 5

## "ስለ እኛ ስለሰዎች ስለ መዳናችን ከሰማያት ወረደ፤፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ

### 1. «ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችን ከሰማያት ወረደ"

ስለ ሰዎች መዳን ስናነሳ ውሃን ከጥሩ ነገርን ከስሩ እንዲሉ ከፍጥረቱ ጀምሮ የሆነውን ማንሳት የግድ ይሆናል ምክንያቱም ከመጀመሪያ ጀምሮ የሰውን ምንነትና ሃላፊነት እንዲሁም የእግዚአብሔርን ዓላማና ፍቅርንም የምንረዳበት ዋነኛ መሠረት ስለምናገኝ የእግዚአብሔር የማዳንና የሰውን የማዳን እውነት በሚገባ መረዳት ያስችለናል::

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ በፊት በጥሩ ሁኔታ ውስጥ ያስቀምጠው ዘንድ ሁኔታዎችን በቅድሚያ አመቻቸለት:: ይህም በዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ 1 እና 2 ተገልጾ ስናነብ አጠቃላይ ሁኔታው እንዲህ ነበር::

1. ብርሃኑ መልካም ነበር /ዘፍ 1:4/
2. የተገለጠው የብስና የተከማቸው የባህር ውሃ መልካም ነበር /ዘፍ 1፤10/
3.በየወገኑ የበቀለው የምድር አዝርእት ሁሉ መልካም ነበር/ዘፍ 1:12/
4. በምርድ ላይ የሚያበሩት ፀሀይ ጨርቃና ከዋክብት መልካም ነበሩ /ዘፍ 1:18/

5. ከጠፈር በታች የሚበሩ አእዋፋት በባህር ውስጥ ያሉ አሳ ዎችና ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት መልካም ነበሩ /ዘፍ 1:21 /
6. የምድር አራዊትና ፍጥረታት ሁሉ መልካም ነበረ /ዘፍ 1፤25/

ከዚህ ሁሉ የመልካም ሙላት በኃላ ሰውን በራሱ መልክና አርአያ ፈጠረው ያም ከሁሉ የተሻለ ሁኔታ እጅግ መልካም ነበረ /ዘፍ 1:31/ እጅግ መልካም አድርጎ መፍጠር ብቻ ሳይበቃ:-

1. ሰውን የፍጥረታት ሁሉ ገዥ አድርጎ ሾመው /ዘፍ 1:26-28/
2. የተባረከ ሠው እንዲሆን ባረከው / ዘፍ 1:26/
3. የሚያስፈልገውን ምግብ ሁሉ ያለድካም ሰጠው ዘፍ 1:30/
4. የሚያምር የአትክልት ስፍራ ተክሎ ኤደን ገነትን መኖሪያው አድርጎ ሰጠው /ዘፍ 2:8/
5. እንደ ጥሩ አሳዳጊ አባት ትእዛዝን ሰጠው:: የሞትንና የህይወትን ሁኔታ በግልፅ አስቀምጦ አስ ረዳው /ዘፍ2:16-17/
6. ብቻውን መሆን እንደሌለበትም አስቦ የምትመቸውን ቆንጆ ረዳትን (ሚስትን) ሰጠው /ዘፍ 2:16-21/
7. ሁልጊዜም እየመጣ ይጎበኘው ነበር /ዘፍ 3:8/

ከዚህ ሁሉ እጅግ መልካም በኋላ ሰው በዚሁ ህይወት መንገድ መቀጠል አልያም የሞትን መንገድን የመምረጥ ሙሉ ፈቃድና ሙሉ ነፃነት ነበረው:: ባጋጣመውም የዲያቢሎስ ፈተና «እንደ እግዚአብሔ ር» ለመሆን በምኞት ተሞልቶ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ አመፀ / ዘፍ 3:1-6/ በዚህ ምክንያትም የመጀመሪያዎቹ ቤተሰቦች ራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ ፣እርስ በርሳቸውም ተፋፈሩ፣በእግዚአብሔር ፊት የመቅረብ ድፍረት አጥተው እንደመሰሳቸው ተሸሸጉ፣እርስ በርሳቸው

መካሰስ ጀመሩ፡ ለሴቲቱም በጭንቅ መፅነስና መውለድ ከዚያም ለባልዋ መገዛት፣ ለእርሱም በህይወት ዘመኑ ሁሉ በድካም መኖር፣ ዘመናቹ ጥቂቶች ሆነው ወደአፈር መመለስ፡ ለዲያብሎስም መቀጥቀጥ:ምድርም ከሰው የተነሳ እሾህና አሜኬላን እንድታበቅልና የማትመች መሆንን ወረሱ።በዚህም ሳይቆም ከኤደን ገነት ተባረሩ። ከእግዚአብሔር ጋርም የነበረው የቤተሰብ ግንኙነት ደበዘዘ።ሲገዛቸው የነበሩትም እንስሳት ያስደነግጡትና ብሎም ያጠቁት ጀመር።ከዚህ በኀ ላ ሰው በኃጢአቱ ምክንያትም እጅግ ፈሪ ድንጉጥ በራሱ የማይተ ማመን እርስ በእርስ የሚጠላላና የሚገዳደል ልቡ በክፋት የተሞላ ብሎም ዘላለማዊ ሞት በመጠባበቅ የሚኖር ተስፋ ቢስ ሆነ። በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ክብር የጎደለው ሰው ሆነ /ሮሜ 3:23/ እንግዲህ ከሰው ፍጥረት ጀምሮ ወደአለም የገባው ኃጢአት የሚተ ላለፍ ባህሪ ይዞ ወደ ሠው ሁሉ ደረሰ። በዚህ ሳቢያ ዛሬ እያንዳንዱ ሰው ወደ ኃጢአት የሚጎትተው ኃይል በውስጡ ይታገለዋል። መልካሙን ለማድረግ ሲመኝ ክፍውን ነገር እንዲያደርግ ይገደዳል። ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለራሱ ህይወት በምሳሌነት ሲተርክ «እኔግን ከኃጢአት በታች ስሆን የተሸጥኩ የስጋ ነኝ የማደርገውን አላውቅምና የምጠላውን ያን አደርጋለሁና :ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንኩ ... የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም። በእኔ የሚያድር ኃጢያት ነው እንጂ በእኔ ማለት በስጋየ በጎ ነገር እንዳኖር አውቃለሁና ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉ ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን የማደርግ ከሆንኩ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ። እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ህግን አገኛለሁ። በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ህግ ደስ ይለኛልና።ነገር ግን በብልቶቸ ከአይምሮየ ህግ ጋር የሚዋጋውንና

በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ህግ የሚማርከኝን ሌላ ህግ አያለሁ እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ስለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» በማለት የሚያድነውን በብርቱ ሲፈልግ እናገኘዋለን::/ሮሜ 7፤14-20 /

ማንም ሰው ከዚህ እውነት ራሱን ሊያገል አይችልም:: በሰው ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የመጣ ኃጢአት አለ:: ይህም ኃጢአት ቤተ ክርስቲያን የውርስ ኃጢአት ብላ ትጠራዋለች:: እያንዳንዱ ሰው በህይወት ዘመኑ የሚፈፅማቸው የገቢር (የድርጊት) ኃጢአቶች ከውስጥ ሰውነቱ የኃጢአት ኃይልና ዘር ስላለ እንዲፈፅማቸው ስለሚገደድ የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ብቻ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ይህም ሰውን አስገድደው ኃጢያት ያሰሩት የጥንተ ኃጢያት ኃይል በመሆኑ የተገደደው ሰው ኃጢያቶቹን ከፈፀማቸው በኃላ የፀፀት ስሜት በእጅጉ ተሰምቶት «እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ»/ሮሜ 7:20 / በማለት ይጸጸታል : ጽድቅንም ይጠማል ::የእግዚአብሔር ቃል ስለውርስ ኃጢአት:-

«ኃጢአት በአንድ ሰው ወደአለም ገባ በኃጢአትም ሞት፣እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአት ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ ...በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሰሩት ላይ እንኳ ...ሞት ነገሰ» /ሮሜ 5: 12-14/

«በአንድ ሰው በደል ብዙዎች ሞተዋልና ... አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደሆነው መጠን ...በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ነገሰ... በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኩነኔ እንደመጣ ...በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ ... በደልም እንዲበዛ ህግ ጭምር ገባ» /ሮሜ 5:15-19/ በማለት ይገልፃል::

እንግዲህ ከዚህ ኃጢአት ሀይል ለመዳን እንዳንዶች እንደሚያደርጉት ውጫዊ ሰውነትን በመታጠብ አልያም ሰውነትን በመግረፍና በማጎሳቆል ብሎም በመቆረጥ እንዲሁም ሐይማኖታዊ ስርአቶችን በጥንቃቄ በመፈፀም ... ወዘተ ሊወገድ ከቶ የማይቻል ነው::

አባ መልከ ፀዲቅ ሊቀ ጳጳስ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ "ቤተ ክርስቲያናችን እንደምታስተምረው የሰው ነገድ አባት የሆነው አዳም በተፈጠረበት ንፅሐ ጠባይዕ ለብዙ ጊዜ አልቆየም፣ ወዲያው ህግ አፍራሽ ሆኖ ወደቀ እንጂ:: እንዲሁም የነገድ ሁሉ አባት እንደመሆኑ በእርሱ መውደቅ ምክንያት ልጁን የልጅ ልጁን ሁሉ ይዞ ወደቀ፣ ይኸ የሰው ነገድ አባት የተባለው ከስህተት በኃላ ባህሪው ወደ ሀጢአት ያዘነበለ ስለሆነ ከሰው የተገኙት ሁሉ በጠባያቸው ህግ አፍራሽ ስለሆኑ በእግዚአብሔር በኩል ለቅጣት የተዘጋጁ ሆኑ:: ይኸን የመሰለውን ቅጣት ያመጣው ጥንተ አብሶ የተባለው የአዳም ስህተት ነው... ትልቁ ፍጥረት አዳም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ የዲያቢሎስን ፈቃድ መፈፀም አስደሰተው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ የራሱን የግሉን ፍላጎት ማሟላት ጠቃሚ መስሎ ታየው፣ ስለዚህ እርሱም ሚስቱም አትብሉ የተባሉትን የዛፍ ፍሬ በሉ በዚህን ጊዜ ከክብራቸው ተዋረዱ አዳም ለጊዜው ኃጢአት መስራቱ ብቻ ሳይሆን ባህሪውም ወደ ኃጢአት ያዘነበለ ሆነና በእርሱ ጠባይ የሚወለደው ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ሆነ ማኀደረ መንፈስ ቅዱስ የነበረው አካሉ ከኃጢአቱ ብዛት የተነሳ ማኀደረ መንፈስ ቅዱስ ከሆነው ራቀ እግዚአብሔርን ከሚያስደስት ፈቃዱንም ከሚፈ ፅም ይልቅ የሰው ልጅ ከራሱ ጋር የሚነጋገር የራሱንም ፈቃድ የሚፈጽም ሆነ ... ኃጢአቱም የወል ሆኖ ከባህርዩ እየወረሰ የኃጢአተኛ ልጅ ኃጢአተኛ እየተባለ ኖሯል :: ከዚህም ከጥንተ አብሶ ከተባለው ኃጢአት ማንም የሰው ልጅ የሆነ ሁሉ ሊያመልጥ አልቻለም ሁሉም በደለኛ ተባለ::

በአዳም በደል የሰው ልጅ ሁሉ በደለኛ እንደ ተባለና በበደሉ ሁሉም እንደ ገባ ስለዚህም ቅጣቱ በሁሉም ዘንድ የተላለፈ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ትወፊትም በሰፊው ያስረዳሉ ከሰው ወገን ምንም ጻድቅ እንደማይገኝ ሁሉም በደለኛ እንደሆነ ኢዮብ እንዲህ ሲል ይመሰክራል:: "ከርኩስ ማነው ንጽህናን የሚያወጣ? አንድም የለም፣

የሰው ዕድሜ በምድር ላይ 1 ቀን ቢሆንም:: ኢዮብ 14:4» ብለዋል፤፤[57]

ስለ ውርስ ኃጢአት እያንዳንዱ ሰው በውስጡ ከኃጢአት ለመዳን የሚያደርገው ትግል ምስክር ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስ በበለጠ ሁኔታ ስለዚህ እውነት ያረጋግጥልናል::

« እነሆ በአመጻ ተጸነስኩ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ» /መዝ (51) ፤5/

« ሰውስ ከእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ይሆን ዘንድ ከሴትስ የተወለደ ንጹህ ይሆን ዘንድ እንዴት ይቻላል» /ኢዮብ 25፤4/

« ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ አስተዋይም የለም እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም ሁሉ ተሳስተዋል በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል» /ሮሜ 3:11/

« ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» /ሮሜ 3፤23/

« ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም ... ኃጢአትም አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም::» /1ኛ ዮሐ 1፤8-10/

እንግዲህ በዚህ ምክንያት ዓለም በሙሉ በክፉ እንደተያዘ እናውቃለን /1ኛዮሐ 5፤19/ እንዲያውም ዲያብሎስ የዚህ ዓለም ገዢ ለመሆን በ?ቷል በክፋቱ ሞልቶ አስቷታልና / ዮሐ 14:30፣ 2ኛቆሮ 4:4፣ ዮሐ 12፤31፣ ራዕ 12፤19/ ስለዚህ ከምድር አዳኝ ሊነሳ ከቶ አልቻለም አይችልም :: ብቃት ያለው የለምና ሁሉ በኃጢአት ተይዘዋልና:: /ኢሳ 59፤16/ ከመላዕክትም ወገን አልተገኘም የለም ከእነርሱም ሲሰው /አንድ ሶስተኛው/ ስተው ወድቀዋልና/ራዕ 12፤4፣ ይሁዳ 1፤6፣ 2ኛጴጥ 24፣ ዕብ 2፤2/ ስለዚህ እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ሰውንም ለዘላለም ሊጥለው ስላልወደደ አብ በእቅፉ ያለውን አንድያ ልጁን ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝ እንዲሆን

ወደ ዓለም ከሰማየ ሠማያት ላከው /ዮሐ 3:16 -17፣ ዮሐ 1:18/ ኢየሱስ ክርቶስም ለህዝቡ ሲናገር "እናንተ ከታች ናችሁ እኔ ከላይ ነኝ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም::

እግዲህ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ እኔ እንደ ሆንኩ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው /ዮሐ 8፤23/ ደግሞም የላከኝ ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና ብሏል /ዮሐ 6፤38/

መጽሐፍ ቅዱስም "ከሰማይ የወረደው ... እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው" እንዲሁም ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው" በማለት ይመሰክርለታል /ዮሐ 3:13፣ ዮሐ 3፤31/ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ከሰማያት የወረደበት ዋና ዓላማ የሰው ልጆችን ለማዳን ሆኖ ይህም ሲዘረዘር:-

1. የዘላለምን ህይወት ይሰጥ ዘንድ / ዮሐ 3:16-17፣ ዮሐ 10:10፣ ዮሐ 3:36፣ 1ኛዮሐ 5:11-12/
2. የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ /ዮሐ 3፤8፣ ሉቃ 19:10፣ ቆላ 1:13/
3. ራሱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ይሰጥ ዘንድ /ማቴ 20:28/
4. አዲስ ልደትን ይሰጥ ዘንድ /ዮሐ 1:12፣1ዮሐ 3:1-2/
5. ከእግዚአብሔር አባት ጋር የፈረሰውን ግንኙነት /ህብ ረት/ ያድስ ዘንድ /1ዮሐ 1:3 ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ « ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" ካለ በኋላ በኢየሱስ ክርቶስን አዳኝነት በማመን እግዚአብሔርን አመስግኗል /ሮሜ 7፤24/ እንዲያውም በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የህይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና፡ ብሎ ስለ ራሱ ከመሰከረ በኋላ ሐዋርያነቱ ለሌሎች መልእክቱን ሲያስተላልፍ "ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው::

ብሏል /ሮሜ 8:1፣ 10/ ይህም የማዳን ተግባሩ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰርያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም:: /1ኛዮሐ 4:10/ ይህንንም በግላችን ይሁን በቤተክርስቲያን ደረጃ "እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት እንዲሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን" ልንል ይገባናል /1ዮሐ 4:14/

## 2. "በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ "

" መላኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደ ምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ ... መልአኩም እንዲህ አላት:- ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ እነሆም ትጸንሻለሽ:: ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፤ እርሱ ታላቅ ይሆናል:: የልዑል ልጅም ይባላል :: ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል:: በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም:: ማርያምም መልአኩን፤- ወንድ ስለ ማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው:: መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፤- መንፈስ ቅዱስ በአንች ላይ ይመጣል የልኡልም ኃይል ይጸልልሻል:: ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ... ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና: ማርያም እነሆኝ የጌታ ባርያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች መልአኩም ከእርሷ ሄደ:: /ሉቃ 1፤26-38/ ከዚህ ክፍል እንደ ምንረዳው ኢየሱስ ክርቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ ወንድ ዘር - ሲጋናደም ነስቶ / ወስዶ / እንደሚወለድና ፍጹም ሰው እንዲሚሆንና "የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚባል በትክክልመረዳት ይቻላል::

ስለዚህ ጉዳይ በስፋት በምሥጢረ ሥጋዌ ርእስ ስር እይተነዋል::

<u>በዚህ አስተምህሮ ላይ የጥንት አባቶች ያላቸው እምነታዊ አቋም</u>

« እርሱ ልዩ መድኃኒታችን በተለየ አካሉ ከሰማያት የወረደ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን አደረ ። ለእኛ ድኅንነትን ያደርግልን ዘንድ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነፍስን ስጋን ተዋሐደ:: በባሕርዩ መለወጥ የሌለበት ቃልም ከእርሷ ተወለደ /ማቴ 1:18-25/ ሰው ሆነ እኛን ለማዳን ከሰው ባሕርይ ስጋን ተዋሐደ እግዚአብሔር ቃል ይህ ነው: ከአብ የተገኘ ፍጹም እርሱ ሕጸጽ የለበትም የሰውን ስራ ፈጸመ እኛን ለማዳን ስለ እኛ ሰው ሆነ እንደ ሰው ነፍስን ስጋን ፈጽሞ ተዋሐደ /ዮሐ 1:1-14/:: ከአብ የተገኘ ፍጹም አምላክ ነው:: ፍጹም ሰውም ሆነ በሐሰት በምትሐት አይደለም በግብረ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ቃልን ከወለዳችው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሊያዋህደው በእውነት ፈጽሞ አካልን ፈጠረ እንጂ ... እርሱ ቃል ስጋ ሆነ እንጂ የመላክትን ባህርይም ሰው ወደ መሆን አልለወጠውም::»[58]

ደግሞም ኤራቅሊጦስ እንዲህ አለ፤፤ «የታመነ የከበረ የተመሰገነ ስለ ሚሆን ስለዮሴፍ የምንናገረውን እንወቅ:: እርሱ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም የሚፈጸመውን ምስጢር አላወቀምና አገልጋይ የሆነለት ምስጢር ምን እንደሆነ አላወቀም:: ለእርሱ ከታጨችለት ከድንግል ነብያት ስለ እርሱ የተናገሩለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ዘር እንዲወለድ አላወቀም:: በነብይ እንደተነገረ ሕጻን ያለ አባት ከድንግል እንዲገኝ አላወቀም:: /ኢሳ :14፣ ኢሳ 9፤6-7/ ድንግል ሆዷ ገፋ ያለዘር የፀነሰች የድንግልን የሆዷን መግፋት ባየ ጊዜ ዮሴፍ ልቡ አዘነ ::የንጽሕት እመቤታችንን ምስጢሯን ፈጽሞ መረመረና በማያውቀው ምስጢር

---

58 ሃይማተ አበው ዘኤጲፋንትዮስ ም 56:28-31

ጸንሳ ቢያገኛት በጽኑ አሳብ በማውጣት በማውረድ ተያዘ ፀንሳ አገኛ ት። በዘር የፀነሰችም መሰለው። ከርሷ የሚወለደው በግብረ መንፈስ ቅዱስነውና አንተም እንደ ምትጠራጠረው አይደለምና ዮሴፍ አትፍራ ብሎ ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ እስኪነግረው ድረስ። ዮሴፍም ይህን በሰማ ጊዜ ንጽህናዋንም አመነ ነብዩ ኢሳያስ እነሆ ድንግል እግዚአብሔር ከእኛ ባህሪ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው ብሎ የተናገ ረላትን ድንግል እርሷ እንደ ሆነች አወቀ። ማቴ 1:18-25፣ ሉቃ 1፤26-39፣ ኢሳ 7:14»[59] ሌላው ድንግል ማርያም እንደ ማንኛውም ሰው እንደ መሆኗ መጠን የሰው ዘር ያለ ልዩነት እንደበደለ ሁሉ ሠው ነችና ፍጡር በመሆና "ጌታየ አምላኬ" ኃጢአተኛ እንደ መሆኗም « መድሃኒቴ » ብላዋለች /ሉቃ1:47/። ምክንያቱም የሃጢአት ሕመምተኞች እንጂ ጤነኞች ባለ መድሃኒት አያስፈልጋቸውም /ማቴ 9፤12/ ቅዱስ ያሬድም "አንጺሖ ሥጋሃ ላዕሌሃ ኀደረ ቀዲሶ ኪያሃ ኀበ ማርያም ኀደረ - ስጋዋን አንጽቶ ቀድሶ በማርያም ላይ አደረ ብሏል»[60] ይህም ድንግል ማርያም ከመጸነሷ በፊት ኃጢአት እንደነበረባት ያስረዳል። አበውም « ቃል በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከሰው የተነገረው ትርጓሜም ከሐድያን መናፍቃን ሰዎች እንደ ሚያስቡት ለመንፈስ ቅዱስ ሥጋ ኖሮት ወይም የተፈጠረ ሆኖ አይደለም መንፈስ ቅዱስ የማርያምን ሥጋ አነጻ ቀደሰ የአብ አካላዊ ቃልንም ለመጽነስ የበቃች እንደሆነች እነጂ አሉ።[61] ስለዚህ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲወለድ የግድ የመንፈስ ቅዱስ መጸለል/መጋረድ መሸፈን ማጥለል ያስፈልግነበር። /ሉቃ 1:35/

---

59. ሃይማተ አበው ዘኤራቅሊጦስ ም 48፤28-25
60. ድጓ ዘፍልስታ ኪዳነ ምሕረት
61 ሃይማኖተ አበው ዘጎርጎሪዮስ ምዕ 36፤19

## አንቀጽ 6

## "ሰው ሆኖ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ ታመመ ሞተ ተቀበረም። በሶስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ በቅዱሳት መጽሐፍት እንደ ተጻፈ።"

### 1. በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን

በዚህ ክፍል የጲላጦስ ስምና አገር የተጠቀሰበት ምክንያት የጌታ ሞትና ትንሳኤ የተጻፈበትን ዘመን ለማመልከት ነው። የድርጊቱን ታሪካዊነትና እውነተኛነት ለመግለጽ ነው። እስራኤል የሮማ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ዘመን የጢባሪዮስ ቄሳር እንደራሴ፡ ጴንጤናዊ ጲላጦስ አገሪቱን ያስተዳድር በነበረ ወቅት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማማትና ሞት በእርሱ ዳኝነት እንደተከናወነና ይህም ታሪኩ ምንኛ እውነተኛ እንደ ሆነ በማሳየት ያረጋግጣልናል። እንግዲህ በዚህ አንቀጽ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሕማማቱንና ሞቱን እንደ ተቀበለ ፡በነፍስ ወደ ሲኦል እንደ ወረደ ፡ ነፍሳትን እንደ ሰበከ፡ በሦስተኛውም ቀን እንደተነሳ ይህም በቅዱሳት መጽሐፍት እንደተጻፈ እናያለን።

### 2. ስለ እኛ ተሰቀለ፣ ታመመ፣ ሞተ፣ ተቀበረም

በአንቀጽ 5 እንደ ተገለጸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው የሠው ኃጢአትና ሞት ለማስወገድ ነው፡፤ መጥምቁ ዮሐንስ «ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤፡» ብሏል /ዮሐ 1:29/ ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት በለበሰው ሥጋ እንደሚታረድ በግ ለኃጢአታችን መስዋዕት በመሆን ምትካችን ሟች እንዲሆን የግድ ያስፈልግ ነበር። ምክንያቱም የኃጢኣት ደመወዝ ሞት ነውና / ሮሜ 6፤23 /። ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን ክፍተት ( የጥል ግድግዳ ) አፍርሶ ዘወትር መካከለኛ ለመሆን ሊቀ ካህን

ሆኖ መስዋዕት ሊያቀርብ የግድ ያስፈልገው ነበር:: ምክንያም የብሉይ ኪዳን ( የአሮን ) የክህነት ስርዓት አክትሞ እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት መተካት ኪዳኑም ሊታደስ ይገባዋልና::

## 2.1 ስለ እኛ ተሰቀለ

ከአዳም ጀምሮ የሠው ልጆች በሙሉ ስለበደሉና በኃጢአታቸው ስለ ሞቱ «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ ሊቀበሉት የተገባ ነው» /1ጢሞ 1፤15/:: ምክንያቱም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ ከፊቱም የተባ ረረ ከገነትም የወጣ ምድራዊ ነገሩ ሁሉ የተጣመመበት ፡ በሥጋው ወደ መቃብር በነፍሱም ወደ ሲኦል የወረደ ምስኪን በመሆኑና እግዚአብሔር ፍቅርና ርኅሩኅ ስለሆነ የእጁ ስራ የሆነው የሰው ልጅ ስቃይ ስላልወደደው ከራሱ ጋር የሚታረቅበትን መንገድ አዘጋጀ:: ይህም መንገድ ክርስቶስ ነው/ ዩሐ 14:6/ :: ክርስቶስ የመጀመሪያውን አዳም በመተካትና ሁለተኛው አዳም የሚል ስያሜን ይዞ እርግማን በእንጨት መሰቀል ነበረበትና ተሠቀለ /ሮሜ 5፤14፣ 1ቆሮ 15፤45፣ ገላ 3፤13፣ ዮሐ 19፤17-30/:: በቅድሚያ ግን የክርስቶስ ስቅለት በሰው አስገዳጅነት የተፈጸመ ሳይሆን መለኮታዊ እቅድ መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል /ፊሊ. 2፤8/:: « እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰ-ማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና» /ቆላ 1፤19-20/

### ለክርስቲያኖች የመሰቀሉ ጥቅም

« በእኛ ላይ የነበረውንም የሚቃወመንንም በትዕዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል:: አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ ድል በመንሳት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው » / ቆላ 2፤14-15 /

« የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን

የእግዚአብሔር ኃይል ነውና" /1ቆሮ 1፥18/
"ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበትን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ" / ገላ 6:14 /

## 2.2 ስለእኛ ታመመ

- "የተናቀ በሰውም የተጠላ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው:: ሰውም ፊቱን እንደ ሚሰውርበት የተናቀ ነው::
እኛም አላከበርነውም በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸክሟል ... እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ:: በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዘበዝን ጠፋን:: ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ:: እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ:: ተጨነቀ ተሰቃየም አፉን አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾችም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም" /ኢሳ 53:2-7/

### ለክርስቲያኖች የመታመሙ ጥቅም

"ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በስጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና:: አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል::" /1ጴጥ 2:24-25/

## 2.3 ስለ እኛ ሞተ

« ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሆ እስከለሞት፥- ወልድ ኃያልን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው» /ቅዳሴ ማርያም ቁጥር 127/

« ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ ጨለማም እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ሆነ ፀሐይም ጨለመ የቤተመቅደሱ መጋረጃ ከመካከሉ

ተቀደደ:: ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤- አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ:: ይሄንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ::»/ሉቃ 23:44-46/

«ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱ ጋር የተ ሰቀለውን የሌላን ጭን ሰበሩ ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው እንዲያውም ደምና ውኃ ወጣ ያየውም መስክሯል ምስክሩም እውነት ነው» /ዮሐ 19:32-35/

«ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና ... ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል ... ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን» / ሮሜ 5:6-10/

«መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል:: እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ» /ሮሜ 6:10-11/

« የኢየሱስ ህይወት ደግሞ በስጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን::» /2ቆሮ 4፣10/

## 2.4 ስለ እኛ ተቀበረ

« በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀመዝሙር ነበር ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው:: ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ ዮሴፍ ስጋውን ይዞ በንጹህ በፍታ ከፈነው ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ» /ማቴ 27፤57 60/

« ዮናስ በዓሳ ነባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበ ረ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት

ይኖራል» /ማቴ 12:40/

<u>ለክርስቲያኖች የመቀበሩ ጥቅም</u>

« ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን » /ሮሜ 6:4/

## 2.5 በነፍሱ ነፍሳትን ከሲኦል እንዳወጣ

« ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቷልና:: በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ:: በእርሱም ደግሞ ሄደ ለወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው» /1ኛጴጥ 3:18-19/::

## 2.6 በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ

የክርስትና እምነት በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ላይ የተ መሠረተ ነው:: በሞቱ የኃጢአት ስርየት አግኝተን ከእግዚአብሔር ጋር የታረቅንበት በትንሳኤው ደግሞ እምነታችንና ተስፋችን ፍጹም እውነት መሆኑን የምንመሰክርበት ነው፤፤ የሙታን ትንሳኤ መኖሩን የምናምነውና የምንሰብከው ባዶ ቃል ላይ ብቻ በተመሠረተ አዋጅ ሳይሆን የክርስቶስ ሞትና መነሳትን ምስክር በማድረግ ነው/1ቆሮ 15:12-19/ እርሱ ክርስቶስ የሙታን ሁሉ በኩር ሆኗልና /ቆላ 1:19/ በነፍሱ ነፍሳት ከሲኦል እንደወጡ ሁሉ ብዙዎችም በሥጋቸው ከመቃብር ወጥተዋል ተነስተዋል በቅድስት ከተማም ታይተዋል::/ ማቴ 27:52-53/

« ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ? ተነስቷል:: እንዲ በዚህ የለም የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሳ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ አስቡ» /ሉቃ 24፤5-7/

"አይሁድን ስለፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ በመካከላቸውም ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፤፤ ደቀመዝሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው" /ዮሐ 20፤19-20/
"መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ተቀበረም መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሳ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአስራ ሁለቱ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ ... ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ በኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ::" /1ቆሮ 15፤3-8/

## ለክርስቲያኖች የመነሳቱ ጥቅም

" ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሳትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን" / 1ቆሮ 15፤55-57 /

" አሁን ግን ለአንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል ... ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና" /1ቆሮ 15፤22/

" ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን ... ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና" /ሮሜ 6፤5-9/

" ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል::" /ሮሜ 8:11/

## አንቀጽ 7

## « በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፣ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ዳግመኛ በሕያዋንና በሙታንም ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም »

1. "በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ":- ይህም ማለት እንደ ሄኖክ በመሰወሩ /ዘፍ 5፤24/ እንደ ኤልያስ በእሳት ሰረገላ/2ኛ ነገ 2፤11/ ሳይሆን ከልደቱ እስከ ሞቱ ድረስ የነበሩት መከራና ስቃይ ፈጽሞ የአባቱን ፈቃድ አከናውኖ በተአምራዊ ሁኔታ ከመሬት በብዙ ጠላቶቹ ፊት በክብር ከፍ ከፍ እንዳለ የሚያስረዳ ነው፤፤
   « ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው» /ሐዋ 1:9/
   « በስጋ የተገለጠ፣ በመንፈስ የጸደቀ፣ ለመላዕክት የታየ፣ በአህዛብ የተሰበከ፣በዓለም የታመነ፣ በክብር ያረገ፤፤» /1ጢሞ 3፤16/
   « ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው» /ዮሐ 3፤13/

### ለክርስቲያኖች የማረጉ ጥቅም

   « ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርሷ ወደ ሰማይ ገባ»/ዕብ 9፤24/
2. "በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ":-
   እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ጠላቶቹም የእግሩ መርገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል» /ዕብ 10፤12-13/
   « ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ» /ሐዋ 7፤5456/::

« የእምነታችንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግስት እንሩጥ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሶ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና::» /ዕብ 12:2/« የሞተው ይልቁን ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ::/ሮሜ 8:34/»

«ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል ::»/ዕብ 7:25/

3.«ዳግመኛ ለሕያዋንና ለሙታንም ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ያመጣል»

« የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው» /ሐዋ 1:11/

« ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሕያውም ሆኖአልና» /ሮሜ 14፤9/

« የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላዕክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል ::በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል ... እነዚህም ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ :: /ማቴ 25:31-46/::

« ለዚያች ቀን ወይም ለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን (በሥጋ) ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም ጊዜው መቼ እንዲሆን አይታወቅምና ተጠንቀቁ::ትጉና ጸልዩ::»/ማር 13፤32-33/

« እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል የምድርም ወገኖችም ሁሉ ስለእርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ» :: /ራዕ 1፤7/

« ለአንዳንዶችም የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም ::ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለእናንተ ይታገሳል:: የጌታ ቀን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል» /1ጴጥ 3፤9-10/

## ለክርስቲያኖች ዳግመኛ የመምጣቱ ጥቅም

«እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም ደግሞ መድሃኒትን እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርቶስን እንጠባበቃለን» /ፊሊ 3፤20/

« ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም ከእንግዲህም አይጠሙም ጸሐይም ትኩሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸዉም:: በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና :: ወደ ሕይወትም ውሃ ምንጭ ይመራቸዋልና ::እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከአይናቸው ያብሳል ::»/ራእ 7:16-17/

«ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንንም ጻዲቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል ደግሞም መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም» ::
/2ጢሞ 4:8/

« ጥበበኞችም እንደ ሰማይ ጸዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደከዋክብት ለዘላላም ይደምቃሉ »/ዳን 12:3/

«በልጁ የማያምን የዘላለም ሕይወት አለው» /ዩሐ 3:36/

« ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ::»/ማቴ 25 :46 /

« አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና» /ራዕ 22፤20/

4. ለመንግስቱ ፍጻሜ የለውም

« እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅ ይባላል ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ያነግሰዋል ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም » /ሉቃ 1:32-33/

« ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግስትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው መንግስቱ የማይጠፋ ነው» ። /ዳን 7:14/

« ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግስቱም ላይ አለቅነቱ ይበዛል ለሠላሙም ፍጻሜ የለውም » /ኢሳ 9:6-7/

በዚህ አስተምህሮ ላይ የጥንት አባቶች ያላቸው እምነታዊ አቋም

- "መከራ መስቀልን ተቀበለ በመለኮት ሕያው ሲሆን ራቁቱን ሰቅለው ዘበቱበት ህይወት እንደምን ሞተ ይባላል? ሰው መሆኑ ያስረዳ ዘንድ ዳግመኛም ያስነሳው ዘንድ በሥጋው ሞተ እንጂ»[62]

- "በሐሰት ያይደል በእውነት የስጋ ህመምን እንደ ታመመ በዚህ እናምናለን በገረፋት ጊዜ አልተሰማውም እና በሰቀሉትም ጊዜ አልደከመውምና በችንካርም በቸነከሩት ጊዜ ሕመም አላገኘውምና ብለው ሳለእርሱ የሚናገሩት ግን መናፍቃን እንደመሆናቸው እኛ እናወግዛቸዋለን"[63]

- "ሁለተኛውም ከነፍስ ጋር በሲኦል ነበር በሲኦልም ለጻድቃን

62. ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ ምዕ 72፣23

63. ሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ ምዕ 52፣10

የምስራች አበሰረ በሁለተኛውም ከሥጋ ጋር በመቃብር ነበር»[64]

- «በመነሳቱም የሙታን ትንሳኤ ጀማሪ እንደሆነ በእግዚአብሔር ቃል የማያምን ሰው ቢኖር ውጉዝ ይሁን»[65]
- «ወደ ሰማይ አረገ በአባቱ ዕሪና ተቀመጠ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ባረገበት በክበበ ትስብዕቱ ይመጣል»::[66]

እንግዲህ ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ላይነው ::ማንም በክርስቶስ ያላመነ ቢኖር የዘላለም ሞትና ቁጣ እንደሚጠብቀው ታስተምራለች መጽሐፍት እንዲህ እንደሚል «የሰውን ምስክር ከምንቀበል የእግዚአብሔር ምስክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል :: ስለልጁ የመሰከረው የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና ::በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሃሰተኛ አድርጎታል እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ህይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው ልጁ ያለው ህይወት አለው:: የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ህይወት የለውም::» /1ዮሐ 5:9-12፣ ዮሐ 3:36/ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የነበረው ተልዕኮ እንደገለጽነው ፈጽሞ ሄዳል ዳግመኛም በክብር ይመጣል !!መሆኑን ማንም ሰው ይህን የማዳን እውነታ ሲቀበለው ደግሞም ሲመሠክር ይገባል /ሮሜ 10:9-10/ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ስታምነው እንደነበር በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ /በልጁ ልጆች/ መባላችንን አጥብቀን እንያዝ ::እነሆ ጌታ ይመጣል ::

---

64. ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ ምዕ 71፤16
65. ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ ምዕ 73፤53
66.ሃይማኖተ አበው ዘሰለስቱ ምዕ 19፤25

## አንቀጽ 8

## "ጌታ ማኅያዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ ዘመንፈስ ቅዱስም እናምናለን:: እንስገድለት እናመስግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት የተናገረ »

በዚህ አንቀጽ መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት ያለውን እምነታዊ አቋም የሚገልጽ ነው ። የመንፈስ ቅዱስን አጠቃላይ ማንነት በምስጢረ ሥላሴ ርዕስ ስር ማስቀመጣችን የሚታወስ ነው::ይሁን እንጂ በሃይማኖት መግለጫው መንፈስ ቅዱስ ከአብ መስረጹን ፣ አምላክ መሆኑንና የጸጋውን አሰጣጥና አገልግሎቱን እንዴት እንደሚፈጽም ከተገለጸው በተጨማሪ በአጭሩ እናስቀምጣለን::

1. "ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ... ከአብና ከወልድ ጋር »

"ጌታ ማኅየዊ »የሚለው ቃል ለመለኮታዊነቱ /ለአምላክ/ ብቻ የሚሰጥ ስያሜ ነው "ጌታ" "ማኅየዊ" የሚሉት ሁለት ጥምር ቃሎች ለመንፈስ ቅዱስ ጌትነትና አምላክነት የተሰጠ እንዲያውም አንቀጹ እንሰግድለትና እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በማለት በእኩልነት ያስቀምጠዋል ይህ ምንኛ ድንቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባል ነው:: ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ "ጌታ" ተብሎ ተ ጽፎአልና:: /2ቆሮ 3፣17-18/ ኢዮብ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነትና ሕይወት ሰጭነት ሲመሰክር "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፣ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስና ሕይወትን ሰጠኝ" /ኢዮብ 33፣4/ አለ:: ዳዊትም "መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉ የምድርንም ፊት ታድሳለህ" ብሏል /መዝ (104):30/ ደግሞም በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ" አለ /መዝ (33):6/:: መንፈስ ቅዱስ እንደ አምላክነቱ በሁሉ ስፍራ መገኘቱን በሚገርም ቃል ዳዊት ሲናገር :-

«ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ አለ /መዝ (139):7/:: እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን እግዚአብሔር ብሎ ሲጠራው:-

«መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሺያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ... እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም» አለ /ሐዋ 5:3-4/ :: ደግሞም ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን <u>እግዚአብሔር ብሎ ሲጠራ</u>ው:-

« የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል» ይላል:: /1ቆሮ 3:16-17/ ደግሞም ከአብና ከወልድ ጋር <u>በአንድነት</u> ሲጠቅሰውም

« የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው /መንፈስ ቅዱስን/ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው (ወልድን) አሰራርም ልዩ ልዩ ነው ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው» /አብን/ በማለት ይናገራል:: /1ኛ ቆሮ 12:4-6/ እንዲሁም «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ (የወልድ) የእግዚአብሔር ፍቅር (የአብ) የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት (መንፈስ ቅዱስን) ከሁላችሁ ጋር ይሁን::» አሜን በማለት ይገልጻል /2ቆሮ 13:14/::

ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን ሲገልጥ ወይም «ሲተርክ» የመጣው /ዮሐ 1:18/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ የስላሴ አንዱ አካል እንደ ሆነ ለማሳየት በአንድነት «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም » በማለት ጠቅሶታል /ማቴ 28፤18/ እንግዲህ በአጭሩ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ብቻ ያለውን ባሕሪያት የያዘ አምላክ መሆኑን ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተቀምጣል::

ሀ. ዘላለማዊነቱ:- /ዕብ 9፣14/

ለ. በሁሉ ቦታ መገኘቱ:- /መዝ (139)፣7/

ሐ. ሁሉን ማወቁ፤- /1ቆሮ 2፣10-11/

መ. በፍጥረት ስራ ውስጥ መፍጠሩ:- / ዘፍ 1:2፣ መዝ(104):30/

ሠ. ክርስቶስ ሰው መሆን መሳተፉ:- /ማቴ 1:18፣ ሉቃ 1:35/

ረ. የክርስቶስ ትንሳኤን ማከናወኑ:- /ሮሜ 1:4፣ ሮሜ 8:11/

ሰ. ሠውን ለደህንነት ማዘጋጀቱ:- /ሮሜ 8:1-27/

አምላክነቱን ሲያስረዳን ደግሞም ዝርው ኃይል ሳይሆን ኃይል ያለው አካል ስለመሆኑ

ሀ. ቃሉን ጠቅሶ መናገሩ /ዮሐ 16:13፣ ሐዋ 1:16፣ 8:29፣ 10:9፣ 11:12፣ 13:2፣ 16:6፣ 20:23፣ 21:11፣ 28:25-27፣ 1ጢሞ 1:11፣ ራዕ 2:7፣11:-29፣ 3:6፣ 13:22/

ለ. አካል በመኖሩ ይዋሻል/ይታለላል/ ::ነገር ግን አምላክ ስለሆነ ያውቃል /ሐዋ 5፣3/

ሐ. ፍርድን (ውሳኔን) ይሠጣል:: /ሐዋ 15:28/

መ. ለሰዎች ይማልዳል /ሐዋ 8፣26/ ተጠቅሷል::

በአጠቃላይ መንፈስ ቅዱስ የስላሴ አንዱ አካል የሆነ እግዚአብሔር "ጌታ ማህየዊ" ነው::

<u>በዚህ አስተምህሮ ላይ የጥንት አባቶች ያላቸው እምነታዊ አቋም</u>

ስለመንፈስ ቅዱስ እውነት አበው የእምነት አቋማቸውን ሲገልጹ "እንዲሁ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ከወልድ ጋር በቅድምና የነበረ ቀዳማዊ ነው:: በስራውም ሁሉ ከአብ ከወልድ ጋር አንድ ነው ጉባኤ በቆመለት ቤተክርስቲያን ተቀበለችው ሐዋርያት ያስተማሩት እውነተኛ ትምህርት ይህ ነው::[67]

---

67. ሃይማኖተ አበው ዘሠለስቱ ምዕት ም 19፣9-10

2 . "ከአብ በሰረፀ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን"

መሥረጽ ማለት መውጣት ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሰረጸ ሲባል የተገኘ የወጣ ማለት ነው ይህም በምስጢረ ስላሴ ላይ ምሳሌ የሰጠነውን ለማስታወስ ያህል ከፀሐይ አካል ብርሃንና ሙቀት እንደሚገኙ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ አካል አብን አክለው መገኘታቸውን መውጣታቸውን መረዳት ይቻላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል" በማለት ከአብ እንደ ወጣ ገልጾአል /ዮሐ 15:26/::

3. "በነብያት የተናገረ መንፈስ ቅዱስ"

ነብያት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የጌታን ፈቃድ ጽፈው አስተ ላልፈውልናል::የህግና የነብያት ሁሉ ፍጻሜ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ዛሬ አዲስ ነብይና መጽሐፍ አያስፈልገንም/ሮሜ 10:4.3:21/:: መንፈስ ቅዱስም እስከዛሬ ድረስ ያኑት መጽሐፍ ቅዱስን በማብራት በትጋት በሰዎች ውስጥ ቤተክርስቲያንን በማገልገልና በመገንባት ላይ ይገኛል::መንፈስ ቅዱስ ያገለገለበትና እያገለገለ ያለብትም መንገድ:-

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን በማጻፍና ቃሉን በመጠበቅ "በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳንሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ"/2ጴጥሮ1:20-21/

ለ. በመከራ ውስጥ በማጽናትና በማጽናናት

"አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ የምትናገሩት በዚች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጅ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና" /ማቴ 10:19:20/

"እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንድኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል" /ዮሐ 14: 16/ ::

ሐ. ወደ እውነት ሁሉ በመምራት

« ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» /ዮሐ 16:13/

« አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል» /ዮሐ 14:26/

በአጭሩ መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያትን ነብያትን ቅዱሳንን ሁሉ ስለመራቸው ቤተክርስቲያን በሐዋርያትና በነብያት ትምህርት ላይ ተመስርታለች የትምህርታቸውም የማዕዘን ራስ ክርስቶስ ነበር:: /ኤፌ 2:20-21/ ስለዚህ አበው በነብያት እናምናለን በነብያት የተናገረ እግዚአብሔር ነውና ብለዋል::

## 4. መንፈስ ቅዱስ የመቀደሳችን ምንጭ

« ... ወይስ አመጸኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣኦትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀራጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሰሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም:: ከእናንተም አንዳንዶች እንደ እነዚህ ነበራችሁ:: ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል ተቀድሳችኋል ጸድቃችኋል::» /1ኛቆሮ 6፤9-11/

እንግዲህ ይህ ጥቅስ ደህንነት ባገኘንበት ጊዜ ከኃጢአት መታጠብን መቀደስን መጽደቃችንን የሚገልፅ ነው::ቃሉ «ነበራችሁ» በማለት ይናገርና « አሁን ግን በጌታ ኢየሱስ » በማለት የመለወጣችን ምንጭ ኢየሱስ ሆኖ በመንፈስ ደግሞ ህይወታችን እንደ ተለወጠ ያስ ረግጥልናል:: ጌታን ክርስቶስን በማወቁ ያልተለወጠና በቀደመ ህይወቱ እንዳለ ያለ ከሆነ ግን ታጥቧል ተቀድሷል ጸድቋል ወይም ድኗል ማለት አስቸጋሪ ይሆናል:: ምክንያቱም ሐዋርያው ያዕቆብ

እንዳለ «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁም ደግሞ ከስራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» :: /ያዕ 2:26/ በመሰረቱ የሞተ ነፍስ ስራ አይጠበቅበትም::ስለዚህ በመቀደሳችን ሳይሆን የዳነው በመዳናችን ነው የተቀደስነው:: የጸደቅነው እንድንቀደስ ነው::የተቀደስነው ሰዎችንና እግዚአብሔርን የክርስቶስን በሚመስል ፍቅር እንድናገለግል ነው:: ቅድስና ተለዋጭ ሳይሆን ዋና ትእዛዝ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱሳን እንድንሆን ያስተምረናል / 1ጴጥ 1:15-16፣ ዘሌ 19:2 / ደግሞም « በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል » የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶናል /2ኛጴጥ 3:11/::«ለእርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናል»/1ኛተሰ 4:4/«ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ» /ዕብ 12:14/ « ሰውነታችሁም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ህያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ» /ሮሜ 12:1/ ይላል ::እንግዲህ ቅድስና የእግዚአብሔር ተአምራዊ ስራ እንጂ የሰው ትግል ውጤት አይደለምና ራስህን ለእግዚአብሔር አቅርብ::

ከላይ ያየናቸው ክፍሎች በሙሉ የሰው ድርሻ ከመዳን በኀላ ለመቀደስ መፈለግ ራስን ማቅረብ እንዳለበት ያስተምራሉ የመቀደስ ተግባር የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነውና:: ምክንያቱም « የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ መንፈሳችሁን ነፍሳችሁን ስጋችሁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ፈጽመው ይጠበቁ የሚጠራችሁ የታመነ ነው እርሱም ደግሞ ያደርገዋል» ተብሎ ተገልጻል ::/1ኛተሰ 5:23-24/

## አንቀጽ 9

## «ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰብዋት አንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያንም እናምናለን »

መጽሐፍ ቅዱስ ስለቤተክርስቲያን የሚከተለውን ይናገራል «አሁኑ በመከራዩ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል :: ስለአካሉም ማለት

ስለቤተክርስቲያን በሥጋየ በክርስቶስ መከራ የጎደለውን ፈጽማለሁ ። ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ » /ቆላ 1፤24-25/።በተጨማሪም አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን /ሐዋ 13:1/ እና የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን /1ኛቆሮ 1:2/ እነዚህና በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቤተክርስቲያን የሕዝቡ ስብስብ እንደሆነች እንጂ ሕንጻው ወይም የክሴ በሚል የሚጠራ ቅጥርን አያመለክትም ።ቃሉን በራሱ ብንፈታው አንድ ሰው በክርስቶስ ሲያምን ክርስቲያን ሲባል፡ ብዙ ሰዎች ክርስቶስን ሲያምኑ ደግሞ ቤተክርስቲያን ወይም ቤተክርስቶሳውያን ይባላሉ። ይህም ቤተ እስራኤል ቤተ አሮን እንደሚባለው የስብስቡን ምክንያት ወይም ዝርያን የሚያመለክት ነው። ክርስቲኖችን በተናጠል መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ብልቶች ሲላቸው በማህበር ሲጠሩ ደግሞ የክርስቶስ አካል ወይም ቤተክርስቲያን ይባላሉ /1ኛቆሮ 12:27-31፣ ኤፌ 5፤23-33/ «ቤተክርስቲያን» የሚለው የጥንቱን የጽርዕ ቋንቋ ብንመለከት «ኤክሌሺያ» የሚል ሲሆን ይህም ለአንድ ዓላማና ስራ የተመረጡና የተጠሩትን ማኅበር ወይም ጉባኤን ያመለክታል[62] እንጂ ህንጻን በፍጹም አያመለክትም።ደግሞም ቤተክርስቲያን የሚለው ስም በስጋ ያሉትን ወይም በአንድ አካባቢ የሚገናኙትን ብቻ ሳይሆን በሩቅና በሌላ ጋጥ ውስጥም እንዲሁም በአጸደ ነፍስ ያሉትንም ጭምር ያካትታል ። /ዩሐ 10:16 ገላ 4:26፣ ሉቃ 23:43፣ 1ጴጥ 3:19፣ ዕብ 12:22/

በዚች የክርስቶስ አካል በሆነው ስብስብ ወይም (ቤተክርስቲያን) ውስጥ የዘር የብሔር የእምነት ክፍል ወይም የስራ ደረጃ የፖለቲካ ... ወዘተ ገደብ የለም «... አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባሪያ ወይም ጨዋ የለም ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁም በክርስቶስ አንድ ሰው ናችሁና።» ይላል በዚች ስብስብ ውስጥ እውነተኛ ፍቅር፣ ትህትና፣ መደጋገፍ፣ ሰላምና ደስታ ይገኙባታል። ቤተክርስቲያን የሁከት ጦር ሜዳ አይደለችም። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ

የእያንዳንዱን ሕይወት ስለሚለውጥና ተግቶ ስለሚሰራ ፍቅር ደስታ ትግስት ቸርነት በጎነት እምነት የዋሃት ራስን መግዛት እንደዚህ ያሉትን በሙሉ ከየትም ስፍራ ሳይገኙ በቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ ይገኛሉ:: ይህ እውነት የታመነ ነው:: /ገላ 5:22/

1 .የቤተክርስቲያን አካሎች /አባሎች/ እነማ ናቸው? ቢባል ክርስቶስ «የራሴን በጎች አውቃለሁ:: የራሴም በጎች ያውቁኛል...ድምፄንም ይሰማሉ» በማለት እንደ ተናገረው/ዮሐ 10:14 -16/ ክርስቶስን የሚያውቁ ድምጽንም የሚሰሙ ብቻ እንጂ እርሱን የሚቃወሙ፡ የቤተክርስቲያንን ጉባኤ መከፋፈልና ሁካታን የሚፈጥሩ በጭራሽ አይደሉም:: ክርስቶስ የእርሱ ስለሆኑት ሕዝብ ባቀረበው ጸሎቱ «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ አንተን የላክውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ህይወት ናት» ብሏል /ዮሐ 17:3/ከዚህ እንደምንረዳው የእሱ የሆኑት ከክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት ያላቸው/ከአካሉ ጋር የተሳሰሩ ብልቶች/ ብቻ ነው::የሃይማኖት መሪ ለነበረው ለኒቆዲሞስ «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተ ወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም» ብሎ ስለ ግል ሕይወቱ ከእግዚአብሔር መወለዱና መገናኘቱን ነግሮታል:: /ዮሐ 3:3 /

ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ካለን /1ኛዮሐ 1:1-6/ ሌሎች የክርስቶስ አካሎች ጋር ጤናማ ህብረት ያላቸው ሰዎች እንሆናለን:: አንዱ ብልት ቢታመም ግን ብልቶች ሁሉ ይታመማሉ ተብሎ እንደ ተጻፈ ጉባዔው ችግር ውስጥ ይወድቃል:: / 1ቆሮ 12:26 / ስለዚህ በቤተክርስቲያን የተለየ መተሳሰር አለ፡፤በመሆኑም ጌታ የግል እንጂ የጃማ ስላልሆነ በማቴ 7:21 «በሰማይ ያለው የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» ሲል ክርስቶስ አስጠንቅቋል:: ይህም በመቀላቀልና የቤተክርስቲያንን ስርዓት በመፈጸም ብቻ የቤተ ክርስቲያን አልያም የክርስቶስ አካል መሆን አይችልም « ከቶ

አላውቃችሁም »ብሎ እንደሚያሰናብት ግልጽ ነው /ማቴ 7:23/ አንዳንድ ሰዎች መጠመቅ የቤክርስቲያን ቅጥር መሳለም ወይም መመላለስ ከክርስቲያን ወላጆች መወለድ ወይም በክርስትና ስም በመጠራት ክርስቲያኖች ወይም የክርስቶስ አካል የሚያደርጋቸው ይመስላቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት በግላቸው በአሚነ ኢየሱስ ክርስቶስ ተዋጅተው የተጠመቁ እንደሆኑ ይናገራ /ዮሐ 1:12፣ 2ጴጥ 1:10-11፣ 2ጴጥ 3:18፣ ራዕ 3፤20/ የኢትዮጵያም ቤተክርስቲያን ሕጻናትን ስታጠምቅ ለክርስትና አባት / እናት/ ሆኖ ለቀረበው የቅርብ ተከታታይ አሳዳጊ ሆኖ ክርስትናን እንዲያስተምረው ከልጅነቱ ጀምሮ በክርስቶስ በማመን ከህብረቱ / ከክርስቶስ አካል/ ጋር ግንኙነት እንዲጠነክ በመሻት በአደባባይ ልጁን ተቀብሎ ቃለ መሃላውን በማስፈጸም ያላትን እምነት ትገልጻለች እንጂ የአፍአ አባል እንዲሆንላት በጭራሽ አይደለም::

2. <u>የእግዚአብሔር መቅደስ</u> የሚለውንም ስንመለከት ክርስቲኖች በትላልቅ ወይንም በትናንሽ ሕንጻዎች አንዳንድ ጊዜም በግለሰቦች መኖሪያ ቤቶች አንዳንድ ጊዜም በዛፍ ጥላ ስር በመሰብሰባቸው ስፍራው ከታሪካዊነቱና ከመሰብሰቢያ ምክንያት ከመሆኑ ውጭ የጎላ ፋይዳ የለውም:: ሕዝቡ ግን ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊዎች ናቸው::በዚህ አይነት በስሙ የሚሰበሰቡትን ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል «በጌታ ቅዱስ ቤተመቅደስ» ይላቸዋል / ኤፌ 2:21 / ሐዋርያው ጴጥሮስም «እናንተ ደግሞ ህያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሰሩ» ይላል /1ጴጥ 2:5/:: ሐዋርያው ጳውሎስም «የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደሚኖርባችሁ አታውቁምን? ...የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ» ብሏል /1ኛቆሮ 3፤16/ ይህች የክርስቶስ አካል /ቤተክርስቲያን/ በማህበረሰቡ መካከል ስትኖር መጸተኛ ነች: ትሳደዳለች: ስይጣንም ይፈታተናታል:: ነገር ግን የገሃነም ደጆች እንኳን አይችሏትም /ማቴ 16:18/ በምድር ላይም መንገሷ አይቀሬ

/ነው /ራዕ 5:9-5/:: ምክንያቱም የምድር ጨው ፡ የምድር ብርሃን ማቴ 5:13-14/ ነችና የሰው ሁለንተና እየቀደሰችና እየለወጠች ትሄዳለች::

የሃይማኖት መግለጫው በቤተክርስቲያን እናምናለን ሲል በኅብረት ጸሎት፣ በህብረት አስተዳደር፣ በህብረት እንጀራ መቁረስ (መቁረብ): በህብረት መረዳዳት: በህብረት መንፈሳዊ ስጦታን መቀባበል፣ በህብረት የእግዚአብሔርን እቅድና ዓላማን በምድር ማስፋፋት፣ በህብረት የክርስቶስን መምጣት መጠባበቅን እናምናለን ማለት ሲሆን ልዩነት ስፍራ የለውም ::በመንፈስ ቅዱስ እርስ በርስ ተቆላልፋለች::

3. <u>ቤተክርስቲያን አንዲት ነች</u>:- ምክንያቱም ክርስቶስ በደሙ ዋጅቶ የመሠረታት አንዲት ነች::የእርሷም የማዕዘን ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ነው በቦታ፣ በጊዜ፣ በብሔር ፣ በቋንቋ፣ በባህል ... ወዘተ ክርስቲያኖች ቢራራቁም ቢደራጁም ያው በአንዱ ግንድ ያሉ ቅርንጫፎች ናቸው /ዮሐ 15፤1-11/ ሐዋርያውም ጳውሎስ «በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ:: አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሰራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ» ብሏል :: /ኤፌ. 4፤4-6/:: «እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ስጋ ነን ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለን» በማለት አንዲት ቤተ ክርስቲያን እንዳለ አስረድቷል::

4.<u>ይህችም ቅድስት እንደሆነች</u> :-ሲናገር «በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጠ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር

ሳይሆንባት ቅድስትና አለነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ" ይላል /ኤፌ 5፤25-27/

5. ሐዋርያዊት እንደ ሆነች

ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው በክርስቶስ ደም ቀው:: እርሱም ከእርሱ ጋር የነበሩትን የከሰሱት ያዩትን እንደእርሱ የቀረጻቸውን ሐዋርያት ቤተክርስቲያኑን እንዲተክሉ ለሐዋርያትና ለነብያት ጸጋና እውነት ሰጥቶ እስከምድር ዳር ድረስ ላካቸው ::እነርሱም ወጥተው ከብዙ መከራ ጋር ሰበኩ::በእነርሱም አስተምህሮ ላይ ቤተ ክርስቲያን ተመስርታለች /ኤፌ 2፤20-22/ ከሃዋርያት አስተምህሮ ውጭ የተቋቋመ ቢኖር እንኳ የክርስትናን ስም ለይስሙላ ይያዝ እንጂ ሐዋርያዊ ያልሆነ መንፈሳዊ ቤትና የእግዚአብሔር ማደሪያ ያልሆነ ለሌላ ዓላማ የተቋቋመ ተቋም ማለት ይቻል ይሆናል::

በአጭሩ ቤተክርስቲያን "ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰብዋት በአንዲት ቤተክርስቲያን እንደ ምታምን አቋሟን አስቀምጣለች"

## አንቀጽ 10

## " ኃጢአትን ለማስተሰረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን "

ስለጥምቀት በሚመለከት ሚስጥረ ጥምቀት በሚል ርዕስ ስር አይተነዋል:: ይህም ጥምቀት የጌታችን ትዕዛዝ ስለመሆኑ /ማቴ 28፤19/ አንዲት ስለመሆኗ /ኤፌ 4፤5/ የቤተክርስቲያን መሆናችንን ለአለም የምንመሠክርበት መሆኑን /ሮሜ 6፤3-5/ ስለገለጽን በዚሁ እናልፈዋለን::

## አንቀጽ 11

## "የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን"

በሃይማኖት መግለጫው እንደተመለከትነው "እናምናለን" "እናምናለን" በሚል እንደተቀመጠ አይተናል:: አሁኑ ደግሞ "ተስፋ እናገርጋለን " በማለት እምነትን ይስረዳል:: "ነገር ግን ተስፋ የሚደ ረግበት ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም:: የሚያየውንማ ማን ተስፋ

ያደርገዋል? የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግስት እንጠባበቃለን፤፤» በማለት ተስፋ ወደፊት ስለሚሆን ነገር ተረድቶ በትዕግስት መጠባበቅን ያመለክታል /ሮሜ 8፤24/ ሰው ከአፈር ተ ፈጥሮ እንደነበርና እንደሚመለስ ተጽፏል /ዘፍ 2:7፣ 3፤19/ ነገር ግን ፍጻሜው አይደለም:: ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባና "ሙታን የእግዚአብሔርን ድምጽ የሚሰሙበትና የሚቀሰቀሱበት ቀን ይመጣል» /ዮሐ 5፤24-29/:: ክርስቶስ ስለ ሙታን ትንሳኤ በርካታ ጊዜ አስተምሮአል «ትንሳኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዶቃውያን ወደ እርሱ ቀርቡ ... ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤- መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ ... የህያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም» አላቸው /ማቴ 22:23-32/ እንዲሁም «ማርታ በመጨረሻው ቀን በትንሳኤ እንዲነሳ አውቃለሁ አለችው::ኢየሱስም ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም» ብሏል /ዮሐ 11:24-26/ ደግሞም ክርስቶስ በትምህርት ብቻ ሳይሆን ከሙታን በመነሳት ምልክት (በኩራት) ሆኗል:: /1ኛቆሮ 15:20/ ሐዋርያትም ስለትንሳኤ ሙታን በአጽንኦት አስተምረዋል:: «ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሳ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ፡- ትንሳኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? እንሳኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሳማ፡ ክርስቶስም ካልተነሳ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው:: እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት ደግሞም፤- ክርስቶስን አስነስቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለመሰከርን ሐሰተ ኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል:: ሙታን ግን የማይነሱ ከሆነ እርሱን አላስነሳውም፡ ሙታን የማይነሱ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሳማ:: ክርስቶስም ካልተነሳ እምነታችሁ ከንቱ ናት:: እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋላ በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን:: አሁኑ ግን ክርስቶስ

ላንቀሳፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷል ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሳኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና ሁሉ በአዳም እንደ ሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና:: /1ቆሮ 15፤12-21/ ከዚህም በላይ በመጨመር "የማይበሰብሱ ሆነው ይነሳሉ እኛም እንለወጣለን::ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ለብሶ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና ... በዚያ ጊዜ ሞት ድል በመነሳቱ ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል:: /1ኛቆሮ 15፤52-54/ ይላል:: ዮሐንስ በራዕይ "ባህርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ ሞትና ሲኦል በእነሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ" በማለት ያየውን ጽፏል /ራዕ 20፤13/ ከዚያም በፍርድ ዙፋን ፊት ፍጥረት ሁሉ ይሰበሰባል:: ለእያንዳንዱም የክብር አልያም የፍርድ ጽዋውን ይቀበላል:: "መጽሐፍትም ተከፈቱ ሌላ መጽሐፍትም ተ ከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው ሙታንም በመጽሐፍት ተ ጽፎ እንደ ነበር እንደ ስራቸው መጠን ተከፈሉ ... እያንዳንዱም እንደ ስራው መጠን ተከፈለ ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ:: ይህም የእሳት ባህር ሁለተኛው ሞት ነው በሕይወትም መጽሐፍ ተ ጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣለ::" /ራዕ 20፤12-15/ " እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ" /ማቴ25፤31-46/ " መልካሙን ገድል ተ ጋድያለሁ ...ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል" /2ጢሞ 4፤7-8/
" መልካም ያደረጉ ለህይወት ትንሳኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ::" /ዮሐ 5፤29/ ከዚህ ሁሉ በኋላ ዘላለማዊ ህይወት ይጀምራል:: የፍጥረት ዓላማ ይዘጋል::

**የአበው <u>እምነት አቋም በሚከተለው</u> መልኩ <u>ተቀምጦአል</u>**

" ዳግመኛም የሞቱ የጻድቃንንና የኃጥአንን መነሳት እናምናለን ሁሉም አካል ሳይጎድላቸው ይነሳሉ ክፉንም ቢሆን በጎውንም ቢሆን

ከፈጣሪያቸው ይቀበላሉ:: /መዝ (61):12፣ ማቴ 25:31-41፣ ሮሜ 6:2፣ ሮሜ 14:9፣ 2ኛቆሮ 5፤10-10/»[68]

## አንቀጽ 12

### «የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ አሜን»

ይህ የክርስቲያኖች ሁሉ የናፍቆታቸውና የተስፋቸው ፍጻሜ ነው:: እዚህ ለመድረስ ብዙዎች በእሳት ውስጥ በሰይፍ ስለት፣ ከማህበራዊ ሕይወት መገለል ... ወዘተ ሁሉ አልፈዋል/ዕብ11:32/:: ጌታ እንደተናገረ ክርስቲያን በዓለም ሲኖር በመከራ ውስጥ ያልፋል / ዮሐ 16፤37/ ሐዋርያትም ሁሉ በዚህ አስቸጋሪ (የጠበበ መንገድ) / ማቴ 7:13/ ውስጥ አልፈዋል:: በክርስቶስ ላሉ ሁሉ የሚመጣውን ሕይወት ይሰጣቸዋል:: መሄጃው መንገዱ መድረሻው ሀገሩ በክርስቶስ በኩል እንጂ በሌላ በኩል አይገኝም[69]«አዲስ ሰማይ አዲስ ምድርንም አየሁ ... እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ሃዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀደመው ስርዓት አልፎአልና»/ራዕ 21:1-4/ ::

« ለበጉም በሆነው በህይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ጸያፍ ነገር ሁሉ እርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርሷ ከቶ አይገባም» / ራዕ 21:27/

« በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ህይወት እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና:: ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ጸዳል፣ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ» /ዳን 12፤2-3/

---

68. ሃይማኖተ አበው ዘአትናቴዎስ 28፤21

69.ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት በሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ ገጽ 216

« በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግስት እንደ ጸሃይ ያበራሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ» /ማቴ 13:42-43/ ፡፡

ነገር ግን ዋናውና ትልቁ ነገር ዛሬ በህይወት ዘመናችን የሚሰበከው ወንጌል /የምስራች/ ቀላል አይደለም። ከዘላለም ሞትና ጥፋት ስለሚያድን የምስራች ተብሏል ወንጌልም ከዳዊት ዘር ስለተወለደው እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሳት ስለ ተነሳው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ብቻ ነው። ይህም እግዚአብሔር ዓለምን እንዲያድን አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታል /ዮሐ 3፤16-17/ በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። /ዮሐ 3፤18/ በተደጋጋሚም በዮሐንስ ወንጌል ብቻ እንኳ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል።

« በልጁ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው፣ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ህይወትን አያይም » /ዮሐ 3፤36/

« እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው ከሞትም ወደ ይወትም ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» /ማቴ 5፤24/

« በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ» /ዮሐ 7፤38/

« እኔ እንደሆንኩ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ሞታላችሁ» /

/ ዮሐ 8፤24 /

« የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል» /ዮሐ 11፤25/

« ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል» /ዮሐ 20፤31/፡፡

በመሆኑም በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ልታምን ይገባሃል:: አለዚያ የእግዚአብሔር ቁጣ በአንተ ላይ አለ እንጂ ህይወትን አታይም:: ደግሞም አሁን ተፈርዶብሃል:: ስለዚህ እምነት፣ እምነት፣ እምነት በእርሱ አዳኝነት ላይ!

እንግዲህ የዘላለም ህይወት ወራሾች የእግዚአብሔር ልጆች /ክርስቲያኖች/ ብቻ ናቸው /ሮሜ 8፤15-17/ መንግስተ ሰማያት ያውርስልን ተብለው እንዲመረቁና እንዲመኙላቸው አይገባም:: ሁሌም ለእነርሱ የተዘጋጀች ናትና ይልቁንም መንግስትህ ትምጣ:: እያሉ በመናፈቅ ይጸልያሉ:: ደግሞም ጌታችን ሆይ ና /ማራናታ/ ይሉታል:: /1ቆሮ 16፤22፣ ማቴ 6፤10፣ ፊሊ 3፤20፣ ራዕ 22፤20/

## 8 .የአስተምህሮው መጠቅለያ

እንግዲህ የጥንቱን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እምነትና አቋም ሳይቀላቀልበትና ሳይበረዝ አበው ያጸኑትና ያስተላለፉትን እውነታና እምነት ይኸው ብቻ ነው በመግለጫው እንዳስቀመጡት አንድም ከቃሉ የወጣ አስተምህሮ የላቸውም ክርስቶስ ለሐዋርያት :ሐዋርያትም ለደቀመዛሙርቶቻቸው : እነርሱም ለእምነት አባቶቻችን ያጸኑልንንና ያስተላለፉልን አጥብቀን ልንይዝ ይገባል ሃይማኖት መግለጫውም ሆነ የሐዋርያት አመክንዮ በአጭሩ ሲቀመጥ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን:-

### 1. ሥላሴ በሆነው አንድ አምላክ ታምናለች

ይህም ለዘላለም ህያው ሆኖ የሚኖርና መጨረሻ የሌለው ሉአላዊ የሆነ አንድ አምላክ እርሱ ብቻውን አምላክ ፈጣሪና ገዢ በማንነቱ በባሕርያቱና በዓላማው ቅዱስ መሠረታዊ ማንነቱም አንድም ሦስትም የሆነ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ የተገለጠውን አንድ አምላክ ታምናለች :: / ዘፍ 1፣ ዘሌ 19፤2፣ ዘዳ 6፤4-፣ ኢሳ 5፤16፣6፤1-7፣ 40፤18-31፣ ማቴ 3፤16-17፣ 19፤20፣ ዮሐ 14፤6-27፣

1ቆሮ 8:6፣ 2ቆሮ 13-14፣ ገላ 4፡4፣ 6፣ ኤፌ 2፡13-18 /

## 2. በኢየሱስ ክርስቶስ ታምናለች

የስላሴ አንዱ አካል የሆነው ወልደ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ከአብ ጋር የነበረ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስጋ ለባሽ ሰው ሆኖ ከድንግል ማርያም እንደተወለደ ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ የፍጹም መለኮትና የፍጹም ትስብእት በተአቅቦና በተዋህዶ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው እንደ ሆነ ለኃጢአታችን እንደሞተ ከሞት ተነስቶ ስጋውን እንደያዘ በሁለተኛው የፍጹም ሰውን ባሕርይ እንደ ያዘ ወደ ሰማይ እንዳረገ ከዚያም በአብ ቀኝ በመቀመጥ ሊቀ ካህን እንደ ሆነ ፡ ተመልሶም ለፍርድ እንደሚመጣ ታምናለች::

/ ማቴ 1:20-25፣ 16፡15-16፣ ሉቃ 1:26-35፣ ዮሐ 1:1-18፣ ሐዋ 2፡22-36፣ሮሜ 8፡13፣ ገላ 4፡4-5፣ ፊሊ 2፡5-11፣ ቆላ 1፡12-22፣ 1ጢሞ 6፡14-16፣ ዕብ 1፡1-5፣ ዕብ 7፡22-28፣ ዕብ 9፡24-28፣ 1ዮሐ 1፡1-3፣ 4፡2-3 /

## 3. በመንፈስ ቅዱስ ታምናለች

የሥላሴ አንዱ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜም ከአብና ከወልድ ጋር እንደኖረና እንደሚኖር በቤተክርስቲያን ውስጥ በትጋት እንደሚሰራ ዓለምን ስለ ኃጢአት እንደ ሚወቅስ ንስሃ ገብተው ለሚያምኑት አዲስ ሕይወትን እንደ ሚሰጣቸው ምዕመንን እንደ ሚቀድስና በክርስቶስ ወዳለው እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ታምናለች::

/ዮሐ 7፡39፣ 14፡15-18፣ 26፣ 16፡7-15፣ ሐዋ 2፡33፣ 15፡8-9፣ ሮሜ 8፡1-27፣ ገላ 3፡1-14፣ 4-6፣ ኤፌ 3፡14-21፣ 1ተሰ 4፡7-8፣ 2ተሰ 2፡13፣ 1ጴጥ 1፡2፣ 1ዮሐ 3፡24፣ 4፡13/

## 4. በቅዱሳት መጽሐፍት ታምናለች

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ - እግዚአብሔር እንደ ተጻፉ የቤተ ክርስቲያኗ መመሪያዋ የመጻሕፍት ሁሉ አውራ እንደሆነ ታምናለች። /ሉቃ 24፤44-47፣ ዮሐ 10፤35፣ 1ቆሮ 15፤3-4፣ 2ጢሞ 3፤15-17፣ 1ጴጥ 1:10-12፣ 2ጴጥ 1:20-21/

## 5. የውርስና የግል ኃጢአት እንዳለ ታምናለች

በአዳምና በሔዋን የመጣ አለመታዘዝ በሰው ሁሉ ዘንድ እርግማኑና ኃጢአቱ እንደ ተላለፈ ሞትንም እንዳመጣ እንዲሁም ከዚህ ባህሪ ከሚመነጭ የግል ኃጢአት ሁሉ ሰው ተጠያቂ እንደሆነ ታምናለች ይህም ማለት :-

ሀ. የውርስ ኃጢአት እንዳለበት:- /ዘፍ 3፤6-5፣ ኢዮብ 15፤14፣ መዝ 51፤5፣ ኤር 17፤9-10፣ ማር 7፤21-23፣ ሮሜ 1፤18-25፣ ሮሜ 5፤12-17፣ ሮሜ 7፤1-8፣ 1ቆሮ 3፤1-4፣ ገላ 5፤16-25፣ 1ዮሐ 1፤7-8 / እንዲሁም

ለ. የግል ኃጢአትም እንዳለበት ታምናለች /ማቴ 22፤36-40፣ ዮሐ 8፤34-36፣ 16፤8-9፣ ሮሜ 3፤23፣ 6፤15-23፣ 8፤18-24፣ 14፤23፣ 1ዮሐ 1፤9፣ 2፤4፣ 77፤10/

## 6. በስርየት ታምናለች

ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው ስቃይ ባፈሰሰው ደምና በመስቀል ላይ በሞቱ አማካኝነት ለሰው ልጆች ሁሉ ስርየትን እንዳስገኘ፣ ይህም ስርየት ብቻውን የደህንነት መሠረት ከመሆኑም በላይ ለአዳም ዘር በሙሉ እንደሚበቃ ታምናለች።

/ኢሳ 53፤5-6፣ 6፤11፣ ማር 10፤45፣ ሉቃ 24፤46-48፣ ዮሐ 1፤29፣ 3፤14-17፣ ሐዋ 4፤10-12፣ ሮሜ 3፤21-26፣ 4፤17-25፣ 5፤6-21፣ 1ቆሮ 6፤20፣ 2ቆሮ 5፤14-21፣ ገላ1፤3-4፣ ገላ3፤13-14፣ቆላ 1፤19-23፣

1ጢሞ 2፤3-6፣ ቲቶ 2፤11-14፣ ዕብ 2፤9፣ዕብ 9፤11-14፣ ዕብ 13፤12፣ 1ጴጥ 1:18-21፣ 2፤19-25፣ 1ዮሐ 2:1-2/

7. በነጻ ፈቃድ ታምናለች

አማኝ ወይም ምእመናን ሁሉ ደግም ልደትን በክርስቶስ ካገኙ በኋላ ከእግዚአብሔር ህብረት ተለይተው ከኃጢአታቸው በንስሃ እስካልተመለሱና ደህንነታቸውን ሊፈጽሙ እስካልቻሉ ድረስ ለቅጣት ሊዳረጉ እንደሚችሉ ታምናለች።

/ ሕዝ 18፤25-26 ፣ ዮሐ 1 12-13፣ 3፤6 ፣ ሐዋ 5፤31 ፣ ሮሜ 5፤6-8 ፣1ኛ 6፤15-16፣ 23፣ 10፤6-8 ፣ 11፤22 ፣ 1ቆሮ 2፤9-14 ፣ 10፤1-12፣ 2ኛቆሮ 5፤18-19፣ ገላ 5፤6፣ ኤፌ 2፤8-10፣ ፊሊ 2፤12-13፣ ቆላ 1፤21-23፣ 2ጢሞ 4፤10፣ ቲቶ 2፤11-14፣ ዕብ 2፤1-3፣ 3:12-15፣ 6:4-6፣ 10:26-31፣ያዕ 2:18-22፣2ጴጥ 1:10-11፣2፤20-22/

8. በአንዲት ቤተክርስቲያን ታምናለች

ቤተክርስቲያን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና አምላክነት የሚያምን ጉባኤ ፣ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአንድነት የተሰበሰቡ፣ የክርስቶስ አካል የሆነች፣ አምልኮ፣ ጥምቀት፣ ቁርባን ፣ ሹመት ወዘተ የምትፈጽም ቅድስት የክርስቶስን ምጽአት የምትሰብክ የምትጠባበቅ ሙሽሪት እንደ ሆነች ታምናለች ።

/ ዘዳ 19፤3፣ ኤር 31፤33፣ ማቴ 8፤11፣ 10፤7፣ 16፤13-19፣ 24፣ 18፤15-20፣ 28፤19-20፣ ዮሐ 17፤14-26፣20፤21-23፣ ሐዋ 1፤7-8፣ 2፤32-47፣ 6፤1-2፣ 13፤1፣ 14፤23፣ ሮሜ 8፤28-29፣ ሮሜ 4፤16፣ 10፤9-15፣ 11፤13-32፣ 12፤1-8፣15፤1-3፣ 1ቆሮ 3፤5-9፣ 7፤17፣ 11፤1፣ 12፤3፣ 14፤26-40፣ 2ቆሮ 5፤11፣ 6፤5፣ ገላ 5፤6፣ 13፤14፣ 6፤1-5፣ 15፣ ኤፌ 4፤1-17፣ 5፤25-27፣ ፊሊ 2፤1-16፣ 1ተሰ 4፤1-12፣ 1ጢሞ 4፤13፣ ዕብ 10፤19-25፣ 1ጴጥ 1፤1-2፣ 13 2፤4-12፣ 21፣ 4፤1-2፣ 10፤11፣ 1ዮሐ 4፤17፣ ይሁዳ 24፣ ራዕ 5፤9-10/

9. በአንዲት ጥምቀት ታምናለች

ጌታችን እንድንፈጽም ያዘዘንን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ስም የምታጠምቅ ምእመናን፣ ይህንን ስርዓት በመፈጸም የክርስቶስን አዳኝነትና ጽድቅ የትንሳኤውን ዓላማ ለህዝብ እንዲመሰክሩ ለሁሉ አንድ ጊዜ የማፍሰስ ሥርዓትን በመፈጸም ታምናለች።

/ ማቴ 3፤1-7፣ 28፤16-20፣ ሐዋ 2፤37-41፣ 8፤35-39፣ 10፤44-48፣ 16:29-34፣ 19፤1-6፣ ሮሜ 6፤3-4፣ ገላ 3፤26-28፣ ቆላ 2፤12፣ 1ጴጥ 3፤28-22 /

10. በቅዱስ ቁርባን ታምናለች

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰረተው ሞቱን የምታስብበትን ከክርስቶስ ጋር ህብረት እንዳለው የምታምንበትን ራሳቸውን መርምረው የቀረቡትን የጌታን እራት/ቁርባንን/ ታምናለች።/ዘጸ 12፤1-14፣ ማቴ 26:29፣ማር 14:22-25፣ሉቃ 22፤17-20፣ዮሐ 6:18-58፣ 1ቆሮ 10:14-21፣ 11:23-32 /

11. የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ታምናለች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ ክርስቶስን ለመቀበል እንደምንወሰድ ከዚያም ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንደምንኖር ክርስቶስን በመጠባበቅ ታምናለች።

/ማቴ 25፤31-46፣ ዮሐ 14፤1-3፣ ሐዋ 1፤9-11፣ ፊሊ 3፤20-21፣1ተሰ 4፤13-18፣ ቲቶ 2፤11-14፣ ዕብ 9፤16-18፣ 2ጴጥ 3፤15፣ ራዕ 1፤7-8፣ 22፤7-20/

12. የሙታን ትንሳኤና ፍርድ ከዚያም የዘላለም ህይወት እንዳለ ታምናለች

ኃጢአተኛም ሆኑ ጻድቃን ከሙታን እንደሚነሱ መልካም ያደረጉ ለዘላለም ሕይወት ክፉም ያደረጉ ለኩነኔ እንደሚሆኑ ወደፊትም እያንዳንዱ ሰው እንደ ስራው በእግአዚአብሔር ፊት ቀርቦ ፍርድ እንደ ሚቀበል ክርስቶስን ያመኑትና በመታዘዝ የተከተሉት ዘላለማዊ

ሕይወት እንደሚያገኙ እስከመጨረሻው ንስሐ ያልገቡት ደግሞ በሲኦል ውስጥ እንደሚቀጡ ታምናለች::
/ዘፍ 18፤25፣1ሳሙ 2፤10፣ መዝ(50)፤6 ኢሳ26፤19 ዳን 12፤2-3 ማቴ 25፤31-46 ማር 9፤43-48 ሉቃ 16፤19-31 20፤27-38 ዮሐ 3፤16-18 5፤25-29 11፤21-27 ሐዋ 17፤30-31 ሮሜ 2፤1-16 14፤7-12 1ቆሮ 15፤12-58 2ቆሮ 5፤10 2ተሰ 1፤5-10 ራዕ 20፤11-15 22:1-15/

ከዚህ በላይ ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች ታስተምራለች:: ይህ እውነት ዛሬ ከብዙ ነገሮች ጋር ቢቀላቀሉና ሌሎች አስተምህሮቶች ደብዛቸው እንዲጠፋ አልያም እንዳይነሱ ተረስተው እንዲቀሩ በአሁኑ ጊዜ የሚደረግ ጥረት ቢኖርም ይህ እውነት ግን ሊሸነፍ አይችልም :: ሁልጊዜም እግዚአብሔር በየዘመናቱ እራሱን ያለምስክርነት አያስቀርምና /ሐዋ:14:16/ ስለዚህ እውነት የሚጋደሉ የእምነት ጀግኖች ሐዋርያቶችን በማስነሳት ይጠብቀዋል:: ዛሬም ለእውነት የሚመሰክሩ በርካታ ናቸው::

## 9. ይህን እውነት መጠበቅ

" ... በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጠ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና አለነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ::" /ኤፌ 5፤26-27/

በዚህ ክቡር ቃል ውስጥ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ የክርስቶስ የልቡ ፍላጎት ወይም መሻት ምን እንደሆነ እናያለን:: እርሱ በመስቀል ላይ ነፍሱን አሳልፎ የሰጠው ስለእርስዋ እንደሆነ እንረዳለን:: በመሆኑም የክርስቶስ ዋነኛ መሞት ስለ ቤተክርስትያን ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በደሙ ስለመሰረታት ነፍሱን በመስጠት እስከ መቃብር ድረስ በመውረዱ ምክንያት ዳግመኛ

እስኪመጣ ድረስ እውነትን እንደ ያዘችና እውነትን እያስተላለፈች በዝታ ጎልብታ እንዲያገኛት በብርቱ ይፈልጋል። ኃላፊነት ለተ ሰጣቸው ለጳጳሳትም አጥብቆ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" ይላል /ሐዋ 20:28/

## 1. ክርስቶስ ከቤተክርስቲያኑ የሚጠብቀው ነገር

### 1.1 በአጋንንት ኃይላት ላይ ጎልታ ትታወቅ ዘንድና የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲገኝባት ይፈልጋል።

ይህ ማለት ለአጋንንት ኃይላት ሁከት ሆና ስራቸውን በማፍረስ ስራ ላይ በመሰማራት ከሩቅ የሚስብ ጸጋ ኖሯት በዚህ ጥበብ የክርስቶስ መሆኗ እንድትታወቅ እንጂ ከአጋንት ኃይላት ጋር ተ ዋርሳና በምድራዊ ሀብቶቿ በመሽቆጥቆጥና በመመካት እንድትታወቅ አይደለም ። ቃሉ እንዲህ ይላልና :-

" ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ስልጣናት /ለአጋንት/ ትታወቅ ዘንድ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘላለም አሳብ ነበር " / ኤፌ 3:10-11 /

### 1.2 ለእግዚአብሔር ከትውልድ እስከ ትውልድ ምስጋናና ክብር እንድትሰጥ ይፈልጋል

ይህም ማለት እግዚአብሔርን ብቻ እያከበረችና እያስከበረች በምድር የእግዚአብሔር ኢምባሲ ሆና ፈቃዱን እንድታስፈጽም እንጂ ሲወርድ ሲዋረድ የመጡትን ሁሉ ፍጥረታትንና ግኡዛንን እያመሰገነችና እየሰገደች በመኖር ዘመኗን እንድታቃጥል አይደለም።፡ቃሉ እንዲህ ይላልና:-

" በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩና

ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ ፡ሁልግዜ ስለሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለሁሉ አመስግኑ።"

"ለእርሱ/ ለእግዚአብሔር/ በቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን" /ኤፌ 3:21 /

## 1.4 ፍቅር እንዲገኝባት

ፍቅር የክርስትና መሰረታዊ ኑሮ የእግዚአብሔርም የዙፋኑ ባሕሪ በመሆኑ ቤተክርስቲያን ይህን አንጸባርቃ የፍቅር ወንዟን በማጠጣት ልታረካ ይገባታል እንጂ ቤተ ትክነትና እርስበርስ የመነካከስ መድረክ ልትሆን አይገባትም። ቃሉ እንዲህ ይላልና :-

« እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ» /ዮሐ 13፣35/

## 1.5 ህዝቡን እንድታስተምር፣እንድትጠብቅ፣ድምጻቸውን እንድትሰማ፣ፈውስም እንድትሰጥ ይፈልጋል

ቤተክርስቲያን ተግታ መጽሐፍ ቅዱስን እንድታስተምር ሕዝቧንም በመንከባከብ ጥያቄያቸውንም በመስማት ፈጣን መልስ እንድትሰጥ እና በተሰጣት ጸጋ እንደቃሉ «በኢየሱስ ስም» /ቆላ 3:17/ እንድትፈውስ እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ በመተረት ህዝቦቿም መረን ወጥተው ያለ ቃሉ ፈውስን በመፈለግ ጋራ ለጋራ እንዲንከራተቱ ጥያቄም ሲጠይቅ አትመራመር በሚል ከውግዘት ጋር የሰነፎች ፍልስፍና በመስጠት ጊዜዋን እንድታቃጥል አይፈልግም ። እግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ ያስቀመጠውን ጸጋ በመጠቀም እንድትባረክ እንጂ ። ቃሉ እንዲህ ይላል።

« እግዚአብሔርም ቤተክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያነትን ሁለተኛም ነብያትን ሶስተኛም አስተማሪዎችን ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን ቀጥሎም የመፈወስ ስጦታን እርዳታንም አገዛዝንም የልዩ ልዩ አይነት ልሳኖችንም አድርጓል» ስለዚህ በዚህ ኢንቨስትመንት ልትጠቀም ይገባታል/1ቆሮ 12:28/።

## 1.6 የወንጌል መልዕክተኞችን እንድትልክ ይፈልጋል

ወንጌል ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ መሆኑን፡ ስለበደላችን ሰው ሆኖ ዙሮ ማስተማሩንና በመስቀል ላይ መሞቱን መቀበሩን መነሳቱን ማረጉን ተመለሶ ዳግም ለፍርድ እንደሚመጣ የሚናገረውን ለሰው ልጆች ሁሉ የሆነውን የምስራች መስበክና ማስተማር / ሮሜ 1:3-4፣ሮሜ 16:25-26 / በመሆኑ የፋጡራንን የጋራ ሽንተረሩን የዛፍ ቅጠሉን ድርሳን ክታቡን በመስበክ የሚያወጉትን መላክና መድረክ መስጠት ማለት አይደለም።

"በወንጌል እንደምሰብከው ከሙታን የተነሳውን ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርሰቶስን አስብ ፡ ይህንንም በመስበክ እንደ ክፉ አድራጊ እስክታሰር ድረስ መከራ እቀበላለሁ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም።" /2ኛ ጢሞ 2፤8 /

«ከዚህም በኃላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጻቸው ላከው»/ ማር15:8ለ /

« በአንጾክያ ባለችው ቤተክርስቲያን ነብያትና መምህራን ነበሩ ... እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ስራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቷቸው» /ሐዋ 13፤1-3/

## 1.7 እንድትገስጽ በዓለም ላይ እንኳ እንድትፈርድ ይፈልጋል

ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ወኪል እንደመሆኗ መጠን በውስጥም ባሉ ምእመናኖቿ ላይም ይሁን በውጭ ላሉት ከፍተኛ መንፈሳዊ ስልጣንና አደራ ስላላት ተሰሚነት አላት።እርሷን የማይሰማ ቢኖር ቅጣት ልትጥልበትና ልትፈርድበትም ሙሉ መለኮታዊ ስልጣን አላት።እግዚአብሔርም ቢሆን በሰማይ ሆኖ ከፍርዷ ጋር ይወግናል ።ይህንን ስልጣኗን መጠቀም የምትችለው ታዲያ እንደቃሉ ስትሔድና ስታስፈጽም እንጂ ከቃሉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን

ሁኔታዎችንና ሰዎችን በሁሉ የተናቁትን በመሾም ውግዘት ዘበከንቱን ልታስፈጽም አይገባትም።

"እንደሚተላለፍ ድንቢጥ ወዲያና ወዲህም እንደሚበርር ጨረባ እንዲሁ ከንቱ እርግማን በማንም ላይ አይደርስም ።" / ምሳ 26:2 /

" እነርሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሁንልህ። እውነት እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል። በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል" / ማቴ 18፤17-18/

" ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን? ... የፍርድ ቤት ቢያስፈልጋችሁ በቤተክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጆች አድርጋችሁ ታስቀምጣላችሁን? አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ እንደዚህ ነውን?" /1ቆሮ 6፤2-5/

እንግዲህ ክርስቶስ የራሱ አካል በሆነችው ቤተክርስቲያን እነዚህን የመሳሰሉ ተግባራትን በማከናውን እንድትጎላና እንድትስፋፋ ይፈልጋል። ለዚህም ሙሉ ስልጣን ሰጥቶ አብሯት ይሰራል / ማቴ 28:19 /። ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያንን የሚፈታተናት በርካታ ፈተናዎች ስለማይታጡ እውነትን እንድትጥልና ከዓለም ጋር ተመሳስላ ፈዛና ደንግዛ ሀሳቧም እቅዷም ምድራዊ ሆኖ እንዲቀር የሚተጉ መንፈሳዊያንና ጉዑዛውያን ኃይላት ስላሉ በእጅጉ ልትጠነቀቅ ይገባታል ።

ለ7ቱ የእስያ አብያተክርስቲያናት የተነገራቸው ማስጠንቀቂያ እውነቱን እንደያዙ እንዲጸኑና ከዓለም ጋር ያላቸውን መመሳሰል እዲያቆሙ ነበር ።

- ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን፦ የቀደመውን ተግባሯን በማድረግ ጸንታ እንድትቆም /ራዕ 2፤1-7/

* ለሰምርኔስ ቤተክርስቲያን፤- በመከራ ጸንታ እንድትቆም /ራዕ2፤8-11/
* ለጴርጋሞን ቤተክርስቲያን፡- በቃሉ እውነት ጸንታ እንድትቆም /ራዕ 2፤12-17
* ለትያጥሮን ቤተክርስቲያን፡- በቅድስና ጸንታ እንድትቆም / ራዕ 2፤18-29
* ለሰርዴስ ቤተክርስቲያን፡- ሌሎችን በማጽናት ጸንታ እንድትቆም /ራዕ 3፤1-6/
* ለፊልድልፊያ ቤተክርስቲያን፡- የጌታን መምጣት በመጠባበቅ ጸንታ እንድትቆም /ራዕ 3፤7-13/
* ለሎዶቅያ ቤተክርስቲያን፤- ከዓለማዊነት ወጥታ ከጌታ ጋር እንድትቆም /ራዕ 3፤14-22/ነበር።

ጆሮ ያለው ይስማ በማለት ሁሉም በጽኑ ሰማያዊ ማስጠንቀቂያ ተመክረዋል ። ነገር ግን እነዚህ የተመከሩ አብያተ ክርስቲያናት ምክሩን ወደ ኋላ በመተውና ቸል በማለት ሁሉም አብያተ ክርስቲያት እንደጠፉ ቀርተዋል ። ዛሬ አገሮቹ የሌሎች እምነት ተከታዮች መሆናቸው አሳዛኝ ነው።

## 2. ይህን እውነት ከመጠበቅ አንጻር የተጋደሉ አባቶች

### 2.1 በመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ለነበሩ ሐዋርያት የደረሰ ፈተና

እንግዲህ ቤተክርስቲያን ያላትን እውነት ለመጠበቅ በርካታ አባቶች ተጋድለዋል ከመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን እንኳ ብንነሳ ክርስቶስ ካረገ ብዙም ሳይቆይ በመካከል መከፋፈል ተጀመረ። /ሐዋ 6:1-4/።ይህንንም በአግባቡ ለመወጣት ብትችል እንኳ የመገ ረዝና ያለመገረዝ ኑፋቄ ገብቶ መልሶ ችግር ውስጥ ጣላት። የሃይማኖት መሪው ኬፋ /ጴጥሮስ/ እንኳ ሳይቀር በግብዝነታቸው ተ ስቦ ተመሳስሎ ነበር /ገላ 1:11-21/ ይህ ሁኔታ ያሳሰባቸው ሐዋርያት በአንጾኪያ ስብሰባ አደረጉ/ሐዋ 15:1-29/በተለይ ሐዋርያው ጳውሎስ

ስለ ወንጌል ሁሉን ዋጋ በመክፈል /1ቆሮ 9:23/ ስለ ራሱ ሲመሰክር:- « በድካም አብዝቼ በመገረፍ አብዝቼ በመታሰር አትርፌ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ ሶስት ጊዜ በበትር ተመታሁ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርኩ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ ሌሊትና ቀን በባህር ውስጥ ኖርሁ ብዙ ጊዜ መንገድ ሄድኩ በወንዝ ፍርሃት በወንበዴዎች ፍርሃት በወገኔ በኩል ፍርሃት በአህዛብ በኩል ፍርሃት በከተማ ፍርሃት በምድረ በዳ ፍርሃት በባህር ፍርሃት በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም በብርድና በራቁትነት ነበርኩ:: የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው::» አለ /2ቆሮ 11:23-28/ ሌሎቹም ሐዋርያትና ደቀ መዝሙርቶቻቸው ከጌታ የተቀበሉትን የወንጌል አደራ በመጠበቅ በታላቅ ሰማዕትነት ሁሉም አልፈዋል:: የድል አክሊሎቻቸውን ከጌታ ዘንድ ለመቀበል ይጠባበቃሉ :: /2ጢሞ 4:6-8/

« ከዚያም በኋላ ቤተክርስቲያን በደረሰባት ልዩ ልዩ ፈተናዎች ስለወልድ አምላክነትና ስለ ስላሴ እውነት በጉባኤ ኒቂያ: ስለ መንፈስ ቅዱስም አምላክነትና ከአብ መውጣት በጉባኤ ቁስጥንጢኒያ : ስለምስጢረ ስጋዌም በጉባኤ ኤፌሶን: ታላቅ ተጋድሎ በማድረግ እውነተኝነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን አስተላልፋለች::»[70]

ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ተመልሰን የቤተክርቲያን ሁኔታ ብንቃኝ እውነትን በፍሬምናጦስ አማካኝነት ከአረማዊነት ወደ አምልኮተ - እግዚአብሔር ተመልሳለች :: ይሁን እንጂ ብዙም ሳትቆይ በርካታ ፈተናዎችን አስተናግዳለች አንድ ያልታተመ ጽሁፍ እንደሚገልጸው

---

70. የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ በአባ ጎርጎሪዮስ በ1978 ዓ.ም ገጽ 50 አንቀጽ 3

ከበርካታ ፈተናዎች ውስጥ የሚከተሉትን አስፍሯል ፡፡

## 2.2 ከአረማውያን የመጣው ትምህርት በውስጧ እየተስፋፋ መምጣት

ተሰዓቱ ቅዱሳት / ዓኙ መነኮሳት / ከ560 - 600 ዓ.ም ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ከሮም ግዛት በመምጣት «እጸድቅ ያሉ መንኩሶ እካስ ያለ ታግሦ» በማለት ህዝቡን ወደ ጫካና ገዳም ገድመው እንዲገባ ያለበትንም ኀላፊነት እንዲተው አስተማሩ ፡፡ "ያን ጊዜም ይህ ትምህርት ከአረማውያን የመጣ እንጂ መጽሀፍ ቅዱሳዊና የአብው ታሪክ አይደለም፡፡

ይህ የገለልተኝነት መንፈስ ለአለም የተጣለባትን የወንጌል አደራ በእጅጉ ይቃረናል በማለት ቤተክርስቲያን በከፍተኛ ሁኔታ ተቃውማ እንደነበር የራሷ ታሪክ ያስረዳል፡፡በኋላ በኋላ ግን በበየዘመናቱ የነገሱ ነገስታቶችና መበለቶች «ሐጢትን የመተዊያ መንገድ» በማለት ወደ ቤተክርስቲያን አሾልከው አስገቡት፡፡»[71]

## 2.3. የእስልምና መግባት

- በመሐመድ አጎት በጃፋር መሪነት ከ600 - 800 ዓም ከመሐመድ ዘመዶች 85 ያህል ጥገኝነት ጠይቀው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ቤተክርቲያንን አሳደዷት የነበራትንም የስላሴ ምስጢርና የሚስጥረ ስጋዌ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ለመበረዝ በእጅጉ ሞከሩ፡፡ ነገር ግን በዘመኑ የነበሩ ክርስቲያኖች ወንጌልን ታጥቀው ህዝባቸውን በማስተማር በሰማዕታትነት እስኪያልፉ ድረስ ስለ እውነት ቆመው ይህን ትምህርት ማስተላለፋቸውን የኢትዮጵያታሪክ ያስረዳል ፡፡

## 2.4. የዮዲት የቤተእስራኤል መጣጣፍ

የእስልምና ተጽእኖ በተጧጧፈበት ሁኔታ በ800 ዓ.ም በዮዲት አዝማችነት የተመራው የቤተ እስራኤል አመጽ በከባድ ሁኔታ ተነስቶ

---

71.መጽሐፈ ጽድቅ ወቅድስና በሊቀስልጣናት ገ/ጊዮርጊስ ወ/ትንሳኤ ገጸ224 1946ዓ.ም

የክርስትና መጀመሪያ ስፍራ የነበረው የአክሱም ከተማ ወደመ:: የሳባውያን መንግስት ተደመሰሰ ::አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ መጽሐፍት ተቃጠሉ መምህራን ቀሳውስት ዲያቆናትና ምዕመናን ሁሉ ተገደሉ ::ይህ ደግሞ ብዙ የተሳሳቱ ንፏቂያት በር አግኝተው በቤተ ክርስቲያን ተስፋፉ :: በርካታዎች ግን ለቤተክርስቲያንና ለያዙት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ሞቱ ::

## 2.5. ክርስትና ተዘንግቶ የስልጣን ሽኩቻ መምጣት

ከ900 እስከ 1200 ዓ.ም ከዮዲት የ40 ዓመት ግዛት ማክተም በኋላ ስልጣን ወደ ነገደ ዛጉዌ ከነገደሳባ ስለተመለሰ የወደቀው የሳባውያን ነገድ መልሰው ትልቅ ሽኩቻ ፈጠሩ:: ሁሉም አውድማቸው አብያተ ክርስቲያናት ስለነበር ፍቅር ጠፍቶ አምልኮተ እግዚአብሔር ተዘንግቶ ቤተክርስቲያን የዘርና የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ወደመሆን አዘመመች:: በዚህም የክርስቶስን ወንጌል የያዙ በርካታ ክርስቲያኖች ቢታገሉም እንኳ ክርስትናው በፊት ቆሞ ወደነበረበት ሁኔታ ሊሆን አልቻለም::ይሁን እንጂ በዚህም ውስጥ የቤተክርስቲኗ እውነት በጭልጭልታም ቢሆን ተላልፏል::

## 2.6 የቤተ መንግስትና የቤተ ክህነት መጣመር

ከላይ ባየነው ተጽእኖ አማካኝነት ከ1300 ዓመት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት የፖለቲካና የሐይማኖት መሪ መሆን ጀምሮ እስከ አፄ ሃይለስላሴ ንጉሰ ነገስት መንግስት ድረስ /እስከ 1966 ዓ.ም/ ቤተ መንግስት ከቤተ ክህነት ጋር ተጣመረ:: በዚህም ሁሉም ባይባሉም ነገስታት የራሳቸውን ስምና ዝና እንዲጻፍላቸው እንዲመሰገኑ ምስላቸውም ቅጥረ ቤተክርስቲያን እንዲሰቀልና ማዕጠንት እንዲታጠን : ለብቻቸው ማስቀደሻ ስፍራ እንዲዘጋጅላቸው:ሲሞቱም ቃል ኪዳን ተቀብለዋል በሚል ጻድቃን ተብለው የእለተሞታቸው ቀን እንዲዘከርላቸው: በስማቸው ታቦት እንዲቀረጽላቸው አጥንታቸውም ህዝቡን እንዲገዛ አስምለውና አስገዝተው በመሄዳቸው ቤተክርቲያን

ዛሬላለችበት ታልቅ ውድቀት ምክንያት ሆኗል። የእነርሱም ካባና መቆሚያ መንበሮቻቸውን ሳይቀር ተይዞ ማዕጠንት በማጠን ሻማና ጧፍ በማብራት መልክአ እንኳ ሳይቀር ተጽፎላቸው ማህሌት የሚቆምላቸው ጊዜያት አሉ። በነዚህ ሁሉ ግን ቤተክርስቲያን የወንጌል እውነትን የያዙ ወገኖች ለንጉስ አልሰገዱም ... ወዘተ በማለት በሐሰት የሞቱ በእውነት በርካታ መሆናቸውን ገድለ እስጢፋኖስ ዘጉንዳ ጉንዲን ማንበብ በቂ ነው ።

## 2.7. አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደግሞ ባእድ አምልኮን በማወጅ ወደ ቤተ ክርስቲያን በማስገባቱ

" ማርያምና መስቀል ከፈጣሪ ጋር እንዲሰገድላቸው"[72] ታላላቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች በማስገባቱ እነ አባ እስጢፋኖስ አምደ ሃይማኖት ወማህቶተ ቤተክርስቲያን ዘጉንጋጉንዲ በእጅጉ እየተ ቃወሙ" በስላሴ ላይ አራተኛ አልጨምርም ራሳችን ለሱሉስ ቅዱስ አስገዝተናል ለሌሎች አንሰግድም "በማለታቸው ምክንያት አስረውና 40 ጅራፍ ለእያንዳንዳቸው በመግረፍና በጉድጓድ አንገታቸውን ብቻ ብቅ አድርገው የጋማ ከብት እየነዱባቸው በዚያም ሳይበቃ ሲቀር እጃቸውና እግራቸውን በስለት በመቆራረጥና በመጥባት እንዲሞቱ አድርጓል።[73] ይሁን እንጂ ዛሬም እንኳ ደቀመዛሙርቶቹ ቤተ ክርስቲያኗ ወደ ጥንት መሠረቷ ተመልሳ እግዚአብሔርን ብቻ እንጂ በፍጡራን እንዳትደገፍ በመታገል ላይ የሚገኙ አያሌ ናቸው።

## 2.8 ክፋት እየጨመረ መሄድ

የአባ እስጢፋኖስ ደቀመዛሙርት በወንጌል ታጥቀው ቤተ ክርስቲያን የገባባትን የስህተት አስተምህሮ እንድትላቀቅ ተግተው

---

72. የዘወትር ጸሎት በውዳሴ ማርያም

73. ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዲ

ቢያስተምሩም በአፄ በእደ ማርያም፡ በአፄ እስክንድር፡ በአፄ ዘመደ ጽዮን በአፄ ናዖድ በአፄ ልብነ ድንግል ... ወዘተ እየታደኑ ተ ደበደቡ፡ ተገደሉ፡ በቅጥረ ቤተክርስቲያንም እንዲባረሩ ይደረጉ ነበር፡፡ ውስጥ ለውስጥ እየተስፋፋ የመጣውም የአስማት የጥንቆላና ከአጋንት ጋር መዋረስም በዝቶ ከቤተክህነት እስከ ቤተመንግስት ድረስ እንኳን አጥለቀለቀው፡፡

ይህም ሳይበቃ 1500 ዓ.ም በአፄ ልብነ ድንግል ዘመን ግራኝ ተነስቶ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠለ፡፡ ንዋየ ቅዱሳትን ዘረፈ መምህራን ቀሳውስትና ዲያቆናትን ምዕመንን ሙስሊሞች እንዲሆኑ ቢያስገድድም አንሰልምም በማለታቸው ተገደሉ ፡፡

ከእርሱም በኋላ ወንጌል ተዳክሞ የኦርቶዶክሳውያንና የካቶሊካውያን ጦርነት በአፄ ሲስንዮስ ተጀምሮ ብዙ ሰው አለቀ፡፡ ይህም እንኳ በአፄ ፋሲል ሲያከትም መልሶ ቅብዓትና ጸጋ የሚባሉ ቡድኖች ከ1600 እስከ 1800 ዓ.ም ድረስ በቤተክርስቲያን ተነስተው ሲከራከሩና ሲዋጉ ብዙዎች ሞቱ፡፡ ከዚያም « ካራ » የተባለው ቡድን በ1900ዓ.ም ተነስቶ ምንም የአውጣኪን እምነት የያዘ ቢሆንም « የኦርቶዶክስ ተዋህዶ » እኔ ነኝ በማለት ስልጣን ይዞ ቅባትና ጸጋ የተ ባሉትን አስፈጀ፡፡ በአሁኑም ጊዜም የአበው ትምህርት እየደከመ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያነት ቀንሶ« የመናፍቅ ነው » በሚል መጠሪ ያ እየተጠራ በውስጧ ሲጥ ሲል ትንሽ ቀርቶታል ፡፡ ዛሬ በምትኩም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ የስብሰባ / የሲኖዶስ ውሳኔዎችን / የያዘ ለማሳተ ም ደፋቀና ማለቱን አልተወችም፡፡ ይህ ባይዘጋጅ እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜዋን ሳታጠፋ የገድላትና የድርሳናት መዓት አውደምህረቷን አጣበውላታል፡፡

**8ኛ. የተሃድሶ መነሳት ከ1950 ጀምሮ**

ቤተክርስቲያኗ የአበው አስተምህሮ ልትይዝ ይገባል፡፡ በኋላ በኋላ የመጣላትን ስህተት የተቀበለችውን ቤተክርስቲያናችን በንስሃ

እንድትመለስ ወንጌል በአውደ ምህረታችን በስልጣን ተገብቶ ስፍራ ይያዝ ምእመናን በቃለ እግዚአብሔር ይታጠቁ ቤተክርስቲያናችን ትጠናከር የሚሉ ቅንአተ-ቤተክርስቲያን የበላቸው በርካታ የቤተ ክርስቲያኗ መነኮሳት፣ ቀሳውስት ዲያቆናትና ምዕመን ሁሉ ተነሱ። ነገር ግን ከፉዎች ነግሰው ብዙዎችን አሳደዱ ገደሉ መጽሐፍ ቅዱስን አቃጠሉ፣ የስም ማጥፋት ዘመቻቸውንም አጧጧፉ ። ይሁን እንጂ ጥያቄው እየሰፋ እንቅስቃሴውም እየጎለበተ ከመንበረ ፓትሪያሪክ እስከ አዲስ አጥቢያ ድረስ ተደርሷል።[70]

## 10. ማጠቃለያ

"ብዘገይ ግን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ። ቤቱም የእውነት አምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነው" /1ጢሞ 3፤15/

እንግዲህ አንባቢ ሆይ ክርስትና በክርስቶስ ብቻ እንዲሆንና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከጥንት መሠረቷ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። መጽሐፍ ቅዱስ የአበው መሠረት መሆኑና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ሌላ መጽሐፍ ለአብነት እንዳልጠቀሱ ሃይማኖተ አበውን ማገላበጥ በቂ ነው። በመሆኑም አባቶቻችን የሰበኩትን መዳን በክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነና በእርሱ የመኖር ምስጢር አጥብቀህ ያዝ ራስህም በቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ፈጥረህ ቃሉንና ድምጹን እየሰማህ ኑር ሁሉን እንደ ስራው ይከፍል ዘንድ ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቶሉ ይመጣል። / ራእ22:20 /

ሌላም የምመክርህ ነገር አለኝ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፡፤ እንዳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ /ማቴ 10፤32/ ይህም የክብርና የዘላም ድነት የሆነውን ወንጌል /ማር 16፤8/ ለቤተሰብህ ለቤተክርስቲያናችን

ምዕመናን ብሎም ለአህዛብ ሁሉ ስበክ።በጊዜውም አለጊዜውም ጽና ። ወንጌል ሰባኪነትን ስራህ አድርግ/ 2ጢሞ 4:1-5 / "ብዙ ሰዎች ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉና" / ዳን 12:3 / ።

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለአባቶቻችን አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ! አሜን